# በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት
## የንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ

# ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ
# የግል ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም

ጥቅምት 2000 ዓ.ም.
አዋሳ

# ማውጫ

ገጽ

**መግቢያ**.....................................................................................................................1

## ክፍል አንድ
## የክልሉ አጠቃላይ ገጽ ና የግል ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ሁኔ

1. የክልሉ አጠቃላይ ገጽ ..............................................................................................4
2. የግሉ ኢንቨስትመንት መነሻ ሁኔታ ፣አደረጃጀትና ያለው የማስፈጸም አቅም ደረጃ.............16
3. የግሉ ኢንቨስትመንት ንቅስቃሴ ሁኔ ..........................................................................18

## ክፍል ሁለት
## የክልሉ የኢንቨስትመንት ፖቴንሻልና የልማት ቀጠናዎች

### 2.1 የክልሉ የኢንቨስትመንት ፖቴንሻል

1. ለግብርና ልማት ያለው ፖቴንሻል....................................................................24
2. ለአግሮ-ኢንዱስትሪ ልማት ያለው ፖቴንሻል.......................................................25
3. ለቱሪዝም ኢንዱስትሪ ያለው ፖቴንሻል.............................................................26
4. ለኢንዱስትሪ ልማት ያለው ፖቴንሻል...............................................................26
5. ለኃይል ማመንጫ ያለው ፖቴንሻል....................................................................27
6. ለማዕድንና ኢነርጂ ልማት ያለው ፖቴንሻል........................................................27

**2.2 የልማት ቀጠናዎች፣ የዕድገት ማዕከላትና የልማት ኮሪደሮች**.............................27

## ክፍል ሶስት
## በክልሉ የግሉ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የተከናወኑ ተግባራት፣ የተገኙ ውጤቶችና መሠረታዊ ችግሮቻቸው

3.1. በክልሉ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የተከናወኑ ተግባራትና ጉድለቶቻቸው.............................35
3.2 የግሉ ኢንቨስትመንት መሠረታዊ ችግሮች.......................................................................40
3.2.1 ከባለሀብቶች አንጻር የሚታዩ ችግሮች.........................................................................41
3.2.2 ከአገልግሎት አቅርቦት አንፃር ያሉ ችግሮች...................................................................43
3.2.3 የመሠረተ ልማትና የፋይናንስ አቅርቦት ችግሮች..............................................................45
3.2.4 ሌሎች ችግሮች......................................................................................................46

## ክፍል አራት
## የግሉ ኢንቨስትመንት መስፋፋት በክልሉ ኢኮኖሚ ልማት የሚኖረው አስተዋጽኦና የትኩረት አቅጣጫዎች

4.1 የግሉ ኢንቨስትመንት መስፋፋት በክልሉ ኢኮኖሚ ልማት የሚኖረው አስተዋጽኦ ..................47
4.2 የግሉ ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ የትኩረት አቅጣጫዎች
1. የነጻ ገበያ ፖሊሲ አቅጣጫን መከተል..........................................................................54
2. ግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫን መከተል...................................................55
3. ኤክስፖርት መር የኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫን መከተል...............................................55
4. ንጽጽራዊ ጠቀሜ ን መሠረት ያደረገ የሀብት አጠቃቀም አቅጣጫን መከተል..........................56
5. የህዝብ ተሳትፎና ተጠቃሚነትን የማረጋገጥ (ጉልበት ተኮር) አቅጣጫ መከተል......................56
6. የማስፈጸም አቅም የመገንባት አቅጣጫን መከተል...........................................................57
7. የፕሮግራሙን ቀጣይነት የማረጋገጥ አቅጣጫ መከተል.......................................................58

## ክፍል አምስት
## የግሉ ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም ራዕይ ዓላማና ግብ

1. የፕሮግራሙ ራዕይ.............................................................................................59
2. የፕሮግራሙ ዓላማ.............................................................................................60
3. የፕሮግራሙ ግብ...............................................................................................60
4. የፕሮግራሙ የጊዜ ሰሌዳ እና በጀት ማጠቃለያ........................................................65
5. የግሉ ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም አፈፃጸም ወሰን (Scope)...................................65

## ክፍል ስድስት
## የግሉ ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም ንዑሳን ፕሮግራሞች

1. የአንድ ማዕከል አገልግሎት አሰጣጥ ንዑስ ፕሮግራም.......................................................66
2. የፕሮሞሽንና የመረጃ ሥርዓት ንዑስ ፕሮግራም...........................................................70
3. የግብአቶችና የጉልበት ሠራተኞች አቅርቦት ንዑስ ፕሮግራም...........................................74
4. የኢንቨስትመንት መሬት ዝግጅት፣ አቅርቦትና የመሠረተ ልማት ንዑስ ፕሮግራም......................79
5. የጥራት ስታንዳርድና የውጪ ገበያ ንዑስ ፕሮግራም.......................................................88
6. የኢንተርፕረነርሽፕ፣ ስትራቴጂክ ፕላኒንግና ፋይናንስ ንዑስ ፕሮግራም...............................90
7. የማስፈጸም የአቅም ግንባታ ንዑስ ፕሮግራም...............................................................95

## ክፍል ሰባት
## የግሉ ኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ፕሮግራም የአፈጻጸም ስልት የክትትልና ግብረመልስ ሥርዓት

1. የግሉ ኢንቨስትመንት የልማት ፕሮግራም ማስፈጸሚያ ሥልቶች.........................................97
2. የግሉ ኢንቨስትመንት የልማት ፕሮግራም የአፈጻጸም ደረጃዎች......................................100
3. የግሉ ኢንቨስትመንት የልማት ፕሮግራም ማስፈጸሚያ ትስስር.........................................101
4. የልማት ፕሮግራሙ ክትትል፣ ግምገማና ግብረ-መልስ ..................................................102
**ማጠቃለያ**-----------------------------------------------------------------------------------103
**ዋቢ መጽሐፍት**...............................................................................................105
**አባሪዎች**.......................................................................................................106

# መግቢያ

ሀገራችን ከምዕተ ዓመት ለሚበልጥ ዘመን የፊውዳልና የደርግ ዕዝ ሥርዓት ስትከተል በመቆየቷ ለግሉ ኢንቨስትመንት መስፋፋት የሚያግዝ ምቹ ሁኔታ ሳይመቻች መቆየቱ የሚታወስ ነው ። ከዚህም የተነሳ በከፋ የድህነት ሽክርክሪት ውስጥ ተዘፍቀን ለዘመናት እንድንቆይና የሥራ አጥነት ችግር እንዲስፋፋ፣ ማህበራዊ ቀውስ እንዲባባስ እንዲሁም ለተደጋጋሚ ረሃብ ተጋላጭ እንድንሆን ተገደናል፡፡ ሁን እንጂ ይህንን ታሪክ በማድረግ ከገባንበት የድህነትና የ|ላቀርነት ሽክርክሪት ውስጥ ለመውጣት የግሉ ሴክተር መስፋፋት ተኪ የሌለው እንደሆነ ግልጽ ሆኗል፡፡

አሁን ባለንበት ዓለም ያለው ተጨባጭ ሁኔታ እንደሚያሳየው የግሉን ኢንቨስትመንት ማበረታታትና ማስፋፋት አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ለማፋጠንና ካሉብን ዘርፈ ብዙ ችግሮች ለመላቀቅ ዋነኛ መፍትሔ ተደርጎ እየተወሰደ ነው፤ ሊወሰድም ይገባል፡፡

ስለሆነም የአገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶችን በብዛት በመሳብ የካፒታል ክምችት ለመፍጠር፣ ሥራ አጥነትን ለማስወገድ፣ የድህነት ሽክርክሪትን ለመበጣጠስና የኢኮኖሚ ዕድገት ለማፋጠን እንዲቻል ለግሉ ኢንቨስትመንት መስፋፋት ቁልፍ የሆኑ ሁኔታዎችን በአፋጣኝ ማመቻቸትና ማነቆ የሆኑ ችግሮችን ከሥር መሰረታቸው ማድረቅ እጅግ አንገብጋቢ ጉዳይ መሆኑን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ወስኖ እነሆ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ከጀመረ አምስት ዓመታት አልፈዋል፡፡

ከዚህም በመነሳት በሀገራችን የግሉን ኢንቨስትመንት ለማስፋፋትና ለማበረታታት ልዩ ልዩ የኢንቨስትመንት አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ወጥተው አበረታች እንቅስቃሴዎች እየተካሄዱ ይገኛሉ፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን የዳበረ የነፃ ኢኮኖሚ ሥርዓት ግንባ መሠረት ያደረጉ የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ስልት፣ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ፣ የከተማ ልማት ፖሊሲ ወዘተ ሰነዶች ተዘጋጅተው በሀገር አቀፍና በክልላችን ደረጃ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛሉ::

በክልላችንም ቢሆን የግሉ ሴክተር የኢኮኖሚው አንቀሳቃሽ ሞተር ባልሆነበት ሁኔታ ፈጣን ዕድገት ማምጣት የማይታሰብ ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም የግሉን ሴክተር ለማስፋፋት የሚያስችሉ በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡ በክልሉ የኢንዱስትሪ ልማትን ለማስፋፋት ይቻል ዘንድ የክልሉ አጠቃላይ የኢንዱስትሪ ፖቴንሻል የሚያሣይ ጥናት ተደርጎ ከሰባት መቶ በላይ የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች የተለዩ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ከሦስት መቶ ለሚበልጡ ኢንዱስትሪዎች የፕሮጀክት ፕሮፋይል ተዘጋጅቷል፡፡ እንዲሁም በክልላችን የሚሌኒየም የልማት ግቦችን (MDGS) ለማሳካት፣ ፈጣንና ዘላቂ ልማት በማምጣት ድህነትን የማስወገድ ዕቅድን (PASDEP) ለማሳካት ና የሶስተኛውን የሰላም፣ የልማትና የዲሞክራሲያዊ ግቦችን ውን ከማድረግ አኳያ ለልማት ቅዶቻችንና የመዋዕለ ንዋይ ፍሰት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜ ባላቸውና የ ምቅ ሀብት አቅማቸው ተለይተው በ ወቁ የ ድገት

ማዕከላትን(Growth poles) ና የልማት ኮሪደሮችን (growth coreders) ለይቶ መረባረቡ የተሻለ የልማት አቅጣጫ መሆኑ ስለታመነበት ይኼው ጥናትም ተከናውኖ የ ድገት ማዕከላት (Growth poles) እና የልማት ኮሪደሮች (growth coreders) ተለይተዋል፡፡

ስለሆነም ዘላቂና ሁለንተናዊ ዕድገት ለማምጣት በሚደረገው ጥረት ውስጥ የግል ኢንቨስትመንት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አስተዋጽኦ የጎላ ንዲሆን ከፍ ብሎ የተጠቀሱትን የኢንዱስትሪ ፖቴንሻል እንዲሁም የ ድገት ማዕከላት (Growth poles) እና የልማት ኮሪደሮች (growth coreders) ጥናቶችን ከግንዛቤ ውስጥ ባስገባ መልኩ ይህ የግል ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም ተዘጋጅቷል፡፡ የዚህ ፕሮግራም ዓላማ ከፍ ብሎ በተመለከተው መሠረት ለአንድ ሀገር ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት ቁልፍ ሚና የሚጫወተውን የግሉን ኢንቨስትመንት ለማስፋፋት የሚያግዙትን ሁለገብ ድጋፎች በመለየት ለዘርፉ መስጠት ሲሆን እነዚህ ድጋፎች የሚሰጡት የገበያ ውድድርን በማጠናከር ባለሀብቶች በራሳቸው የሚያደርጉትን ጥረት የበለጠ ለማገዝ ነው ፡፡ ይኸው በኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ሠነድ ላይ እንደሚከተለው በግልጽ ተቀምጧል፡፡

*#መንግሥት ለልማታዊ ባለሀብቶች የሚሰጠው እገዛ የገበያ ውድድርን የሚያጠናክር እንዲሆን ከማድረግ አኳያ በመመሪያነት ሊያገለግሉ የሚገባቸው ሁለት መሠረታዊ መርሆዎች አሉ፡፡ /በመጀመሪያ ደረጃ መንግሥት የሚሰጠው እገዛ ባለሀብቶች ጠንካራ ውድድር ባለበት ገበያ ውስጥ ገብተው በውድድር አሸናፊ ለመሆን የሚያስችላቸውን አቅም እንዲገነቡ እንጂ፣ ከገበያ ውድድር ተከልለው እንዲበለጽጉ የሚያደርግ መሆን የለበትም፡፡ መንግሥት እያንዳንዷን ድጋፍ ከዚህ አኳያ እየመዘነ የሚሰጥበት አሰራር መከተል አለበት፡፡ ባለሀብቱም የመንግሥት እገዛ በገበያ ፍልሚያ ለማሸነፍ ይችል ዘንድ የማስታጠቅና የማብቃት እንጂ ከፍልሚያው የመከለል ዓላማ የሌለው እንደሆነ በጥብቅ እንዲገነዘብ መደረግ አለበት፡፡ በሁለተኛ ደረጃ መንግሥት እገዛውን መስጠት ያለበት በእንደዚህ ዓይነቱ ፍልሚያ አሸንፎ ለመውጣት ፍላጎቱና ዝግጁነቱ ላለው ብቻ መሆን ይኖርበታል፡፡ የራሱን ጊዜና ገንዘብ መስዋዕት አድርጎ ለመወዳደር ዝግጁነት ላለው ባለሀብት መንግሥት ሁሉን አቀፍ ድጋፍ ሊያደርግለት ይገባል፡፡ የራሱን ጊዜና ገንዘብ መስዋዕት አድርጎ ለመፍጨርጨር ዝግጁነቱ የሌለውና በመንግሥትና በህዝብ ጫንቃ ለመክበር የሚፈልገውን ግን ከጥገኝነት ሊላቀቅ የማይችል ነውና መንግሥት ምንም ዓይነት እገዛ ሊያደርግለት አይገባም፡፡;*

ስለሆነም ከወዲሁ ሊሠመርበት የሚገባው ጉዳይ የግሉ ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም ሲዘጋጅ ማዕከል ያደረገው በገበያ ውድድር ውስጥ ገብተው ለማሸነፍ የሚጥሩትን ልማታዊ ባለሀብቶችን እንጂ የጥገኝነት አስተሳሰብ የተጠናወታቸውንና በአቋራጭ ለመክበር የሚሯሯጡ ግለሰቦችንና ድርጅቶችን ለማገዝ ያለመሆኑ ነው፡፡

ከላይ በተጠቀሱ መነሻ ሐሳቦችን ማዕከል በማድረግ የተዘጋጀው ይህ ሰነድ 7 ዋና ዋና ክፍሎች ያካተተ ሲሆን **በክፍል አንድ** የክልሉ አጠቃላይ ገጽ ና የግሉ ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ሁኔ ፣ **በክፍል ሁለት** የክልሉ የኢንቨስትመንት ፖቴንሻል ይዳስሳል፡፡ **በክፍል ሶስት** በግሉ ኢንቨስትመንት ልማት መስፋፋት ዙሪያ የተገኙ ውጤቶችና የሚታዩ መሠረታዊ ችግሮች የክፍተት ዳሰሳ ቀርቧል፡፡ **ክፍል አራት** የግሉን ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም መርሆዎች ያካተተ ሲሆን **ክፍል አምስት** የግሉ ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም ራዕይ፣ ዓላማና ግብን አካቶ የያዘ ነው፡፡ **ክፍል ስድስት** የግሉን ኢንቨስትመንት ልማት

ፕሮግራምና ንዑሳን ፕሮግራሞችን የሚዘረዝር ሲሆን በመጨረሻም **ክፍል ሰባት** የፕሮግራሙን የክትትል፣የግምገማና የግብረ መልስ ሥርዓት የሚዳስስ ይሆናል፡፡

በሰነዱ የተካተቱት መሰረ ዊ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ንዲሆኑ በሁሉም ወገን ትኩረት ተሰጥቶ በቅንጅት መንቀሳቀስ ያስፈልጋል፡፡ የፕሮግራሙን ስኬ ማነት ለማረጋገጥ የተለያዩ ፕሮጀክቶች ተዘጋጅተው ተግባራዊ መሆን የሚጠበቅ ሲሆን በዚህ ሰነድ ላይ በየንዑስ ፕሮግራሙ ሥር ጠቃሚ የሆኑ የፕሮጀክት ሐሳቦች ተዘጋጅተው ቀርበዋል፡፡ ስለሆነም በግል ኢንቨስትመንት ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች፣ ግለሰቦች፣ በፌዴራልና በክልል ደረጃ የሚገኙ አስፈጻሚ አካላት ንዲሁም የልማት ይሎችና አጋሮች ለፕሮግራሙ መሳካት ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ጥቅምት 2000 ዓ.ም

<u>አዋሳ</u>

# ክፍል አንድ

## የክልሉ አጠቃላይ ገጽ ና የግል ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ሁኔ

## የክልሉ አጠቃላይ ገጽ

ይህ ክፍል **#የክልሉ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ጂኦግራፊያዊ ሁኔታ በአጠቃላይ ምን ይመስላል?;** ለሚለው ጥያቄ ምላሽ  የሚሰጥ ይሆናል፡፡

### 1.1 ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ

የደቡብ ብሔሮች  ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በሰሜናዊ የሐሩር መስመርና ከምድር ወገብ አካባቢ ከ $4^0$27 ስከ $8^0$30 ሰሜናዊ ላቲትዩድና ከ$34^0$ $21^1$ ስከ $39^{0-}$ $11^1$ ምሥራቅ ሎንግቲዩድ ድረስ ባለው ቦ  ላይ ይገኛል፡፡ ክልሉ በ13 ዞኖች፣ በ8 ልዩ ወረዳዎች፣በ134 ወረዳዎች እና 22 የከተማ አስተዳደሮች የተከፋፈለ ሲሆን አጠቃላይ የቆዳ ስፋቱም 110,931 ካሬ.ኪ.ሜ ነው፡፡ ከሀገሪቱም የቆዳ ስፋት 10% የሚሆነውን  ንደሚሸፍን ያለው መረጃ ያረጋግጣል፡፡

### 1.2 የአየር ንብረት

የደቡብ ክልል በአምስት ሥነ ምህዳሮች (Agro Ecological Zones) የተከፈለ ሲሆን 57.5 በመቶ ቆላና ከፊል በረሃ፣ 33.9 በመቶ ወይና ደጋ  ና 8.6 በመቶ ደጋና ውርጭ የአየር ንብረት ሽፋን ያለው ነው፡፡  ንደ ብሔራዊ ሜትሮሎጂ አገልግሎት ድርጅት መረጃ በክልሉ የዝናብና የሙቀት ስርጭት መጠን ከቦ  ቦ  የሚለያይ ሲሆን የዝናብ ድግግሞሽ፣ የሚቆይበት ጊዜና መጠኑ ከደቡብ ወደ ሰሜናዊ ምዕራብና ምሥራቅ አካባቢ ሲጨምር በአንጻሩ የሙቀት መጠኑ ይቀንሳል፡፡ የክልሉ ዓመ  ዊ አማካይ የዝናብ መጠን ከ400–2200 ሚ/ሜ ሲሆን አማካይ የሙቀት መጠንም ከ$7.5^0{}_c$–$27.5^0{}_c$ ይሆናል፡፡

### 1.3. የመሬት አቀማመጥ

የክልሉ የተፈጥሮ አቀማመጥ በዋነኛነት የተመሰረተው በባሮና በኦሞ ጊቤ ተፋሰሶች ላይ ሲሆን የስምጥ ሸለቆ ተፋሰስ በምሥራቃዊ አካባቢ ያለውን የክልሉን አካባቢ መሀል ለመሀል አቋርጦ ያልፋል፡፡ ከነዚህም ሁኔ  ዎች በመነሳት የተለያዩ የከርሰ ምድር የተፈጥሮ ክስተቶች (Geological

Phenomena) በምሥራቅ አካባቢ የሚፈራረቁበትና ሰፊ ብዝሐ ሕይወት (Biodiversity) የሚገኝበት ክልል ንዲሆን አስችለው ል:: ከዚሁም በተጨማሪ ዝቅተኛው የመሬት ከፍ በ ችኛው የኦሞ ወንዝ መጨረሻና ወደ ቱርካና ሀይቅ መግቢያ አካባቢ የሚገኝ ሲሆን ከባህር ወለል በላይ ያለው ከፍ 376 ሜትር ሲሆን ከፍተኛው ቦ በጋሞጐፋ ዞን ውስጥ የሚገኝ ሆኖ ከባህር ወለል በላይ ያለው ከፍ 4200 ሜትር ነው:: ይህም ከፍ የሚገኘው በጉጌ ተራራ ላይ ነው::

## 1.4. የተፈጥሮ ሀብትን በሚመለከት

በክልሉ ያለው የተፈጥሮ ሐብት ስፋትና ስርጭት ከቦ ቦ የሚለያይ ሲሆን ዋንኞቹ የተፈጥሮ ሐብት ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው::

### ሀ. የደን ሀብት

ተፈጥሮአዊ የሆነው የ ጽዋት ሽፋን መጠን በክልሉ ውስጥ ከቦ ወደ ቦ በተለያየ መጠንና ስርጭት ይገኛል:: በአመዛኙ ግን በስፋት በ ፅዋት ተሸፍኖ የሚገኘው አካባቢ የክልሉ ምዕራባዊ ክፍል ነው:: የክልሉ ሰሜናዊ ምዕራብ ደጋማና ተራራማ ቦ ዎች በደጋማ የተፈጥሮ ደን የተሸፈኑ ሲሆን ደቡባዊ ዝቅተኛ አካባቢዎች ደግሞ በአብዛኛው በግጦሽ ሣር ሽፋን ወይም በተለያዩ የሣር አይነቶችና፣ በተፈጥሮ ቁጥቋጦ፣ የተሸፈኑ ናቸው:: በደን ጽዋት ሀብት ምዝገባና ስትራቴጂክ ኘላኒንግ ኘሮጀክት **(Woody Biomas Inventory & Strategic Planning Project)** ጥናት መሰረት ከክልሉ አጠቃላይ የቆዳ ስፋት **11** በመቶ የሚሆነው በተለያዩ የደን ጽዋት ዓይነቶች የተሸፈነ ሲሆን በአብዛኛውም የደን ሽፋኑ ያለባቸው አካባቢዎች ቤንች ማጂ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ዳውሮ፣ ጋሞጐፋ፣ ሲዳማ፣ ደቡብ ኦሞ ዞኖችና ኮን ፣ የምና አማሮ ልዩ ወረዳዎች ናቸው::

### ለ. የዱር ንስሳት ሀብት

ክልሉ ካለው የተለያየ የአየር ንብረትና የመሬት አቀማመጥ መነሻነት ለተለያዩ የተፈጥሮ ጽዋት መገኘትና ለበርካ የዱር ንስሳት መኖሪያነት አመቺ ንዲሆን አድርጎ ል:: ከዚሁ አንፃር ዋነኛ ከሆኑት የዱር ንስሳት መካከል ዝሆን፣ አንበሣ፣ ቀጭኔ፣ ነብር፣ የሜዳ አህያ፣ ቆርኬ፣ አውራሪስ፣ ጉሽ (Lesser kudo, water buck, water houe) የሚጠቀሱ ናቸው:: በመሆኑም ክልሉ ከፍተኛ የሆነ የቱሪስት መስህብ (Tourism pole) ንዲሆን ምቹ ሁኔ የተፈጠረ ሲሆን ከዚሁም በተጨማሪ በክልሉ ውስጥ አምስት ፓርኮች ሁለት የዱር ንስሳት መጠጊያና አሥራ ስድስት የቁጥጥር አደን ቀበሌዎችና አንድ የአዞ ርባ ጣቢያ ይገኛሉ::

## ሐ. የውሃ ሀብት

ክልሉ ለተለያየ አገልግሎት ሊውል የሚችል ከፍተኛ የሆነ የውሃ ሀብት ያለው ሲሆን ለኤሌክትሪክ ሀይል ፍላጐት፣ ለዓሣ ሀብት፣ ለመስኖ ልማትና ለሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶች ሊውሉ የሚችሉ በርካታ ወንዞች በስፋት ይገኛሉ፡፡ ያሉትም ወንዞች ቋሚና ወቅ ዊ ባህሪይ ያላቸው ሲሆን የተለያዩ ርዝመት ያላቸውና የተለያየ ዓይነት አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ናቸው፡፡ ከ ነዚህም መካከል ኦሞ ጊቤ፣ ጉጀብ፣ አኮቦ፣ ሰገን፣ ብላቴ፣ ወይጦ በምሳሌነት የሚጠቀሱ ሲሆኑ የተለያዩ ገባር ወንዞችና ጅረቶች ንዲሁም በቱሪስት መስህብነት የሚ ወቁ ፏፏቴዎችና ፍልውሀዎች በተንዳኝነት ይገኛሉ፡፡ ሀገሪቱ ካላትና በአብዛኛው ጥልቀት ካላቸው ሀይቆች መካከል አብዛኛዎቹ በክልሉ የስምጥ ሸለቆ ተፋሰስ ውስጥ የሚገኙ ናቸው፡፡ ነዚህም የአዋሣ፣ የአባያ፣ የጫሞ፣ የጨው ባህርና የሩዶልፍ ሀይቆች ሲሆኑ ለአሣ ርባ አመቺ ከመሆናቸውም በተጨማሪ በቱሪስት መስህብነ ቸው የሚ ወቁ ናቸው፡፡

## መ. የከርሰ ምድርና የማዕድን ሀብት

ክልሉ በከርሰ ምድራዊ /ጂኦሎጂ/ ጥናት መሰረት በሶስት ዋና ዋና ከርሰ ምድራዊ ይዘት የተከፈለ ሆኖ ይገኛል፡፡ ይህም ፐሪካምብሪያን ወይም የመሰረ ዊ አለት ይዘት፣ የሲኖዞይክ ሳተ ገሞራዊ አለት ይዘትና ያልተለያዩ የቅርብ ጊዜ አለቶች ስብርባሪ ደለል (Quaternary sediments) በመባል ተከፋፍሏል፡፡ በአገር አቀፍ ደረጃ በተዘጋጀው የጂኦሎጂ ካር መሰረት በክልሉ በአብዛኛው ተሰራጭቶ የሚገኘው የማዕድን ዓይነት በ ሳተ ጐሞራዊና ሳተ ገሞራዊ ወለድ የአለት ስብርባሪ ደለል ያለበት ንደሆነ ይጠቁማል፡፡ ምንም ንኳ ዝርዝር ጥናት ባይኖርም በክልሉ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜ ያላቸው ውድ ማዕድናት ንደሚኖሩ ይ ወቃል፡፡ ለምሣሌም ወርቅና ከወርቅ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ማዕድናት በአብዛኛው ተሰራጭተው የሚገኙ ሲሆን ለኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ ሊያገለግሉ የሚችሉ የማዕድን ውሃ ሀብት፣ የክሌይ ማዕድን ሀብት ንዲሁም ለግንባ አገልግሎት ሊውሉ የሚችሉ ንደ አግኒምብራይት ሪሆላይት፣ ስኮሪያና የኖራ ድንጋይ /ላይምስቶን/ የመሳሰሉት በስፋት በጌዲኦ፣ በቤንች ማጂ፣ በሲዳማ፣ በጋሞጐፋ ዞኖች ንደሚገኙ የቀረቡ ሪፖርቶች ያመለክ ሉ፡፡

## ሠ. የአፈር ሀብት

ክልሉ ካለው የተለያዩ የሥነ ምህዳር፣ የአየር ንብረት ቀጠና ንዲሁም የከርሰ ምድር ይዘት ጋር በተገናኘ የተለያዩ የአፈር ዓይነቶች በስብጥር ተሰራጭተው ይገኛሉ፡፡ ነዚህም የአፈር ዓይነቶች ለተለያዩ የሰብል፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ጥቅም የዋሉ የሚገኙ ናቸው፡፡ በክልሉ የደን ድርጊት መርሀ ግብር ና በክልሉ አትላስ መረጃ መሰረት 13 ዋናና 22 ንዑሳን የአፈር ዓይነቶች በክልሉ ንዳሉ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከ13 ዋና ዋና የአፈር ዓይነቶችም መካከል ኒቶሶል፣ ካምቢሶል፣ ሉቪሰል፣ ቨርቲሰል፣ ሉቶሶል፣ አክሪሶል፣ ግላይሶል፣

ፍሉቪዮሶል፣ ሪጎሶል፣ ኢንዱሶል፣ ፋይዘም፣ ስሎንቻክና ሂስቶሶል ተጠቃሽ ሲሆኑ ነዚህም የየራሳቸው የምር ማነት ደረጃና ጠቀሜ አላቸው:: ክልሉም በአብዛኛው በኒቶሶልና በአክሪሶል የአፈር ዓይነት የተሸፈነ ሆኖ ይገኛል::

### 1.5. የሕዝብ ስርጭት

የማዕከላዊ ስ ትስቲክስ ኤጀንሲ መረጃን መነሻ በማድረግ የክልሉ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ባደረገው ትንበያ ላይ ንደተገለጸው በ1999 ዓ.ም የክልሉ አጠቃላይ ሕዝብ ብዛት 15.3 ሚሊዮን ንደሆነ ይገመ ል:: ከአጠቃላይ ሕዝቡም 92 በመቶ በገጠር የሚኖር ሲሆን 8 በመቶ የከተማ ነዋሪ መሆኑ፣ ጥግግትንም በአንድ ካሬ ኪ.ሜ በዞኖች ከ76 ስከ 591 ሲሆን በወረዳዎች ደግሞ ስከ 1080 ነዋሪ ሊኖር ንደሚችልና በክልል ደረጃም ጥግግቱ በአንድ ካሬ ኪ.ሜ 130 ሰዎች ይኖራሉ ተብሎ ንደሚገመት ከቢሮው የተገኘው መረጃ ያመለክ ል::

### 1.6. ክልሉ የሚገኝበት ሁኔ በዋነኛ የልማት መስኮች

## ሀ. የግብርናና ገጠር ልማት ዘርፍ

ይህ ዘርፍ የክልሉን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማፋጠን ወሳኝ ሚና ያለው ሲሆን የገጠር ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂን መሠረት በማድረግ በተደረጉት ንቅስቃሴዎች የምግብ ዋስትናን በዘላቂነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ሥራዎች የተከናወኑ ከመሆናቸውም ባሻገር ለአገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ገበያ ጥራ ቸውን የጠበቁ የግብርና ምርቶች ንዲመረቱና የአርሶ አደሩ ኑሮ ንዲሻሻል በማድረግ ባለፉት ዓመ ት አበረ ች ውጤቶች የተመዘገቡ ሲሆን፤ በመሬት አጠቃቀምና በሌሎችም ያለው ሁኔ ንደሚከተለው ነው::

### የመሬት አጠቃቀም

ክልሉ ካለው የመሬት ሀብት ውስጥ 25% የ ረሰ፣ 22% ሊ ረስ የሚችል፣ 12% ግጦሽ፣ 19% ደን ቁጥቋጦና ጥሻ ንዲሁም 22% ለተለያዩ ግልጋሎቶች የሚውል ነው:: የገጠር ርሻ መሬትን ከያዙት አርሶ አደሮች መካከል 76.2% በጥምር ርሻና ርባ ሥራ የሚተዳደሩ ሲሆን 14.7% ደግሞ በሰብል ልማት ሥራ ብቻ ሲተዳደሩ የተቀሩት 9.1% ደግሞ በ ርባ ው ዘርፍ ላይ የተሰማሩ አርብቶ አደሮች ናቸው::

## የሚመረቱ ዋና ዋና ሰብሎች

በክልሉ የሚመረቱ የሰብል ዓይነቶች ንደየ አግሮ ኢኮሎጂውና የአየር ንብረት ቀጠናዎቹ ይለያያሉ:: በመሆኑም በክልሉ ጐላ ብለው የሚ ዩት አግሮ ኢኮሎጂዎችና የአየር ንብረቶች በአራት የተከፈሉ ናቸው:: ነዚህም:-

1) **በቂ ርጥበት ባለባቸው ምዕራባዊ የክልሉ ዞኖች (ካፋ፣ሸካ፣ቤንች ማጂ)** ውስጥ በዋነኝነት ለገበያ በስፋት የሚቀርቡ ምርቶች ቡና፣ ቅመማ ቅመምና ፍራፍሬ ፣ ማርና ሰም ሲሆኑ ለምግብና ለአካባቢ ገበያ የሚቀርቡት ንሰት፣ የአገዳና የብርዕ ንዲሁም የስራስር ሰብሎችም በተጓዳኝ ይመረ ሉ::
2) **የ ርጥበት ችግር በሌለባቸው የማዕከላዊ ዞኖች** ውስጥ ለገበያም ሆነ ለቤት ውስጥ ፍጆ የሚመረቱት ዋና ዋና ሰብሎች:- የብርዕ ሰብሎች ስንዴ፣ ገብስና ጤፍ፣ ከአገዳና ከጥራጥሬ ሰብሎች በቆሎ፣ ማሽላ፣ ባቄላና አተር ሲሆኑ ከቋሚ ሰብሎች ደግሞ ቡና ና ንሰት በስፋት የሚመረቱበት ቦ ነው::
3) **የ ርጥበት ችግር የሌለባቸው ደቡባዊ ምሥራቅ የክልሉ አካባቢዎች** በቅደም ተከተል ለገበያና ለቤት ውስጥ ፍጆ የሚውሉ ሰብሎችን በስፋት ያመር ሉ:: በዋነኛነትም ቡና፣ ንሰት፣ አትክልትና ፍራፍሬ፣ በቆሎ፣ ጤፍ፣ ስንዴ፣ ድንችና ሌሎች የስራስር ተክሎች በስፋት ይመረ ሉ::
4) **ደረቅና የ ርጥበት ችግር ባሉባቸው የክልሉ ማዕከላዊና ደቡባዊ አካባቢዎች** የሚበቅሉት በርበሬ፣ ማሽላ፣ በቆሎ፣ ጥጥና ቦሎቄ ሲሆኑ ለገበያ ጐላ ብለው የሚወጡ ሰብሎች ግን በአብዛኛው በርበሬ፣ በቆሎና ቦሎቄ ናቸው፣

## የ ንስሳት ሀብት

ከኢንዱስትሪ ፖቴንሺያል ጥናት በተገኘው መረጃ መሰረት በክልላችን የተለያዩ የ ንስሳት ዓይነቶች ይገኛሉ:: ከነዚህም ውስጥ:- የቀንድ ከብት 9.3 ሚሊዮን፣ በግ 3.2 ሚሊዮን፣ ፍየል 2.7 ሚሊዮን፣ የጋማ ከብት 0.8 ሚሊዮን፣ ዶሮዎች 7.3 ሚሊዮን ናቸው:: የ ንስሳቱ ሀብት አገሪቱ ካላት ድርሻ አኳያ ሲ ይ የቀንድ ከብት 30.9 በመቶ፣ በግ 12.8 በመቶ፣ ፍየል 15.8 በመቶ፣ የጋማ ከብት 11.2 በመቶና ዶሮ 14.6 በመቶ ይሆናል:: ስለሆነም ክልሉ ባሉት የ ንስሳት ሀብት /በዓይነትና በመጠን/ ለጠቅላላው ሀገሪቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል::

## ለገበያ የቀረቡ ያሉ ምርቶችን በተመለከተ

ከክልሉ የተለያዩ ምርቶች ለዓለም ገበያ የቀረቡ ያሉ ሲሆን በዋነኝነት ሊጠቀሱ የሚችሉት፣ ከሰብል ልማት የቡና ምርት ሲሆን አገሪቱ ለአለም ገበያ ከም ቀርበው ምርት ከ40-45% ይሸፍናል:: ከቡና ከአቅርቦት አንፃር ሲታይ በየጊዜው ከፍተኛ መሻሻል የታየ ሲሆን በ1992 ዓ.ም ቀርቦ ከነበረው 71,246 ቶን (712,460 ኩ/ል) በ1997 ዓ.ም 100,302 ቶን (1,003,020 ኩ/ል) ዕድገት አሳይቷል:: በሌላ በኩል ሀገሪቱ ወደ ውጪ ከምትልካቸው ምርቶች የእንስሳት ተዋጽኦ ሰፊ ድርሻ ያለው ሲሆን በ1994 ዓ.ም መረጃ መሠረት ከክልሉ በጥቅሉ 1,511,015 ቆዳና ሌጦ ለገበያ የቀረበ ሲሆን በ1997 ዓ.ም ወደ 1,616,796 አድጓል::

## ለ. ጤና

የልማት ጥያቄ ሲነሣ በአብዛኛው የማሕበራዊና የኢኮኖሚያዊ መሰረተ ልማትን አሻሽሎ ከማቅረብና ሕብረተሰቡ በሰፊው ንዲጠቀም / ንዲገለገል/ ከማድረግ ጋር የተያያዘ ንደሆነ የሚ ወቅ ነው:: ከዚሁ አንጻር ለጤና ዘርፍ የሚሰጠው ትኩረት ከሁሉም በላይ ቀዳሚውን ስፍራ ይዞ ይገኛል:: ምክንያቱም ጤንነቱ ያልተጠበቀ ሕዝብ በልማ ዊ ንቅስቃሴ ሊሳተፍ የሚችል ባለመሆኑ ነው:: በአንድ ሕብረተሰብ ውስጥ የጤና አገልግሎት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ መገኘት ወይም አለመገኘት ና ድህነት ቀጥተኛ የሆነ ቁርኝት ያላቸው ክስተቶች ናቸው::

በክልሉ በጤናው አገልግሎት ዘርፍ የሚደረገው ንቅስቃሴ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ከማሳካት አኳያ ቀዳሚ ትኩረት የተሰጠው ሲሆን በዚህም አካሄድ አዎን ዊ ለውጥ ንደሚገኝ ይጠበቃል:: ይሁንና በአሁኑ ጊዜ በክልሉ ያለው የጤና አገልግሎት ተቋማት ስርጭት በሚታይበት ጊዜ በቁጥር 19 ሆስፒ ሎች፣ 161 ጤና ጣቢያዎች፣ 194 ዳጊ ጤና ጣቢያዎች፣ 1593 ጤና ኬላዎችና 4 የሚሆኑ የላቦራቶሪ ማዕከሎች በተለያዩ አካባቢዎች ተሰራጭተው የሚገኙ ሲሆን የክልሉ የጤና አገልግሎት ሽፋንም 73.5% ነው::

ከጤና አገልግሎት ተቋማትና ከጤና ባለሙያዎች ብዛት አንጻር በክልሉ ያለው የአገልግሎት ሽፋን በሚ ይበት ጊዜ የሆስፒ ል አገልግሎት ሽፋን 22%፣ የጤና ጣቢያ አገልግሎት ሽፋን 28% ና የጤና ኬላ የአገልግሎት ሽፋን 45% የደረሰ ሲሆን የጤና ባለሙያዎችና የሕዝብ ብዛት ጥምር ን በተመለከተ አንድ ሀኪም ለ150,934፣ አንድ የጤና መኮንን ለ125,997፣ አንድ ፋርማሲስት ለ1,811,213፣ አንድ ነርስ ለ6278፣ አንድ ላብራቶሪ ቴክኒሽያን ለ144,897፣ አንድ ፋርማሲ ቴክኒሽያን ለ80,054፣ ና አንድ ሳኒተሪያን ለ2,414,951 ሕዝብ ነው:: በአጠቃላይ የጤና ባለሙያዎችና የሕዝብ ብዛት ጥምር ን በተመለከተ አንድ የጤና ባለሙያ ለ3,351 ሕዝብ ነው::

በሌላ በኩል በአሁኑ ጊዜ በዓለም ትልቅ ሥጋት ሆኖ የሚገኘውና በተለይም በሀገራችን ካለው ዝቅተኛ የማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት አንጻር ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳደረ የሚገኘው የኤች.አይ ቪ /ኤድስ ወረርሽኝ ነው፡፡ ይህንን ወረርሽኝ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የክልሉ መንግስት ትኩረት ሰጥቶት በየመሥሪያ ቤቶች ደረጃ ሥራውን የሚሰራ መዋቅር ንዲካተት በማድረግ የተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡

## ሐ. ትምህርት

በአንድ ሕብረተሰብ ውስጥ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማምጣት ትኩረት ሊሰጣቸው ከሚገባቸው የማሕበራዊ አገልግሎቶች አንዱ የትምህርት ሥራ ነው፡፡ የትምህርት አገልግሎት በሕብረተሰብ የኑሮ ሂደት ውስጥ በሚደረጉ ንቅስቃሴዎች ሁሉ ተግባራዊ የሚሆንና የዕድገት ለውጥ ማምጣት የሚችል በመሆኑ የአገልግሎቱ አድማስ ሰፊ ነው፡፡ ስለሆነም ከትምህርት አገልግሎት ጋር በተያያዘ በአንድ ሀገር፣ በአንድ ክልል ወይም በአንድ ሕብረተሰብ ውስጥ ያለው ሁኔ የሚ የው ከስርጭት/ ከብዛት/፣ ከትምህርት ደረጃዎች ስብጥርና ከትምህርት ጥራት አኳያ ተነጻጽሮ ሊሆን ይገባል፡፡

በክልሉ የትምህርት አገልግሎት ስርጭትን በተመለከተ በተለያዩ ደረጃ የሚገኙ ቁጥራቸው ከ3834 በላይ የሚሆኑ የመንግሥትና የግል የትምህርት ተቋማት በ1998 ዓ.ም የትምህርት ዘመን የትምህርት አገልግሎት በመስጠት ላይ ንደሚገኙ ተመልክቷል፡፡ ከ ነዚህ የትምህርት ተቋማት ውስጥ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች ቁጥር /1-8/ 3,338፣ የ2ኛ ደረጃ /9-10/ ት/ቤቶች 127፣ የመሰናዶ /11-12/ ት/ቤቶች 35፣ የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት 20፣ የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ 4 ሲሆን በግል ሴክተሩም 237 አጸደ ሕጻናት፣ 21 የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማትና 9 የጤና ሳይንስ ኮሌጆች የትምህርት አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡

በየትምህርት ደረጃው የዕድሜ ክልላቸው ለሚፈቅድላቸው ዜጐች የትምህርት አገልግሎት ከማዳረስ አንጻር በክልሉ በ1998 ዓ.ም የተመዘገበው የትምህርት ሽፋን ገጽ ንደሚያመለክተው ጥቅል ተሳትፎ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት /ከ1-8/ 89.7% ሲሆን በ2ኛ ደረጃ /9-12/ ት/ቤት ደግሞ 26.7% ነው፡፡ ይህም በ1997 ዓ.ም ከነበረው የትምህርት ሽፋን ጋር ሲነጻጸር ጥቅል የትምህርት ሽፋን በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት /1-8/ በ4.6% በ2ኛ ደረጃ /9-10/ ት/ቤት ደግሞ በ5.1% ድገት ያሳየ ቢሆንም በተለይ በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ሽፋን ክልሉ የሚገኝበት ደረጃ ዝቅተኛ ንደሆነ ያሳያል፡፡

በተመሣሣይ መልኩ የሴት ተማሪዎች ተሳትፎም በአሁኑ ጊዜ በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት /ከ1-8/ 77.8%፣ በ2ኛ ደረጃ ት/ቤት /9-12/ 16.9% የደረሰ ሲሆን በ1997 ዓ.ም ከነበረው ጥቅል የሴቶች

የትምህርት ተሳትፎ ጋር ሲነጻጸር ንደ ቅደም ተከተላቸው በ6% ና በ6.6% መሻሻል አሳይቷል፡፡

ከዚህ አንጻር በክልሉ ያለው ሁኔ በሚ ይበት ጊዜ በ1997 ዓ.ም ከሚያስተምሩ ጠቅላላ መምህራን መካከል በአንደኛ ደረጃ በ1ኛ ሳይክል /1-4/ ት/ቤቶች 96.1%፣ በ2ኛ ሳይክል /5-8/ ት/ቤቶች 66.9% ንዲሁም በሁለተኛ ደረጃ /9-12/ ትምህርት ቤቶች 34.2% የሚሆኑት የሰለጠኑ ሲሆኑ የተማሪ መምህራን ጥምርት ደግሞ በመጀመሪያ ደረጃ 1ኛ ሳይክል /1-4/፣ 2ኛ ሳይክል /5-8/ ና በ2ኛ ደረጃ /9-12/ ትምህርት ቤቶች ንደ ቅደም ተከተላቸው 1:71 ፣ 1: 59 ና 1: 54 ነው፡፡ ንዲሁም የተማሪው ቁጥር ከመማሪያ ክፍሎች ብዛት ጋር ሲነፃፀር በመጀመሪያ ደረጃ በ1ኛ ሳይክል የመማሪያ ክፍል ተማሪ ጥምርታ 1:74፣ በሁለተኛ ሳይክል 1:75 ና በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች 1:90 ሲሆን በሀገር አቀፍ በትምህርት ሚ/ር የተቀመጠው ስ ንዳርድ ግን በመጀመሪያ ደረጃ /1-8/ ት/ቤቶች 1 የመማሪያ ክፍል ለ50 ተማሪዎች በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች /9-12/ ደግሞ 1 የመማሪያ ክፍል ለ40 ተማሪዎች ነው፡፡

## መ. መገናኛ አው ሮች ዝርጋታ፣ የመጠጥ ውሃና የሀይል አጠቃቀም

የመገናኛ አው ሮች ዝርጋ ና የኤሌክትሪክ ሀይል አጠቃቀም ሽፋን የአንድን ማሕበረሰብ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ንቅስቃሴ በማፋጠን ቀጣይነት ያለው የዕድገት አቅጣጫ ንዲኖረው ለማድረግ የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ንደሆነ የሚ ወቅ ነው፡፡ በዚህ መነሻ ክልሉ ለልማት መሰረት በሆኑት በ ነዚህ አገልግሎቶች ረገድ የሚገኝበት ደረጃ ንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### i. መንገድና ትራንስፖርት

በአሁኑ ጊዜ በክልሉ ያለው የመንገድ አገልግሎት ሽፋን ቀደም ሲል ከነበረው ሽፋን የተሻሻለ ቢሆንም ከአገልግሎቱ ወሳኝነትና ካለው የአገልግሎት ክፍተት አንጻር ሲታይ ገና በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው፡፡ መረጃዎች ንደሚያመለክቱት በ1996 ዓ.ም መጨረሻ ላይ በክልሉ የተዘረጋው መንገድ 8,250 ኪ.ሜትር ሲሆን ከዚህ ውስጥ 421 ኪ.ሜ አስፓልትና 4,778 ኪ.ሜ ጠጠር መንገድ ነው፡፡ የቀረው ርዝመቱ 3,052 ኪ.ሜ የሚሆነው መንገድ ግን ጥርጊያ መንገድና ለበጋ ብቻ የሚያገለግል ነው፡፡ በሌላ በኩል ክረምት ከበጋ የሚያገለግል መንገድ በጠቅላላ ካለው መንገድ ውስጥ 5,199 ኪ.ማ /63%/ ብቻ የሚሸፍን ነው፡፡ በ1997 ዓ.ም የነበረው የመንገድ ጥግግትም በ1,000 ኪ.ሜ. ውስጥ 74 ኪ.ሜትር ንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መንገዶች የሚገኙበትን ደረጃ በተመለከተ ካሉት መንገዶች ውስጥ 57 በመቶ ያህል ብቻ በጥሩና በደህና ሁኔ ላይ የሚገኙ ንደሆነና የቀረው 43 በመቶ የሚሆነው መንገድ ደግሞ በመጥፎ ሁኔ ላይ ንደሚገኙ የመንገድ ኔትወርክ ጥናት ያመለክ ል፡፡ ንደዚሁም በክልሉ ካሉት

134 ወረዳዎች 12ቱ ወረዳዎች ክረምት ከበጋ የሚያገለግልና ከሌሎች አካባቢዎች ጋር የሚያገናኛቸው መንገድ የሌላቸው ናቸው::

በሌላ በኩል በትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፍ በክልሉ የየብስና የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ አው ሮች ያሉት ሲሆን የየብስ ትራንስፖርት አገልግሎትን በተመለከተ ከላይ በዝርዝር በተቀመጡት መንገዶች፣ የአየር ትራንስፖርትን በተመለከተ ደግሞ በአርባ ምንጭ ከተማ በተቋቋመ 1 አለም አቀፍ የአውሮኘላን ማረፊያ፣ በ3 ከተሞች ማለትም፣ በጂንካ፣ በቴፒና በሚዛን አማን ከተሞች በሚገኙ መለስተኛ የአውሮኘላን ማረፊያ ሜዳዎች አማካኝነት አገልግሎቱ በመሰጠት ላይ ይገኛል::

## ii. ቴሌኮሙኒኬሽንና ፖስ አገልግሎት

በቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ዘርፍ ባለፉት ዓመ ት የ የው ዕድገት በሀገር አቀፍ ደረጃ የጐላ የመሆኑን ያህል በክልሉም በተመሣሣይ መልኩ የቴክኖሎጂ ስርጭት ዕድገት ተጨባጭ ለውጦች አስመዝግቧል:: በክልሉ 26 ከተሞች የአውቶማቲክ ስልክ ተጠቃሚ ሲሆኑ 53 ከተሞች ደግሞ የከፊል አውቶማቲክ ስልክ አገልግሎት ተጠቃሚ ናቸው:: በአብዘኛዎቹም ከተሞች የኢንተርኔት አገልግሎትም የተስፋፋ ይገኛል::

በፖስ አገልግሎት ረገድም በክልሉ በ1997 ዓ.ም 84 የፖስ አገልግሎት ማዕከላት የሚገኙ ሲሆን ከ ነዚህ ውስጥ 18 ቋሚ፣ 21 መደበኛ አገልግሎት፣ 38 ወኪሎችና 7 የ ግረኛ ፖስተኛ አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው::

## iii. የመጠጥ ውሀ አቅርቦት

በንጹህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ዘርፍ በመንግሥት ከሚገነቡት የውሃ ተቋማት በተጨማሪ ሕብረተሰቡንና መንግሥ ዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በማሳተፍ ከ10 ዓመት በፊት ከነበረበት 20% የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋን በ1997 የበጀት ዓመት ወደ 48% አድጓል:: የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋን በከተማና በገጠር ተለይቶ በሚ ይበት ጊዜ ደግሞ በከተማ 60% ሲሆን በገጠሩ ክፍል 45% መሆኑን መረጃዎች ያረጋግጣሉ:: ከመጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋን ጋር በተያያዘ ያለውን ሁኔ ለማሻሻል ስከ 1997 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ ምንጮች 2941፣ የ ጅ ውሃ ጉድጓዶች 1304፣ መለስተኛ የውሃ ጉድጓዶች 1678፣ ጥልቅ የውሃ ጉድጓዶች 421 የተገነቡ መሆናቸው ተመልክቷል::

## iv. ኢነርጂ አገልግሎት

በሕብረተሰቡ ውስጥ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ንቅስቃሴን ለማገዝ ወሳኝ ድርሻ ካላቸው ቅድመ ሁኔ ዎች ወይም አገልግሎቶች መካከል የኢነርጂ / ይል/ አቅርቦት መመቻቸት ዋነው ነው፡፡ ይል በተለያየ ዓይነት ቴክኖሎጂ የሚመረት ንደመሆኑ ሁሉ አጠቃቀሙ ንደዚሁ ለተለያዩ አገልግሎቶች ነው፡፡

በዚሁ መሰረት ከኤሌክትሪክ፣ ከባዮ ጋዝና ከማገዶ የሚመነጩ ሀይሎችን የክልሉ ሕብረተሰብ ለተለያዩ ተግባራት የተጠቀመባቸው የሚገኝ ሲሆን የአጠቃቀሙ ሁኔ ሲ ይ 87 ከተሞች የሀይድሮ ኤሌክትሪክ ሀይል ንዲሁም 10 ከተሞች በጀኔረተር በጠቅላላው 97 ከተሞች የኤሌክትሪክ ሀይል አገልገሎት ንደሚያገኙና በ4 ዞኖች ደግሞ የአማራጭ ሀይልን ከማስተዋወቅ አኳያ የባዮ ጋዝ ማመንጫዎች ተገንብተው አገልግሎት በመስጠት ላይ ንደሚገኙ መረጃዎች ያመለክ ሉ፡፡

## ሠ. ቱሪዝም

ክልሉ የተለያየ የአየር ንብረትና የመሬት አቀማመጥ ያለው በመሆኑ አካባቢው ለተለያዩ ዓይነት ዕፅዋትና ንስሳት መገኛ ምቹ ንዲሆን አስችሎ ል፡፡ ንደዚሁም በክልሉ የሚማርኩ ተራሮች፣ ሸለቆዎች፣ ወንዞች፣ ሀይቆችና ደኖች የሚገኙ ከመሆኑም ባሻገር ተራሮቹ የብዙ ወንዞችና ምንጮች መገኛ ናቸው፡፡ እንዲሁም ለበርካ ዕፅዋትና ንስሳት ምቹ የመኖሪያ ክልል በመሆናቸው ይህም የቱሪዝም ኢንዱስትሪን በክልሉ ለማስፋፋት አመቺ ሁኔ ን ፈጥሯል፡፡ በተመሣሣይ መልኩ ክልሉ በተፈጥሮ ያገኛቸውና ጉብኝን የሚስቡ ሥፍራዎች ያሉት ሲሆን፣ ነዚህ ሥፍራዎች ለመዝናኛነት በጣም ምቹ ከመሆናቸውም ባሻገር በየአካባቢው የሚገኙት ፍልውሀዎች፣ ቀዝቃዛ ምንጮችና የማዕድን ውሃዎች ለልዩ ልዩ ዓይነት በሽ ዎች በፈውስነት ያገለገሉ ይገኛሉ፡፡ ከዚሁ በተጨማሪ ከሰባት በላይ የሚሆኑ ትላልቅ ወንዞችና አምስት ዋና ዋና በባህር ውስጥ ንስሳት ሀብት የተሞሉ ሀይቆች በክልሉ ይገኛሉ፡፡

የዱር ንስሳት ሀብትን በተመለከተም በክልሉ አምስት ፓርኮች ያሉ ሲሆን በነዚህም ውስጥ ዝሆን፣ አንበሣ፣ ቀጭኔና፣ የመሳሰሉት የዱር ንስሳት ይገኛሉ፡፡ በተለይም በአሥራ ስድስት የጥብቅ አደን ቀበሌዎችና የዱር ንስሳት መጠበቂያ ቦ ዎች በርካ የሆኑ የዱር ንስሳት ንደሚገኙ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በሌላ በኩል በሀገሪቱ ከሚገኙት ብሔረሰቦች አብዛኞቹ የሚገኙት በዚሁ ክልል ሲሆን ያንዳንዱ ብሔረሰብም የየራሱ የሆነ አለባበስ፣ የአኗኗር ሥርዓት፣ ባህላዊም ሆነ ሃይማኖ ዊ በአሉችና የአከባበር ሥርዓት ያለው ሲሆን ይኼው ንደ አይነተኛ የቱሪስት መስህብነት ያገለገለ ይገኛል፡፡ ሰው ሰራሽ ከሆኑትና ለቱሪስት መስህብነት ሊያገለግሉ ከሚችሉት ሪካዊ ቅርሶች መካከል ረጅም ዕድሜ ያስቆጠሩ ሃይማኖ ዊ ገዳማትና

መስጊዶች፣ ንዲሁም ዋሻዎችና የተለያዩ የስዕል ቅርጾች የተቀረጸባቸው ትክል ድንጋዮች በክልሉ የተለያዩ አካባቢዎች ይገኛሉ::

በአጠቃላይ ክልሉ ለቱሪዝም ኢንዱስትሪ መስፋፋት አመቺ ሀብቶች ያሉት ሲሆን ነዚህን ሀብቶች ከመጠቀም አንጻር ገና ብዙ የሚቀረው መሆኑን ያለው መረጃ ያመለክ ል:: በዚህ ዘርፍ ከሚመለከ ቸው መሥሪያ ቤቶች ከተገኙ መረጃዎች ለማረጋገጥ ንደተቻለው ከ1995-1997 ዓ.ም ድረስ ክልሉን የጐበኙ ቱሪስቶች ቁጥር 455,622 ሲሆን ከዚህ ውስጥ 360,322 /79%/ የሀገር ውስጥ ጐብኚዎች ንደሆኑና ቀሪው 95,096 /21%/ የውጭ ሀገር ጐብኚዎች ናቸው:: ከዘርፉ የተገኘውን ገቢ በተመለከተ በተጠቀሱት ሶስት ዓመ ት ብር 26,679,244 ንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ::

በተጨማሪ መረጃዎች ንደሚያመለክቱት በክልሉ የጐብኝዎች ቁጥር በየዓመቱ በአማካኝ 15 በመቶ ዕድገት የሚያሳይ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ለቱሪስቶች አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ዝቅተኛ፣ መካከለኛ ንዲሁም ባለኮከብ ሆቴሎች የተስፋፉ የመጡ ቢሆንም ክልሉ ካለው የቱሪዝም መስህቦችና የቱሪስት ሀብት አንጻር በዘርፉ ገና ብዙ መሰራት ይኖርበ ል::

## ረ. ንግድ

በክልሉ የንግድ ሥራዎች በጅምላ፣ በችርቻሮና በአገልግሎት መስጫ ንግድ ዘርፎች ተለይተው የሚ ወቁ ናቸው:: በዚህም መሰረት በ1997 የበጀት ዓመት መጨረሻ ላይ በክልሉ ተመዝግበው ከሚ ወቁት 7762 የንግድ ሥራዎች መካከል ብዛታቸው 1362 /17.5%/ የሚሆኑት በጅምላ ንግድ፣ 3479 /44.8%/ በችርቻሮ ንግድና 2312 /29.8%/ በአገልግሎት መስጫ ንግድ ዘርፍ ተመድበው የሚንቀሳቀሱ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ::

## ሰ. ኢንዱስትሪ

በኢንዱስትሪ ልማት በሀገሪቱም ሆነ በክልሉ ያለው ዕድገት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው:: በአጠቃላይ ኢንዱስትሪዎች ከባድና ቀላል ኢንዱስትሪ በሚል በሁለት ምድብ ተከፍለው የሚ ዩ ሲሆን ንደሀገራችን ባሉት ዳጊ ሀገሮች የሚኖሩት ኢንዱስትሪዎች በአብዛኛው በቀላል ኢንዱስትሪ የሚመደቡ ናቸው::

ከዚህ አንጻር በክልሉ ያሉትን ኢንዱስትሪዎች በተመለከተ የክልሉ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ .ኤ.አ. በ2005 ካሳተመው የክልሉ አትላስ ለማረጋገጥ ንደተቻለው በቀላል ኢንዱስትሪዎች የሚመደቡ የጨርቃ ጨርቅ፣ የቆዳ ሥራ፣ የብረ ብረት ሥራ፣ የቡና መፈልፈያ ወይም መቀሸሪያ፣ የሕትመት ሥራ፣ የሴራሚክ፣ የ ንጨት ሥራና የምግብ ማሸጊያ ወዘተ ፋብሪካዎች ሲሆን በጠቅላላው ከ518 ሚሊዮን ብር በላይ ካፒ ል ግምት ያላቸው 1948 ያህል የተለያዩ ኢንዱስትሪዎች በክልሉ ንዳሉ ተመልክቷል::

በክልሉ የሚገኙት ኢንዱስትሪዎች ከጥቂቶች ማለትም የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ከሆኑት የአዋሣ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ የአርባ ምንጭ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ አዋሳ ዱቄት ፋብሪካና የአዋሣ ሴራሚክ ፋብሪካ በስተቀር ሌሎቹ የግል ሲሆኑ ከብዛትም አንጻር ከምግብ ማቀነባበርና ማሸግ ጋር የተያያዘ ሥራ የሚያከናወኑ ኢንዱስትሪዎች ከጠቅላላ የኢንዱስትሪዎች ብዛት 63.8 ከመቶ ያህሉን የሚሸፍኑ ስለሆነ በአንደኛ ደረጃ ላይ ተመዝግበው ይገኛሉ፡፡ የቡና መፈልፈያ ኢንዱስትሪ 18.6 ከመቶ ድርሻ ያለው በመሆኑ በሁለተኝነት ደረጃ ሲገኝ የ ንጨትና የብረ  ብረት ኢንዱስትሪ ደግሞ 16.6 ከመቶ የሚሸፍን ሆኖ ይገኛል፡፡ በሌላ በኩል ለኢንዱስትሪዎቹ ከፈሰሰው ካፒ ል አንጻር ሲ ይ ለቡና መፈልፈያ ኢንዱስትሪዎች የዋለው ካፒ ል  በጠቅላላ ከተመዘገበው  ከፍተኛውን ድርሻ (86.9%) ይዞ ይገኛል፡፡

## ሸ. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፐራይዞች ማስፋፋት

በኢንዱስትሪ በበለጸጉ ሀገሮችም ሳይቀር በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፐራይዞች ውስጥ ተቀጥሮ የሚሠራው ሰው  በትልልቅና መካካለኛ ኩባንያዎች ውስጥ ተቀጥሮ ከሚሠራ ሰው በእጅጉ እንደሚበልጥ ይታወቃል፡፡ በተለይም እንደ እኛ ባሉ የኢኮኖሚ እድገታቸው ወደ ኂላ የቀሩና ካላቸው ሀብት በአንጻራዊ ሁኔታ የሰው ኃይል ከፍተኛውን ድርሻ በሚይዝ ሀገሮች የሰው ኃይልን በሰፊው ከመጠቀም አኳያ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፐራይዞች በእጅጉ ተመራጭ እንደሚሆን አጠያያቂ አይሆንም፡፡ ሆኖም ግን በክልላችንም ሆነ በሀገራችን እስካለፉት አራትና አምስት ዓመታት ድረስ ዘርፉ የህዝቡን መሰረታዊ የኢኮኖሚና ማህራዊ ችግር ሊቀርፍ የሚችል መሆኑን ባገናዘበ መልኩ ትኩረት ተሰጥቶ አልተሰራበትም ነበር፡፡

ይሁን እንጂ በዘርፉ መሰረታዊ ለውጥ በማምጣት ዘርፉን በህብረተሰብ ውስጥ ስር ሰዶ የቆየውን ድህነትና ኋላቀርነትን የምንዋጋበት ቁልፍ መሳሪያ ከማድረግ አኳያ  የጥቃቅንና አነስተኛ የልማት ኢንተርፐራይዞች ማስፋፊያ ፕሮግራም ተቀርፆ ቀደም ሲል ዘርፉ በመቶዎችና በሺዎች ብቻ እየተፈጠረ የነበረው የስራ ዕድል ባለፉት ሁለት ዓመታት ብቻ በመቶ ሺዎች  የስራ ዕድል የሚፈጠርበት፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር የሚካሄድበት፣  የፈጠራ ስራዎች የሚፈልቁበትና ለከፍተኛና መካካለኛ ኢንዱስትሪዎች  አስተማማኝና መሰረት የሚጣልበት ለማድረግ ተችሏል፡፡

በዘርፉ እየተመዘገበ ያውን አበረታች እንቅስቃሴ ዘላቂ በማድረግ ድህነትን በመቅረፍ በጥቃቅንና አነስተኛ  ኢንተርፕራይዞችና በዘርፉ በተሰማሩ ትላልቅና መካከለኛ ኩባንያዎች መካከል ጠንካራ የኢኮኖሚ ትስስር፣ የሰብ ኮንትራክት ትስስር እንዲኖር ማድረግ የአነስተኛ ጥቃቅን ኩባንያዎችን ችግሮች በመፍታት ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡

በአጠቃላይ የኢንዱስትሪ ልማት ስታራቴጂን ከማሳካት አንጻር የአነስተኛ ጥቃቅን ኩባንያዎች በአይነትና በጥራት ማበብ እጅግ ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን በመገንዘብ ባለፉት ዓመታት በክልሉ በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡

## 2. የግሉ ኢንቨስትመንት መነሻ ሁኔታ፣ አደረጃጀትና ያለው የማስፈጸም አቅም ደረጃ፣

### 2.1. የግሉ ኢንቨስትመንት መነሻ ሁኔታ

በሀገሪቱ የሥርዓት ለውጥ በ1983 ዓ.ም ከመደረጉ በፊት ሀገሪቱን ያስተዳድር የነበረው መንግስት ሶሺሊስታዊ የእዝ ኢኮኖሚ መርህን ይከተል ስለነበር በማንኛውም የሥራ መስክ የተሰማሩ የግል ባለሀብቶች የካፒታል ገደብ ተጥሎባቸው ጥብቅ ቁጥጥር ይደረግባቸው ስለነበረ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ የተጀመረው ሀገሪቱ የነፃ ኢኮኖሚ ሥርዓት መከተል ከጀመረችበት የሽግግር ወቅት አንስቶ በመሆኑ የግል ኢንቨስትመንት በሀገራችንም ሆነ በክልላችን ደረጃ የተጀመረው ከባድ ነው ማለት ይቻላል፡፡

መንግስት የነፃ ገበያ ሥርዓትን በመከተል የገንዘብ ግሽበትን በመቋቋምና በማረጋጋት፣ ንግድና የውጭ ምንዛሬን ሊብራላይዝ በማድረግ በአጠቃላይ የማክሮ-ኢኮኖሚ ሪፎርም በማካሄድ የሀገር ውስጥንም ሆነ የውጭ ባለሀብቶችን ለመሳብ ምቹ የኢንቨስትመንት ሁኔታን ከመፍጠር አንጻር በሀገሪቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በ1984 ዓ.ም የፌዴራል ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን እና ቀጥሎ ክልላዊ የኢንቨስትመንት መ/ቤቶች እንዲቋቋሙ አድርጓል፡፡

የክልሉ መንግስትም ለኢንቨስትመንት ምቹ አካባቢን በመፍጠር፣ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ባለሀብቶችን በመሳብና በኢኮኖሚው ውስጥ እንዲሳተፉ በማድረግ ረሃብን ፣ሥራ አጥነትን፣ ማህበራዊ ቀውስን ፣በአጠቃላይ ለዘመናት ተዘፍቀን ከምንገኝበት የድህነት ሽክርክሪት ውስጥ መውጣት እንደሚቻል በመገንዘቡ ኢንቨስትመንትን የሚያስፋፋ መ/ቤት በ1986 ዓ.ም አቋቁሟል፡

ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ለማበረታታት በፌዴራልም ሆነ በክልሉ መንግስት አማካይነት የኢንቨስትመንት ፖሊሲ፣የተለያዩ አዋጆችና ደንቦችን በማውጣት ያላሰለሰ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል፡፡ በ1994 ዓ.ም ደግሞ የገጠር ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ፣ የኢንዱስትሪ ልማትና የአቅም ግንባታ ስትራቴጂዎች በመዘጋጀታቸው ጥርት ያለ የዕድገት ዓላማ፣ግብና ራዕይ አስቀምጦ ፈጣን ልማት ማምጣት የሚቻልበት መሰረት ተጥሏል፡፡ በኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂው ላይ በስፋት እንደተመለከተው

#....በተለይ በኢንዱስትሪው ዘርፍ የሚካሄደው ልማት ላይ የግል ባለሀብቱ ሞተር ሆኖ ማንቀሳቀሱ በፍጹም የማይታለፍ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም የሀገራችን የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ የግሉ ባለሀብት ሚናውን እንዲጫወት ከማስቻልና ከማብቃት ውጭ ሊታሰብ የሚቻል አይሆንም፡፡ በሀገራችን የተሳካ የኢንዱስትሪ ልማት ሊሠራ የሚችለው የዚሁ ሥራ ሞተር የግል ባለሀብቱ መሆኑን የተቀበለ ስትራቴጂ በመንደፍ የግል ባለሀብቱ ይህንኑ ሚናውን እንዳይጫወት የገቱትን ነገሮች በዝርዝር በማየትና ከዚህ ተነስቶ የግል ባለሀብቱ ሚናውን እንዲጫወት ለማድረግ የሚያስችሉ አቅጣጫዎችን አስቀምጦ በመረባረብ ነው፡፡;

ስለዚህ በክልሉ እስካሁን ያለው እንቅስቃሴ እንዳለ ሆኖ ለግሉ ኢንቨስትመንት ልማት ትኩረት በመስጠት ገና በስፋት መሰራት እንዳለበት በስትራቴጂው ከተቀመጠው ሃሳብ መገንዘብ ይቻላል፡፡

## 2.2. የክልሉ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ አደረጃጀትና ያለው የማስፈጸም አቅም ደረጃ፣

ኢንቨስትመንትን ወደሚፈለገው አካባቢ ለመሳብ የሚቻለው በኢንቨስትመንት አስፈጻሚ መ/ቤቶች ብቻ በሚደረግ እንቅስቃሴ ሳይሆን ከክልል እስከ ታችኛው እርከን ድረስ ባሉ ሕግ አስፈጻሚ፣ ሕግ አውጭና ሕግ ተርጓሚ አካላት እና በህብረተሰቡ የተቀናጀ ጥረት ጭምር ነው፡፡

ነገር ግን ከላይ በተጠቀሱት አካላት ዘንድ በቂ የኢንቨስትመንት ግንዛቤ ካለመፈጠሩ የተነሳና የግሉ ሴክተር ልማትን በማምጣት ረገድ የሚጫወተውን ሚና ለማጎልበት እንዲቻል እስካሁን ድረስ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጠት የሚያስችል አደረጃጀትና መዋቅር መፍጠር በከፊል እየተሠራበት ያለ ቢሆንም በዚህ ፕሮግራም እንደታሰበው የተሟላ ባለመሆኑ የሚፈለገውን ያህል ባለሀብቶችን ወደ ክልሉ መሳብ ካለመቻሉም በላይ በልማት ላይ የተሰማሩትም ቢሆን የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በአንድ ማዕከል አገልግሎት አቅርቦት በቅልጥፍና መፍታት የሚቻልበት ደረጃ ላይ አልተደረሰም፡፡

ለግሉ ኢንቨስትመንት ልማት መስፋፋት አንዱና ዋነኛው ግብዓት የገጠርና የከተማ መሬት በማዘጋጀት በቀለጠፈ ሁኔታ ለባለሀብቱ መስጠት ሲቻል ነው፡፡በክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ የመሬት መስጠቱ ሂደት እጅግ ከፍተኛ ውጣ ውረድ ያለበት ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር በየጊዜው የሚደረገው የመዋቅር መለዋወጥና የኃላፊዎች መቀያየርም ቢሆን የራሱ አሉታዊ አስተዋፅኦ ነበረው፡፡

ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአሁኑ ወቅት ከክልል ጀምሮ ያለው የኢንቨስትመንት መዋቅር ሁሉንም አገልግሎቶች በአንድ ማዕከል አገልግሎት አቅርቦት መርህ መሠረት ባለሀብቶችን ማስተናገድ የሚያስችለው አደረጃጀትና ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ፣ሥልጣንና ኃላፊነት በአጥጋቢ ደረጃ የሌለው ከመሆኑም በላይ አሁን ያሉት ባለሙያዎች አቅምም ቢሆን ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት በሚፈለገው ሁኔታ፣ ለማጠናከርና ተገቢ ክትትልና ድጋፍ

መስጠት በሚያስችል ብቃት ደረጃ ላይ ያለ ነው ማለት የማያስደፍር ከመሆኑም ባሻገር ጠንካራ ባለሙያዎች በየጊዜው መ/ቤቱን ሲለቁ ይስተዋላል፡፡

ስለዚህ ጠንካራ መዋቅራዊ አደረጃጀት በመፍጠር ይህንን ውሱን የማስፈጸም አቅምን ደረጃ በደረጃ በተለያዩ ሥልጠናዎች በመታገዝ ማጎልበትና ማሻሻል ያስፈልጋል፡፡

## 3. የግሉ ኢንቨስትመንት ንቅስቃሴ ሁኔ

ይህ ክፍል ‹‹የግሉ ኢንቨስትመንት ንቅስቃሴ በክልላችን ደረጃ ምን ይመስላል?›› ለሚለው ጥያቄ ምላሽ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

### በክልሉ የኢንቨስትመንት አፈጻጸም ሁኔታ

የደ/ብ/ብ/ህ/ክልል በአይነትም ሆነ በመጠን ለበርካታ ኢኮኖሚያዊ ልማቶች ሊውሉ የሚችሉ መጠነ ሰፊ የተፈጥሮ ሀብቶች የታደለ መሆኑና በኢንቨስመንት አስተዳደሩም ረገድ የሀገሪቱንና የክልሉን ነባራዊ ሁኔታዎች መሠረት በማድረግ በተወሰዱ የማሻሻያ እርምጃዎችና በተፈጠሩ ምቹ ሁኔታዎች የተሣቡ ልማታዊ ባለሀብቶች በተለያዩ የኢንቨስትመንት መስኮች በመሰማራት ተጠቃሚ ከመሆናቸው ባሻገር ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ልማትን ለማፋጠን እየተደረገ ባለው ጥረት ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛሉ፡፡

የክልሉ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ከተቋቋመበት ከየካቲት 1985 ዓ.ም ጀምሮ እስከ እስከ ሰኔ 30 ቀን 1999 ዓ.ም. ድረስ ባለው 3125 ባለሀብቶች በክልሉ በተለያዩ የኢንቨስትመንት ልማት መስኮች ለመሠማሩት ፈቃድ የተሰጣቸው ሲሆን የተሰማሩበትን ዘርፍ፣ያስመዘገቡት ካፒታል፣ የሚፈጥሩት የሥራ ዕድል፣ የእንቅስቀሴ ደረጃና የዞን ስርጭታቸውን እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

## የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰጣቸው ኘሮጀክቶች በክፍለ ኢኮኖሚ

ክልሉ ለኢንቨስትመንት ካለው አመቺነት አንጻር የተለያዩ ባለሀብቶች በልዩ ልዩ ዘርፎች ለመሰማራት ፈቃድ የወሰዱ ሲሆን መረጃዎች እንደሚያሳዩት በክልላችን ከተሰማሩ ባለሀብቶች 26.4 በመቶ ድርሻ የሚይዘው ኢንዱስትሪ ሴክተር ነው፡፡ ከኢንዱስትሪው ውስጥ አብዛኛውን ድርሻ የሚይዘው የቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ ሆኖ ግብርናና ሆቴልና ቱሪዝም በቅደም ተከተል **20.9.%, 15.36%** ድርሻ ይኖራቸዋል፡፡



## የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰጣቸው ፕሮጀክቶች በሚፈጥሩት የሥራ ዕድል

ፈቃድ የተሰጣቸው 3125 ፕሮጀክቶች በሙሉ አቅማቸው ወደ ማምረት ወይም አገልግሎት መስጠት ሲጀምሩ ለ 450,039 ቋሚና ጊዜያዊ ሠራተኞች የሥራ ዕድል ይፈጥራሉ፡፡ ከዚህም ውስጥ የግብርናው ሴክተር 42.34% የሥራ ዕድል በመፍጠር ከፍተኛውን ድርሻ ሲይዝ አግሮ ኢንዱስትሪ 16.74%፣ ኢንዱስትሪ 15.14% እና በመያዝ ይከተላሉ፡፡ ቀሪው በሪል ስቴት፣ በኮንስትራክሽን፣ ኢነርጂ፣ ሆቴልና ቱሪዝም፣ማህበራዊ አገልግሎት፣ንግድና ሌሎች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ድርሻ ይሆናል፡፡




የተፈጠረ የሥራ ዕድል ስንመለከት ከተፈጠረው የሥራ ዕድል ውስጥ የኢንዱስትሪው ዘርፍ 36% በመያዝ ሲመራ የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ 31% በመያዝ ይከተላል፡፡አግሮ ኢንዱስትሪው 15.4% ሲይዝ ቀሪው 17.42% በሌሎች ሴክተሮች የሚሸፈን ይሆናል፡፡



## የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰጣቸው ፕሮጀክቶች ባስመዘገቡት ካፒታል

ፈቃድ የተሰጣቸው ፕሮጀክቶች በአጠቃላይ ያስመዘገቡት ካፒታል 21.03 ቢሊዮን ሲሆን በግብርና ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች ያስመዘገቡት ካፒታል 4.8 ቢሊዮን ሲሆን ዝቅተኛ ያስመዘገበው የንግዱ ዘርፍ ነው፡፡




## ፈቃድ የተሰጣቸው ፕሮጀክቶች በባለቤትነት ሲታዩ

እስከ ሰኔ 30 ቀን 1999 ዓ.ም. ድረስ ባለው ጊዜ ፈቃድ ከተሰጣቸው አጠቃላይ ፕሮጀክቶች መካከል 2972 ያህሉ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ሲሆኑ 85 ፕሮጀክቶች የውጭ ባለሀብቶች፣ 64 ባለሀብቶች በጋራ የተሰማሩበት መስክ ሲሆን ቀሪዎቹ መንግሥታዊ ድርጅቶች ናቸው፡፡



## ፈቃድ የተሰጣቸው ኘሮጀክቶች ዓመታዊ ዕድገት

ኤጀንሲው ከተቋቋመበት ከ1986 ዓ.ም. ጀምሮ ባለው ጊዜ ውስጥ ፈቃድ የተሰጣቸው ባለሀብቶች እድገት ስንመለከት መንግሥት ለግሉ ኢንቨስትመንት በፈጠረው ምቹ ሁኔታ ምክንያት የነበረው ዓመታዊ ፍሰት ዕድገት እያሳየ የመጣ ሲሆን በ1998 ዓ.ም. በልዩ ልዩ ዘርፎች የሚሰማሩ 912 ባለሀብቶች ፈቃድ ወስደዋል፡፡ በ1999 እስከ ሰኔ 30 ባለው ጊዜ የወሰዱት ቁጥር 898 ደርሷል፡፡




## ፈቃድ የተሰጣቸው ኘሮጀክቶች በእንቅስቃሴ ደረጃቸው ሲታዩ

ፕሮጀክቶቹ በእንቅስቃሴ ደረጃቸው ሲገመገሙ ፈቃድ ከወሰዱት ጠቅላላ ፕሮጀክቶች መካከል 4.29% ፈቃዳቸው የተሰረዘ, 4.03% እንቅስቃሴ የሌላቸው, 54.37% በቅድመ ግንባታ ሂደት ላይ የሚገኙ ፣ 8.93% ግንባታ ላይ ያሉ ሲሆን 23.38% ማምረት ወይም አገልግሎት መስጠት የጀመሩ ናቸው፡፡



## የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች እንቅስቃሴ በዞኖችና ልዩ ወረዳዎች

የአዋሳን ከተማ ጨምሮ በክልሉ ውስጥ በሚገኙ 14 ዞኖችና 8 ልዩ ወረዳዎች ውስጥ ባለፉት አሥርት ዓመታት ፈቃድ የወሰዱ የኢንቨስትመንት ኘሮጀክቶች ስርጭት በዞን ሲቃኝ ከጠቅላላው ፕሮጀክቶች ድርሻ አንፃር አዋሣ 1013 ፕሮጀክቶችን በማስመዝገብ የመጀመሪያውን ሥፍራ ሲይዝ ሲዳማ ዞን 427 ፕሮጀክቶችን በማስመዝገብ ሁለተኛ ነው፡፡ ጉራጌ፣ ወላይታ፣ ጌዴኦ፣ ጋሞ ጎፋ እና ሃድያ በቅደም ተከተል 253፣250፣209፣200፣እና 203 ፕሮጀክቶችን አስመዝግበዋል፡፡ በክልሉ ካሉት 8 ልዩ ወረዳዎች መካከል በ7ቱ ለመሰማራት 63 ባለሀብቶች ፈቃድ ወስደዋል፡፡

አዋሳ የክልሉ ዋና ከተማ በመሆኗና አስፈላጊ መሠረተ ልማት አውታሮች በሙሉ የተሟሉ በመሆናቸው እንዲሁም ቁልፍ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ማዕከል በመሆኑ ፍሰቱ ከፍተኛ ሊሆን ችሏል፡፡ ይኸው ፍሰት ወደፊትም እንደሚቀጥል የሚጠበቅ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በየአካባቢው ለኢንቨስትመንት እየተፈጠረ ካለው ምቹ ሁኔታ በመነሳት በሁሉም ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች ያለውን እምቅ የተፈጥሮ ሀብት የሚያለሙ ባለሀብቶች በተለያዩ ሴክተሮች እንደሚሰማሩ ይጠበቃል፡፡






# ክፍል ሁለት

# የክልሉ የኢንቨስትመንት ፖቴንሻልና የልማት ቀጣናዎች፣

ይህ ክፍል *"የክልሉ ንጽጽራዊ የኢንቨስትመንት ፖቴንሻል፣ የልማት ቀጣናዎች፣ የዕድገት ማዕከላትና የልማት ኮሪደሮች ሁኔታ ከክልላችን ልማት አንጻር ምን ይመስላል?"* ለሚለው ጥያቄ በአጭሩ ምላሽ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

## 2.1 የክልሉ የኢንቨስትመንት ፖቴንሻል

ቀደም ሲል በክልላዊ ገጽታ ላይ እንደተመለከተው ክልሉ በተለያዩ የሥነምህዳር ዞኖች የተከፋፈለ በመሆኑ ልዩ ልዩ የግብርና ምርቶች ማለትም ሰብል፣ ጥራጥሬ፣ ቅመማ ቅመም፣ ፍራፍሬ፣ የብርዕና አገዳ ሰብሎች፣ ደን ልማት፣ ቡና ልማት ወዘተ እና የእንስሳት ሀብትና ተዋጽኦ (የቁም ከብት፣ ሥጋ ምርትና ኤክስፖርት፣ ቆዳና ሌጦ) ለማልማት እጅግ ምቹ ክልል ነው፡፡ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ ክልሉ የተለያዩ የከርሰ ምድር ሀብቶችና ማዕድናት ባለቤት መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ እንዲሁም ክልሉ የልዩ ልዩ ባህሎች ሙዚዬም ስለሆነ ለቱሪዝም ሴክተር እና ተያያዥነት ላላቸው ዘርፎች ልማት እጅግ ምቹ ነው፡፡ ይህን ዕምቅ ሀብት በመጠቀም የግል ባለሀብቶች በተለያዩ ዘርፎች እንዲሰማሩ ማድረግ የሚቻልበት ሁኔታ የተመቻቸ መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ ክልሉ ለግብርና ልማት፣ ለኢንዱስትሪ፣ ለአግሮ ኢንዱስትሪ ልማት፣ ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት፤ ለቱሪዝም ኢንዱስትሪ ልማት ለማዕድን ልማት፤ ለሃይል ማመንጫና በሰው ኃይል ረገድ ያለው ፖቴንሻል ከዚህ በሚከተለው ሁኔታ ቀርቧል፡፡

### 1. ለግብርና ልማት ያለው ፖቴንሻል

### ሀ. በሰብልና ፍራፍሬ ልማት፡-

በክልላችን 451.888.55 ሄክታር የገጠር መሬት ለኢንቨስትመንት ተግባር እንዲውል ተለይቷል፡፡ በሌላ በኩል ከክልላችን የቆዳ ስፋት 65.2% የሚሆነው ከ1000- 2000 ሚ.ሊ. ሜትር አመታዊ የዝናብ መጠን ያለው ከመሆኑም ሌላ ሦስት የስምጥ ሸለቆ ሀይቆች (አዋሣ፣ አባያና ፣ጫሞ) እና እንደ ኦሞ፣ጎጀብ ፣ወይጦ ፣ብላቴና ገላና የመሳሰሉ በርካታ ትላልቅና ትናንሽ ወንዞች ስላሉት በወቅታዊ ዝናብና በመስኖ የግብርና ልማት ለማካሄድ ምቹ ነው፡፡ እንዲሁም አግሮ ኢኮሎጂውና የመሬት ለምነቱ፤ ለሰብል ልማት፤ ለእንስሳት እርባታ፣ ለአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ተስማሚ ነው፡፡

ስለሆነም በተነፃፃሪ በክልሉ በተሻለ ሁኔታ ከሚለሙ የግብርና ልማቶች መካከል፡-.

1) የቅባት ሰብሎች፡- ሰሊጥ፣ ለውዝ፣ፓልም፣አኩሪአተር፣አቾሎኒ፣ ሱፍና የጥጥ ፍሬ ወዘተ፣
2) የጥራጥሬ ሰብሎች፡- ቦሎቄ፣ አኩሪ አተር፣ ሽንብራ፣ አተር፣ባቄላ፣ሩዝ ወዘተ፣
3) የምግብ ሰብሎች የብርዕ ህል /በቆሎ፣ ዘንጋዳ፣ስንዴ፣ ገብስ ወዘተ
4) ቅመማ ቅመም፡- ቁንዶ በርበሬ፣ ጥምዝ፣ ኮረሪማ ፣ዝንጅብል፣ሄል፣ ቁርንፉድ፣ ዕርድና የተለያዩ ዕፀ ጣዕሞች፣
5) ከፍራፍሬ፡-ማንጎ፣ አቮካዶ፣ አናናስ፣ ፓፓዬ፣ ሙዝ፣ ከደጋ ፍራፍሬዎች ፖም ወዘተ፣
6) የአገዳ ስብሎች፡- በቆሎ፣ ማሽላ፣ ዘንጋዳ ወዘተ።
7) ከአንቂ ሰብሎች- ቡናና ሻይ በአብዛኛው የክልሉ አካባቢዎች ይመረ ሉ።

## ለ. በእንስሳት ሀብት ልማት፡-

በኢንዱስትሪ ፖቴንሻል ጥናት መረጃ መሠረት የክልሉ የእንስሳት ሀብት የአገሪቱን 20% የያዘ ነው። ይኸውም በዝርዝር ሲታይ ክልሉ የ9.3 ሚሊዮን ቁም ከብት፣የ3.2 ሚሊዮን በጎች፣ የ2.7 ሚሊዮን ፍየሎች፣ የ0.8 ሚሊዮን ጋማ ከብቶች፣ የ7.3 ሚሊዮን ዶሮች፣ ባለቤት እንደሆነ መረጃዎች ያሣያሉ።

ስለሆነም ከፍ ብሎ በተመለከሳ መሰረት ክልሉ ካለው ሰፊ የ ንስሳት ሀብት አንጻር በዚህ ዘርፍ ለሚሰማሩት ባለሀብቶች ሰፊ የኢንቨስትመንት ዕድል አለ። ጥቂቶችን ለመጥቀስ ያህል፡-
በከብት ማደለብ፣ ወተትና የወተት ተዋፆኦ ልማት፣ በማር ምርት፣ በሰጎን፣ አዞና፣አሳ ልማት ሰፊ አማራጮች አሉ። ከዚህ በተጨማሪ ሰፊ የእንስሳት ሀብት በሚገኝባቸው የክልሉ አካባቢዎች ዘመናዊ ቄራዎችን በማቋቋም ለውጭም ሆነ ለሀገር ዉስጥ ገበያዎች ሥጋ የማቅረብ ሥራ በስፋት ለማከናወን የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎች በክልሉ አሉ።

## 2. ለአግሮ-ኢንዱስትሪ ያለው ፖቴንሻል

ይህ ኢንዱስትሪ የግብርና ምርቶችን እሴት ጨምሮ ለገበያ የማቅረቢያ ኢንዱስትሪ ሲሆን ሀገራችን ካላት ሰፊ የግብርና ሀብት አንጻር በዚህ ዘርፍ መሰማራት ለሚሹ ባለሀብቶች ምቹ ጥሬ ሀብት በክልላችን ይገኛል።

ስጋና የስጋ ውጤቶች ማቀነባበሪያ፣ቆዳ ኢንዱስትሪ፣ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ፣ወተት ማቀነባበሪያ፣ማር ማቀነባበር፣ምግብ ፕሮሴሲንግ እና ምግብ ነክ፣(ስኳር ማምረቻ ኢንዱስትሪ፣ የፍራፍሬ ማቀነባበሪያ (ሙዝ፣ማንጎ፣አናናስ፣ አፕል/ፓም/)፣ ሳሙናና ሌሎች የንጽህና መጠበቂያ ዲተርጅንቶች፣ቅመማ ቅመም ማቀነባበር /ዝንጅብል ፣ዘይት የበርበሬ ድልህ፣የጥጥ

መዳመጫ የልብስ ስፌት፣ቡና ቆልቶ ፈጭቶና በጥራት አሽጎ ለውጭ ገበያ ማቅረብ፣ችፑድ ፐልፐና የወረቀት ምርቶች፣የምግብ ቀለም ፋብሪካ ወዘተ... የክልሉ የንጽጽራዊ ጥንካሬ አካል በመሆናቸው የኢንቨስትመንት ፖቴንሻል ናቸው፡፡

3. ለቱሪዝም ኢንዱስትሪ ልማት ያለው ፖቴንሻል ፡

ክልሉ በሀገሪቱ ከሚገኙ 85 ብሔረሰቦች መካከል የ56ቱ መኖሪያ በመሆኑ የብሔረሰቦች ሙዚየም ተሰኝቷል፡፡ የእነዚህ ብሄረሰቦች የተለያየ የባህል እሴቶች ራሳቸው የቱሪዝም መስህቦች ከመሆናቸውም በላይ የተለያዩ ባሕላዊ ሴቶች የሚ ዩባቸው ነጭ ሳር፣ ማጎ፣ ኦሞ፣ ማዜና ጨርጨራ ጨበራ የተባሉ በጠቅላላው 5 ብሔራዊ ፓርኮች፣2 የዱር አራዊት ጥበቃ ስፍራዎችና 6 የጥብቅ አደን አካባቢዎች፣ በዓለም ቅርስነት ከተመዘገቡት ሰባት የሀገሪቱ ቅርሶች መካከል ሁለቱ ማለትም የጢያ ትክል ድንጋይና የ ችኛው ኦሞ ሸለቆ የቅድመ ሪክ ጥናትና ምርምር ቦ ዎችም በዚሁ ክልል የሚገኙ ናቸው፡፡ በክልሉ በሚገኙ በእነዚህ ፓርኮች የሚገኙ የዱር እንስሳትና አእዋፋት፣ ማራኪ የመሬት አቀማመጣቸውና ረጅም እድሜ ያስቆጠሩ አስደናቂ ታሪካዊ ቅርሶች፣ በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ በርካታ ትላልቅና ትናንሽ ወንዞችና ሐይቆች (ኦሞ ወንዝ፣ አዋሳ፣አባይና ጫሞ ሀይቆች) በመዝናኛ ሥፍራነት በምሳሌነት ከሚጠቀሱት ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

እነዚህንም ለመጎብኘት በዓመት ከ108,853 በላይ ቱሪስቶች የሚመጡ ቢሆንም እስከአሁን ያለው የቱሪስት አገልግሎት አቅርቦት ስፋትና ጥራት እጅግ አነስተኛ ነው፡ ይህንን መነሻ በማድረግ በመስኩ ባለሀብቶችን ለመሳብ 200 የፕሮጀክት ሃሳቦችና 50 ፕሮጀክት ፕሮፋይሎች ተዘጋጅተዋል፡፡ ይሁን እንጂ ከሚጠበቀው ውጤት አንጻር መስኩ ፖቴንሻል ገና ያልተነካ በመሆኑ በመስኩ መሰማራት አዋጭነት እንዳለው ይታመናል፡፡

4. ለኢንዱስትሪ ልማት ያለው ፖቴንሻል ፡-

በአጠቃላይ በክልሉ በሚገኙት በ18 የሪፎርም ከተሞች ማለትም አዋሳ፣ይርጋለም፣ዲላ፣ይርጋጨፌ፣ ወላይታሶዶ፣አርባምንጭ፣ቦዲቲ፣አረካ፣ሳውላ፣ዱራሜ፣ሆሳዕና፣ቡታጅራ፣ወልቂጤ፣ቦንጋ፣ቴፒ፣ሚዛን-አማን፣ጂንካ እና አላባ ውስጥ ባሉ የኢንዱስትሪ መንደሮች ከ370 ሄ/ር በላይ መሬት የለማ እና 940 ሄክታር የተከለለ ሲሆን በድምሩ 7300 ሄክታሬ በላይ መሬት ደግሞ በ56 ከተሞች ለማኀበራዊና ሌሎች አገልግሎቶች ተዘጋጅቷል፡፡

በኢንዱስትሪ ልማት ረገድ በሀገሪቱም ሆነ በክልሉ ያለው ዕድገት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው፡፡ ንደሀገራችን ባሉት ዳጊ ሀገሮች የሚኖሩት ኢንዱስትሪዎች በአብዛኛው በቀላል ኢንዱስትሪ ደረጃ የሚመደቡ ናቸው፡፡

ለእነዚህ ቀላል ኢንዱስትሪዎች በክልላችን ምቹ ጥሬ ሀብት የሚገኝ ሲሆን ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል የብረ ብረት ሥራ፣ የቡና መፈልፈያ ወይም መቀሸሪያ፣ የሕትመት ሥራ፣ የሴራሚክ፣ የ ንጨት ሥራና ምግብ ማሸጊያ ፋብሪካዎች ወዘተ ናቸው፡፡

### 5. ለኃይል ማመንጫ ያለው ፖቴንሻል ፡-

በክልሉ 111.5 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት የሚችሉ 26 አነስተኛ ወንዞች የተጠ ኑበት ሁኔታ ስላለ መስኩ ሰፊ ዕድል ይዞ ይጠብቃል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ኦሞ ወንዝ ብቻውን 36,560 ሜጋ ዋት ኃይል የማመንጨት አቅም አለው፡፡

### 6. ማዕድንና ኢነርጂ ሀብት ያለው ፖቴንሻል፡-

ከፍተኛ የኢኮኖሚ ጥቅም የሚያስገኙ ውድ የሆኑ የማዕድን ሀብቶች በክልሉ ውስጥ ንደሚገኙ ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ የነጭና የቀይ ድንጋይ ክምችት፣ የላይም ስቶን ወይም ኖራ፣ የወንዝ አሸዋ፣ ድንጋይ፣ ሪሆላይት፣ ኢገኒምብራይት ንዲሁም ሳተ ገሞራዊው ዓመድ ተብለው የሚ ወቁት የቀይና ጥቁር አሸዋ ሀብት፣ ወርቅ፣ ብረት ወዘተ በስፋት ስለሚገኙ በዚህ ዘርፍ በፍለጋም ሆነ በማምረት ተግባር የሚሰማሩ ባለሀብቶች የሚበረታቱበትን ሁኔታ በማመቻቸት በኩል ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

#### ሀ. ዳሽ የማይነጥፍ የ ይል ምንጭ በተመለከተ፡-

በክልሉ ለረዥም ሰዓት የሚቆይ የፀሐይ ብርሃን ያለ በመሆኑ ከፀሃይ የሚገኘውን ብርሃንና ሙቀት ለ ይል አቅርቦት አማራጭነት ለመጠቀም የሚያስችል ቴክኖሎጂ የመስፋፋት አቅም አለው፡፡

#### ለ. ጂኦ-ተርማል ኢነርጂ (የከርሰ ምድር ሙቀት)

የከርሰ ምድር ሙቀት በክልላችን ንደሚኖር የተለያዩ ፍንጮች በተለይም የፍል ውሃዎች በብዙ የክልሉ አካባቢዎች የሚገኙ በመሆኑ ሰፋ ያለ ጥናት በመስኩ ተደርጎ ይህ ይል አካባቢውንና ክልሉን ንዲሁም ሀገሪቱን የሚጠቅምበት ሥልት ሊነደፍለት ይገባል፡፡

## 2.2. ልማት ቀጣናዎች፣ የ ድገት ማዕከላትና የልማት ኮሪደሮች

ንደ ኢትዮጵያ ባሉና በልማት ወደ ኋላ በቀሩ አገሮች የተወሰኑ አካባቢዎች የተሻለ የዕድገት ደረጃ ላይ በሚገኙበትና በአብዛኛው አካባቢ የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ የመሠረተ ልማት ሥርጭት ውስን በሆነበት፣ በዚህም መነሻ በክልሎች መካከልና ውስጥ ንዲሁም በገጠርና

በከተማ መካከል ያለው የዕድገት ልዩነት በሰፋበት ነዚህንና ሌሎች መጠነ ሰፊ የዕድገት ማነቆዎች ለማስወገድና ዘላቂ ልማት ማምጣት ንዲቻል ክፍለ ኢኮኖሚያዊ /ሴክቶራል/ የልማት ዕቅድን በመተካት መልክአ ምድራዊ አሀድ (Geographic Unit) ላይ የተመሠረተ አካባቢያዊ የልማት ዕቅድ ፕላኒንግ (Spatial Development Planning) ማውጣትና መተግበር ሚዛናዊና ውጤ ማ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ከግቡ ንዲደርስ ዓይነተኛ መሣሪያ ስለመሆኑ በተለያዩ ሀገሮች ተሞክሮ ተረጋግጧል፡፡ የአካባቢ የዕድገት ማዕከላትን መሠረት በማድረግ የሚ ቀደውና የሚተገበረው ክልላዊ ዕቅድ ለአፋጣኝና ለተመጣጠነ ዕድገት ጉልህ ድርሻ ንዳለው ቀደም ሲል ይህንን የልማት አቅጣጫ ተከትለው የተሻለ ውጤት ካገኙት አገሮች የተገኙት መረጃዎች ያመለክ ሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ

1. በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፈጣንና ዘላቂ ልማት በማምጣት ድህነትነን ለማጥፋት እንዲቻል በታቀደው የዕቅድ (PASDEP) ሠነድና
2. የኢሕአዴግ 6ኛ መደበኛ ጉባዔ ሪፖርት ላይ በሀገራችን የተለያዩ አካባቢዎች ባላቸው ምቅ ሀብትና የልማት አለኝ ነት ተጠንተውና ተመርጠው የልማት ቀጣናዎች (የዕድገት ማዕከላት) በአግባቡ ተለይተው የልማት ንቅስቃሴው በተፋጠነ አቅጣጫ ንዲጀመርና በ ስከዛሬው ጥረ ችን ያልተሟሉ የልማት ክፍተቶች ንዲሟሉ ማድረግ አስፈላጊና ተገቢ መሆኑ በተቀመጠው መሠረት
3. በክልላችን ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ዕድገት ለማምጣት ንዲቻል የማልማት አቅም ያላቸውን ማዕከላት በጥንቃቄ ንዲመረጡ በማድረግና ለማዕከላቱ የልማት ንቅስቃሴ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔ ዎችን በማመቻቸት አዲስ የልማት አቅጣጫ መያዝ ተገቢ መሆኑን የክልሉ መንግሥት በማመን የልማት ቀጣናዎች ፣ የልማት ማዕከላትና የልማት ኮሪደሮች እንዲለዩ የተደረገ ሲሆን በእነዚህ የልማት ቀጣናዎች ተግባራዊ እንዲደረጉ የሚያስፈልጉ አንኳር ፕሮጀክቶችና ደጋፊ ፕሮጀክቶች ተለየተዋል፡፡

በዚህ መሠረት በየአካባቢው የሚደረጉ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በተመረጡ የልማት ቀጣናዎች ተግባራው በሚደረጉበት ጊዜ በየአካባቢው በጥናት ተለይተው የተመረጡትን አንኳርና ደጋፊ ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ እንዲያደርጉ በከፍተኛ ደረጃ የሚበረታቱ ሲሆን በመሬት አቅርቦት፣ በመሠረተ-ልማት ፣ በማትጊያ ወዘተ በመንግሥት በኩል ልዩ ትኩረት ይደረግላቸዋል፡፡

| ተ.ቁ | የልማት ቀጣናውሥም | የልማት አካባቢ | የ ድገት ማዕከሉ ስም | ዋና ኘሮጀክት Anchor project | ተጨማሪ ኘሮጀክት Supplementary Projects | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የላይኛው የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ የልማት ቀጣና | | ስልጤ | የተሻሻሉ የበርበሬ ዝርያዎች ልማት ማስፋፊያ ፕሮጀክት | አዋጭነት ያላቸው አትክልትና ፍራፍሬ ልማት ፕሮጀክት<br>የአበባና ሌሎች ኤክስፖርቴብል ጽዋት ልማት ፕጀክት<br>የ ንስሳት ሐብት ልማት /ፕሮጀክት<br>አማራጭ የሐይል ምንጭ የሚያስተዋውቅና<br>የሚያሰራጭ ፕሮጀክት<br>የላይም ስቶን /የኖራ ድንጋይ/ ማበልፀጊያና ማምረቻ. | የበርበሬ ማዘጋጃና ማቀነባበሪያ ፋብሪካ፣<br>በቆሎ፣ ስንዴና ጥራጥሬ ንዲሁም የመሣሠሉትን ማዘጋጃና ማቀነባበሪያ ፋብሪካ፣<br>የቆዳና ሌጦ ማከማቻና ማዘጋጃ መጋዘኖች፣<br>የዘይትና ሳሙና ፋብሪካዎች፣ |
| 2 | | የልማት አካባቢ 1 | እዣ | | የኦሞ ጊቤ የተቀናጀ የተፋሰስ ልማት ፕሮጀክት<br>የአነስተኛ መስኖ ልማት<br>የ ንስሳት ሀብት ልማት ማሻሻያ ፕሮጀክት<br>የደጋ ፍራፍሬ ማስፋፊያ<br>የማዕድን ልማት ፕሮጀክት<br>የድህረ ምርት ቴክኖሎጂዎች ማስፋፊያ ፕሮጀክት<br>የአማራጭ ኢነርጂ ልማት | • ከ ንስትና ከሌሎች ሥራ ሥር ሰብሎችን ስ ርች መጭመቂያ ኢንዱስትሪ፣<br>• የዱቄት፣ የፓስ ና ማካሮኒ ምግብ ኮምፕሌክስ፣<br>• የቆዳ ማልፊያና የቆዳ ውጤቶች፣<br>• የወተትና የወተት ውጤቶች ማቀነባበሪያ፣<br>• የቃጫ ውጤቶች ፋብሪካ ፣<br>• የጐጆ ኢንዱስትሪ፣<br>• የፍራፍሬ ማቀነባበሪያ ፕሮጀክት፣<br>• የደን ውጤቶች /የወረቀት ፋብሪካ፣<br>• ከተለያዩ ዕፅዋቶች የቦተንካል ኬሚካል ዝግጅት፣<br>• ማአዛና ዘይቶች፣ |
| | ሰሜናዊ ደጋማ ሰብል አምራች የልማት ቀጣና | የልማት አካባቢ 2 | ሌሞ | በአርሶ አደር አማካኝነት የዳቦ ስንዴ ልማት ማስፋፊያ ፕሮጀክት | የደጋ ፍራፍሬና አትክልት ልማት<br>የደን ልማት ፕሮጀክት<br>የመድሃኒት ጽዋትና የአበባ ልማት ፕሮጀክት<br>የ ንስሳት ሐብት ልማት<br>የሰፋፊ ርሻዎች ልማት<br>የአነስተኛ መስኖ ልማት<br>የቆዳና ሌጦ ማሻሻያ<br>የፖሪትረምና አርቴሚዝያ የተባሉ ጽዋት ማስፋፊያ ፕሮጀክት<br>የአማራጭ ኢነርጂ ልማት | |

| ተ.ቁ | የልማት ቀጣናውሥም | የልማት አካባቢ | የ ድገት ማዕከሉ ስም | ዋና ፕሮጀክት Anchor project | ተጨማሪ ፕሮጀክት Supplementary Projects | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 3 | ማዕከላዊ የሰብል አምራች የልማት ቀጣና | የልማት አካባቢ 1 | ሶዶ ዙሪያ | | የአፈርና ውሃ ጥበቃ ፕሮጀክት<br>የ ንስሳት ርባ ፕሮጀክት<br>የጃትሮፋ ተክል ልማት<br>አነስተኛ መስኖ ልማት<br>የፍራፍሬ ልማት<br>የንብ ርባ<br>የአማራጭ ኢነርጂ ልማት | የፍራፍሬ ማቀነባበሪያ ማሸጊያ ፕሮጀክት፣<br>የ ደ ጥበባት /ሽመና፣<br>የሸክላ ሥራ፣<br>የቆዳ ሥፌት ማሻሻያ ፕሮጀክት/፣<br>የቆዳና ሌጦ ማልፊያና ማደራጃ ፋብሪካ፣<br>የሳሙና ፋብሪካ፣ |
| | | የልማት አካባቢ 2 | ቃጫ ቢራ | | የፍራፍሬ ልማት<br>የ ንስሳት ዝርያ ማሻሻያ<br>የአፈርና ውሃ ጥበቃ ፕሮጀክት<br>የጃትሮፋ ልማት ለባዩዲዝል<br>የጥጥ ርሻ ልማት<br>ንብ ርባ<br>የ ንዱስትሪ ማዕድናት ልማት<br>የአማራጭ ኢነርጂ ልማት | |
| | | የልማት አካባቢ 3 | ጎፋ | የቦሎቄ ማስፋፊያ ልማት ፕሮጀክት | የ ንስሳት ሐብት ልማት<br>የቱሪዝም ልማት<br>የቅባት ሰብሎች ልማት<br>የጥጥ ርሻ ልማት<br>አነስተኛ መስኖ ልማት<br>የፍራፍሬ ልማት<br>ቅመማቅመም ልማት<br>የጃትሮፋ ልማት ለባዩዲዝል<br>የአማራጭ ኢነርጂ ልማት | |

| ተ. ቁ | የልማት ቀጣናውሥም | የልማት አካባቢ | የ ድገት ማዕከሉ ስም | ዋና ኘሮጀክት Anchor project | ተጨማሪ ኘሮጀክት Supplementary Projects | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 4 | ማዕከላዊ የደጋ ሰብልና ፍራፍሬ አምራች የልማት ቀጣና | | ቦንኬ | የደጋ ፍራፍሬ ልማት | የቀርከሃ ምርት ማሳደጊያ ልማት<br>የቱሪዝም መስህቦች ማጠናከሪያ<br>የማገዶና ግንባ  ደን ልማት<br>የአማራጭ ኢነርጂ ጥናትና ልማት<br>የ ንስሳት ልማት ፕሮጀክት | የወተትና የወተት ተዋጽኦ ማቀነባበሪያነ<br>የቆዳና ሌጦ ማቀነባበሪያነ<br>የፍራፍሬ ማቀነባበሪያነ<br>የምግብ ዘይት መጭመቂያ  ንዱስትሪነ<br>የባዮ ዲዝል ማምረቻ  ንዲስትሪነ<br>የጥጥ ማዳመጫ  ንዱስትሪነ<br>የጨርቃጨርቅ  ንዱስትሪነ<br>የዝንጅብል መጭመቂያ  ንዱስትሪነ<br>የጥራጥሬ ዱቄት ማምረቻ  ንዱስትሪነ |
| 5 | ምስራቃዊ የቡና  አምራች የልማት ቀጣና | | ወናጎ | የቡና ልማት ማስፋፊያ ፐሮጀክት | ለ ርጥበት አጠር አንባቢ ተስማሚ ሰብሎች ልማት<br>ፍራፍሬ ልማት<br>ወተትና የወተት ውጤቶች<br>አነስተኛ መስኖ ልማት<br>የጥራጥሬ ምርት ልማት<br>የማዕድን ውሃ ልማት<br>ቱሪዝም ልማት<br>የአማራጭ ኢነርጂ ልማት | • የቡና ማቀነባበሪያ /ቡና ቆልቶ የሚፈጭና የሚያሽግ ኢንዱስትሪነ<br>• የቡና ማበጠሪያ ኢንዱስትሪ<br>• የቆዳና ሌጦ ኢንዱስትሪነ<br>• የፍራፍሬ ውጤቶች ማቀነባበሪያና ማሸጊያ ኢንዱስትሪነ<br>• በቡና ገለባ ላይ የተመሰረቱ የቺፕ ውድና የማገዶ ማምረቻ ኢንዱስትሪነ<br>• የ ንስት ተክል ምርት ውጤቶች ማቀነባበሪያና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ ናቸው:: |
| 6 | ምስራቃዊ የደጋ ሰብል አምራች የልማት ቀጣና | | በንሣ | የ ንስሳት ርባ | የማገዶና የግንባ  ና ደን ልማት<br>የደጋ ፍራፍሬ ልማት<br>የወርቅ ጥናትና ልማት<br>የአማራጭ ኢነርጂ ልማት | የሥጋና የወተት ውጤቶች ማደራጃ ፋብሪንነ<br>የቆዳና ሌጦ ፋብሪንነ<br>የዱቄት ፋብሪንነ<br>የሳሙና ፋብሪንነ<br>የ ንስሳት ማደለቢያነ<br>የፍራፍሬ ማቀነባበሪያ ማሸጊያ ፕሮጀክትነ |

| ተ.ቁ | የልማት ቀጣናውሥም | የልማት አካባቢ | የ ድገ ት ማዕከሉ ስም | ዋና ፕሮጀክት Anchor project | ተጨማሪ ፕሮጀክት Supplementary Projects | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 7 | ምዕራባዊ የልማት ቀጣና | የልማት አንባቢ 1 | ቤንች | ንጨት ያልሆኑ የደን ሐብት ውጤቶች ማስፋፊያ ዋና ፕሮጀክት (ንትፍፕ) | የጫን ቡና ልማት<br>ቅመማ ቅመም ልማት ማስፋፊያ<br>የደን አጠባበቅ ፕሮጀክት<br>የ ንስሳት ሐብት ልማት<br>በአርሶ አደር ደረጃ የሻይ ልማት ማስፋፊያ ፕሮጀክት | የማርና የሰም ምርት ማቀነባበሪያ ፋብሪንነ<br>የቡና ማዘጋጃ ኢንዱስትሪነ<br>የ ሸት ቡና መፈልፈያ ኢንዱስትሪነ<br>የቆዳና ሌጦ ማዘጋጃ ፋብሪናነ<br>የቅመማ ቅመም ማዘጋጃና ማቀነባበሪያ ፋብሪናነ<br>የዱቄት ምርት ማዘጋጃ ኢንዱስትሪነ<br>ዘመናዊ የንብ ቀፎ ማምረቻ ማዕከልነ<br>የተሻሻለ የማርና የማር መያዣ ማምረቻነ<br>የሻይ ማቀነባበሪያ ፋብሪንነ |
| | | ልማት አንባቢ 2 | ማሻ | | የማርና ሰም ምርትማሳደጊያ<br>ህብረተሰብን ያሳተፈ የደን አጠባበቅ<br>የቀርከሀና የቀርከሀ ውጤቶች ልማት<br>የጫካ ቡና ልማት ማስፋፊያ<br>ቅመማ ቅመም ልማት ማስፋፊያ<br>በአርሶ አደር ደረጃ የሻይ ልማት ማስፋፊያ | |
| | | የልማት አንባቢ 3 | ጊምቦ | | የማርና ሰም ምርትማሳደጊያ<br>ህብረተሰብን ያሳተፈ የደን አጠባበቅ<br>የ ንስሳት ሀብት ልማት<br>የጫን ቡና ልማት ማስፋፊያ<br>ቅመማ ቅመም ልማት ማስፋፊያ<br>በአርሶ አደር ደረጃ የሻይ ልማት ማስፋፊያ | |
| 8 | ማዕከላዊ የኦሞ ጊቤ ተፋሰስ የልማት ቀጣና | | ማረቃ | የተፈጥሮ ደንና ቅመማ ቅመም ልማት | የ ንስሳት ርባ ና ልማት<br>የደን ልማት ማቀነባበሪያ<br>የንብ ዕርባ<br>የፍራፍሬ ልማት<br>የቱሪዝም ልማት<br>የአማራጭ ኢነርጂ ልማት | የ ንስሳት ተዋጽኦ ማቀነባበሪያነ<br>የደን ልማትና ማቀነባበሪያ ፕሮጀክትነ<br>የማርና የሰም ምርት ማቀነባበሪያ ፋብሪንነ<br>የፍራፍሬ ልማትና ማቀነባበሪያነ<br>የቅመማቅመም ማቀነባበሪያ ፋብሪን ኖ<br>የቅባት ፋብሪን ኖ |

| ተ.ቁ | የልማት ቀጣናውሥም | የልማት አካባቢ | የ ድገ ት ማዕከሉ ስም | ዋና ኘሮጀክት Anchor project | ተጨማሪ ኘሮጀክት Supplementary Projects | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 9 | የአባያና ጫሞ ሐይቆችና አካባቢ የልማት ቀጣና | | አርባም ንጭ ዙሪያ | ዘላቂነት ያለው የአሣ ሃብት ልማት | የቱሪዝም ሀብት ልማት<br>የሰብል ልማት<br>የ ንስሳት ሀብት ልማት<br>የተፋሰስ ልማትና ጥበቃ መሰረት ያደረገ<br>የማገዶና ግንባ ደን ልማት<br>የአዞ ዕርባ ልማት | የአሣ ሥጋ ማቀነባበሪያና ማዘጋጃ፣<br>የአዞ ቆዳ ማለስለሻና ማዘጋጃ፣<br>ደረጃቸውን የጠበቁ ባለ ኮከብ ሆቴሎች ግንባ ፣<br>የዱቄትና የጣፋጭ ምግብ ማዘጋጃ ፋብሪካ፣<br>የወተት ምርት ማቀነባበሪያ፣<br>የሥጋ ፋብሪካ፣<br>የአትክልትና ፍራፍሬ ማቀነባበሪያ፣<br>የቱሪስት አስጐብኚ ድርጅት፣<br>የሀይቅ ላይ መዝናኛ አገልግሎት (የጀልባ ሽርሽር፤ሀይቅ ላይ ስፖርት፣ |
| 10 | የአርብቶ አደር አካባቢ የልማት ቀጣና | የልማት አካባቢ 1 | ባኮ ጋዘር | የኦሞ ወንዝ ግድብ ልማት ፕሮጀክት | ሰፋፊ የመስኖ ርሻ<br>የ ንስሳት ሀብት ልማት<br>ቱሪዝም ልማት<br>የአዞና ሰጐን ርባ<br>አሣ ሀብት ልማት<br>ፍራፍሬ ልማት<br>ጣንና ሙጫ ምርት<br>ንብ ርባ<br>የአማራጭ ኢነርጂ ልማት | ምግብ ዘይት ፋብሪካ፣<br>የባዮዲዚል ፋብሪካ፣<br>የከብት ማድለብ ሥራዎች፣<br>የሥጋ ፋብሪካ፣<br>የ ንስሳት ቆዳና ሌጦ ማዘጋጃ ፋብሪካ፣<br>የማርና ሰም ማቀነባበሪያ፣<br>የዕጣን ምርት ማዘጋጃ ኢንዱስትሪ፣<br>የፍራፍሬ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ፣<br>የቅመማ ቅመም ማቀነባበሪያ፣<br>በማዕድን ኢንዱስትሪ፣<br>የአሣ ሥጋ ማቀነባበሪያና ማዘጋጃ፣<br>የአዞ ቆዳ ማለስለሻና ማዘጋጃ፣<br>ደረጃቸውን የጠበቁ ባለ ኮከብ ሆቴሎች ግንባ |
| | | የልማት አካባቢ 2 | ሱርማ | | የመስኖ ልማት<br>የ ንስሳት ሀብት ልማት<br>ቱሪዝም ልማት<br>ፍራፍሬ ልማት<br>የ ጣን ምርት<br>ቡናና ቅመማ ቅመም<br>ደንና የደን ውጤቶችልማት<br>ንብ ርባ<br>የአማራጭ ኢነርጂ ልማት<br>የማዕድን ሐብት ልማት | |

| ተ.ቁ | የልማት ቀጣናውሥም | የልማት አካባቢ | የ ድገ ት ማዕከሉ ስም | ዋና ፕሮጀክት Anchor project | pplementary Projects | ተጨማሪ ፕሮጀክት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የልማት አካባቢ 3 | ኩራዝ | | የመስኖ ልማት<br>የ ንስሳት ሀብት ልማት<br>ቱሪዝም ልማት<br>የቅባት ሰብሎችና ፍራፍሬ ልማት<br>በዝናብ የሚመለማ ሰፋፊ ርሻ<br>ቡናና ቅመማ ቅመም<br>ደንና የደን ወጤቶች ልማት<br>ንብ ርባ<br>የአማራጭ ኢነርጂ ልማት<br>የማዕድን ሐብት ልማት | |
| 11 | የአዋሣ ሐይቅና አከባቢ ልማት | | አዋሳ ዙሪያ | የዓሣ ሀብት ልማት ፕሮጀክት | የቱሪዝም ልማት<br>የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት<br>የሸንኮራ አገዳ ልማት<br>የ ንስሳት ማደለቢያ<br>ዶሮ ርባ<br>የአማራጭ ሀይል ምንጭ ልማት | አትክልትና ፍራፍሬ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ፣<br>የዱቄት ፋብሪካ፣<br>የሥጋ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ፣<br>የዶሮ ሥጋ ማዘጋጃና ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ፣<br>ደረጃቸውን የጠበቁ የቱሪስት ማስተናገጃ ሆቴሎች፣<br>የዓሳ ምርት ማዘጋጃና ማቀነባበሪያ ፋባሪካ፣<br>የዓሳማ ርባ ና ሥጋ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ፣<br>የደን ውጤቶች መሰረት ያደረገ የ ንጨት ሥራ፣<br>የቱሪስት አስጎብኚ ድርጅት፣<br>የሀይቅ ላይ መዝናኛ አገልግሎት (የጀልባ ሽርሽር፣ሀይቅ ላይ ርት)<br>የወተትና የወተት ተዋጽኦ ማቀነባበሪያ፣<br>የአኩሪ አተር ዘይት መጭመቂያ ንዱስትሪ፣<br>ዳና ውጤቶች ማምረቻ ፋብሪካ፣ |
| 12 | ደቡባዊ ልዩ ወረዳዎች የልማት ቀጣና | | ኮንሶ | በግና ፍየል ማርባትና ማሞከት | ንብ ማንባት<br>የማዕድን ሀብት ልማት<br>የዶሮ ርባ<br>የቱሪዝም ልማት<br>አነስተኛ መስኖ<br>ጣንና ዛፎችን ማልማት<br>የአፈርና ውሃ ጥበቃ ፕሮጀክት<br>የአማራጭ ኢነርጂ ልማት | የሥጋ ፋብሪካ፣<br>የቆዳና ሌጦ ፋብሪካ፣<br>የማር ማቀነባበሪያ፣ |

# ክፍል ሦስት

## በክልሉ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የተከናወኑ ተግባራትና የተገኙ ዉጤቶችና መሠረታዊ ችግሮቻቸው

### 3.1. በክልሉ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የተከናወኑ ተግባራትና ጉድለቶቻቸው

ባለፉት ዓመታት በክልላችን ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ለማበረታታት የተለያዩ ፖሊሲዎች፣ አዋጆችና ደንቦች፣ የአሠራር ሥርዓት የማሻሻል ሥራዎች ሲከናወኑ ቆይተዋል፡፡ የተሰሩት ሥራዎች ለዘርፉ ያበረከቱትን ፋይዳ በተመለከተ በጥልቀት የተጠና ጥናት ባይኖርም በተጨባጭ ከሚታየው ስንነሳ የግል ዘርፉ የክልሉን ዕድገት ከማፋጠንና ድህነትን ከመቀነስ አንፃር ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ ይገኛል፡፡ በመሆኑም የግሉ ኢንቨስትመንት ሴክተር የሚጠበቅበትን ክልላዊ አስተዋጽኦ ከማበርከት አኳያ የተከናወኑ ተግባራትንና ያጋጠሙትን ጉድለቶች ቀጥሎ ለማየት ተሞክሯል፡፡

#### 3.1.1. የማስተዋወቅና የማስፋፋት ሥራዎችን በተመለከተ

በአብዛኛው ኢንቨስትመንትን የማስፋፋት ስራዎች በባለቤትነት ተትቶ የነበረው ለክልሉ ኢንቨስትመንት መ/ቤት ብቻ ነበር፡፡ ኢንቨስትመንት በባህሪይው ከብዙ ሴክተር መ/ቤቶችና ሌሎች ቢሮዎች ጋር በቅንጅት የሚሠራ ሆኖ ሳለ ከኢንቨስትመንት መ/ቤት ባሻገር ኢንቨስትመንትን የማስፋፋቱና ምቹ ሁኔታ የመፍጠሩ እንቅስቃሴ በሌሎች አካላት እንደትርፍ ሥራ የሚታይ በመሆኑ የኢንቨስትመንት መ/ቤት ብቻውን የሚያደርገው እንቅስቃሴ በአንድ እጁ ከማጨብጨብ ያለፈ አልነበረም፡፡ ሆኖም የክልሉ ኢንቨስትመንት መ/ቤት የክልሉን ሀብት በህትመት፣ በኤግዚብሽኖችና በባዛሮች በመሳተፍ፣ ከባለሀብቶች ጋር በግንባር በመገናኘት፣ በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች በርካታ የማስተዋወቅ ሥራዎች ሰርቷል፡፡ ነገር ግን ይህንኑ የማስተዋወቅ ሥራ ለመሥራት ይተላለፉ የነበሩት መረጃዎች በጣም ጠቅለል ያሉ ስለነበሩ በተለይ ከክልሉ ንፅፅራዊ ጠቀሜታ አንፃር ዘርፎች ተለይተውና ለተለዩትም ምቹ የሆኑ ፓኬጆች ተዘጋጅተውላቸው የሚተላለፉ ስላልነበረ መልዕክቱ ለባለሀብቶች በአግባቡ ተላልፎ ወደ ክልሉ እንዲሳቡ የሚያደርግበት ብቃት ያልነበረው ነው፡፡

#### 3.1..2. የፖሊሲ ሥራዎችን በተመለከተ

ለግሉ ኢንቨስትመንት ምቹ አሠራርን ለመፍጠር ባለፉት አመታት በፌደራልም ይሁን በክልሉ መንግስት አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ወጥተዋል፡፡

በፌዴራል መንግሥት ደረጃ የኢንቨስትመንት አዋጅና የማበረታቻ ደንብ ባለሀብቱን በይበልጥ ሊያሰሩ በሚችሉ መልኩ በየጊዜው ተሻሽለዋል፡፡ ሆኖም እነዚህ በፌደራል ደረጃ የወጡት አዋጆችና ደንቦች

በየተሻሻሉበት ወቅት በክልሉ ውስጥ ለሚገኙ አግባብነት ላላቸው መስሪያ ቤቶችም ይሁን አስፈጻሚ አካላት ግንዛቤ እንዲጨብጡ የተደረገው ጥረት አጥጋቢ አልነበረም፡፡

በሌላ በኩል በክልላችን ደረጃ የወጡት የኢንቨስትመንት አስተዳደር አዋጅና ለኢንቨስትመንት ተግባር የሚውል የገጠር መሬት ደንብ የወጡ ሲሆን ሲዘጋጁ የሚመለከታቸው ወገኖች በአግባቡ ያልተሳተፉበትና በአመዛኙ ከአንድ ወገን የቀረቡ ቢሆኑም ወጥ አሰራሮችን ከማስፈን አንጻር የኢንቨስትመንት አስተዳደሩን ሲያግዙ ቆይተዋል፡፡ ከነዚህ በተጨማሪም የቋሚ ሰብሎች ኢንቨስትመንትን የሚያበረታታ መመሪያ መውጣቱ ዘርፉን ጠቅሟል፡፡

ይሁን እንጂ በፌዴራልም ሆነ በክልል ደረጃ የወጡት አዋጆችና ደንቦች ወደ መሬት ሲወርዱ በሚመለከታቸው ወገኖች ላይ ምን ዓይነት አዎንታዊና አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳመጡ ለመገምገም የተደረገ ጥናት አለመኖሩ እንደ ጉድለት ሊታይ ይችላል፡፡

ስለዚህ አንድ አዋጅም ይሁን ደንብ ስራ ላይ ሲውል የባለሀብቶችን ሥራ በማስፋፋት ረገድ፣ የአገልግሎት አሰጣጥን ከማቀላጠፍና በአጠቃላይ የአፈጻጸም ችግሮችን ከመቅረፍ አንፃር የሚኖረውን ፋይዳ በማጥናት ችግር ያለበትን በማሻሻል እገዛ ማድረግ በቀጣይ ያስፈልጋል፡፡

### 3.1.3. የአንድ ማዕከል አገልግሎት አሠጣጥን በተመለከተ

ባለሀብቶች የኢንቨስትመንትና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ፍቃዶችን በሚያወጡበት ወቅት ወደ ተለያዩ መ/ቤቶች በመመላለስ ጊዜያቸውንና ገንዘባቸውን እንዳያባክኑ የሚያግዘውን የአንድ ማዕከል አሠራር /ፈቃድ መስጠትን በተመለከተ/ የክልሉ ኢንቨስትመንት መ/ቤት ከሴክተር መ/ቤቶች ውክልና በመውሰድ ተግባራዊ ማድረግ የጀመረው በ1988 ዓ/ም ነው፡፡ መ/ቤቱ ይህንን የአንድ ማዕከል አገልግሎት በዚያ ወቅት መጀመሩ ከሌሎች ክልሎች በግንባር ቀደምትነት አስፈርጆት ስለነበር ሁሉም ክልሎች ወደ መ/ቤቱ መጥተው ልምድ ቀስመዋል፤ ባለሀብቶችንም ከሞላ ጎደል ጠቅሟቸዋል፡፡ ነገር ግን አሠራሩ ላይ ሁለት ጉድለቶች ነበሩት አንደኛው የሴክተር መሥሪያ ቤቶች የአንድ ማዕከልን ጠ ቀሜታ በተመለከተ የጋራ ግንዛቤ ጨብጠው አምነውበትና ለሥራውም የሚያደርጉትን እገዛ ተረድተው ሳይሆን ውክልናውን የሰጡት በደብዳቤ ታዘው ስለነበር ለኢንቨስትመንት ቢሮ ባላቸው አመለካከት ላይ ችግር ነበረበት፡፡ በተለይ #ሥራዎችን ጠቅልሎ ስለወሰደ ማንኛውንም ሥራ እራሱ ይወጣው’’ የሚል አስተሳሰብ እየጎላ መጥቶ ነበር፡፡ ይህ አስተሳሰብ ደግሞ ኢንቨስትመንቱን ለማስፋፋት በሚደረገው ቅንጅታዊ ሥራ ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር ችሏል፡፡ ሁለተኛው ጉድለት የአንድ ማዕከሉ አሠራር ማዕከል ያደረገው ፈቃድ ነክ ጉዳዮችን ብቻ ስለነበር ከፈቃድ በኋላ ያሉት አገልግሎቶች በተለይ የመሬት ጉዳይ በተመለከተ ግምት ውስጥ የገባ ስላልነበረ አብዛኛዎቹ

ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት ፈቃድ አሰጣጡ የፈካው ፊታቸው በመሬት አሰጣጡ ሂደት ይጠቁር ስለነበር የአንድ ማዕከል አሰራሩ በሁለት እግሩ መቆም ያልቻለ ነበር፡፡

በሌላ በኩል በገጠር መሬት አቅርቦት ረገድ በአሰጣጡ ላይ የሚሳተፉ አካላትን ብዛትና የአሰጣጥ ሰንሰለቱን ለማሳጠር ይቻል ዘንድ የመሬት የጋራ ኮሚቴ በሚል ተቋቁሞ/ በደንብ ቁጥር 2/90 መሠረት/ ሥራውን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡

ይህ አሰራር መነሻ ያደረገው ፈጣን አገልግሎት መስጠትን ቢሆንም አሠራሩን የራሱ የሆነ ችግር በሂደት እያነቀው መጥቷል፡፡ በተለይ የኮሚቴው አባላት በተደራራቢ ኃላፊነትና ሥራ ከመጠመድ የተነሳ በስብሰባ ያለመገኘት፣ ቀልጣፋ ውሳኔ ያለመስጠትና አሠራሩን ቀጣይ የሚያደርግ ግልጽና ተጠ ያቂነትን ያሰፈነ ሥርዓት አለመኖሩ እንደ ችግር የሚወሰዱ ናቸው፡፡

የመሬት መለካት ስራን በተመለከተ የኢንቨስትመንት መ/ቤትም በሚሰጠው አገልግሎት መሬት በግምት ይሰጥበት የነበረውን አሰራር በመቀየሩ ለመሬት ኪራይ አከፋፈልም ይሁን የመሬት ሀብቱን መጠን ከማወቅ አንፃር ጠቀሜታ አትርፏል፡፡ ነገር ግን አልፎ አልፎ የመሬት መለካቱ ሥራ በባለሀብቱና በኢንቨስትመንት መ/ቤት ተሳትፎ ብቻ ይከናወን ስለነበርና በዞንና በወረዳ ደረጃ የሚመለከታቸው ወገኖች አለመሳተፍ በአፈጻጸም ረገድ ውጣ ውረዶች ለመከሰት መንስኤ ነበር፡፡

## 3.1.4. የፕሮጀክት ክትትል ሥራዎችን በተመለከተ

በኢንቨስትመንት መ/ቤት በኩል ይከናወኑ የነበሩት የፕሮጀክቶች ክትትል ሥራዎች ሁለት ፈርጆች ነበሯቸው፡፡ ይኸውም ቅድመ ፈቃድና ድህረ ፈቃድ የክትትል ሥራ ሲሆን ባለሀብቶች የሥራ ፈቃድ ከማውጣታቸው በፊት ፈቃድ ለማግኘት በተለይ የቡና መፈልፈያና ማበጠሪያ ፈቃድ ለማግኘት የፕሮጀክቶቹን ብቃት በመስክ በመሄድ የሚታይበት ሲሆን በሌላ በኩል ፈቃድ የተሰጣቸው ፕሮጀክቶች የሚገኙበት ደረጃ፣ ያጋጠሟቸውን ችግሮች፣ ከቀረጥ ነፃ ያስገቡአቸው መሣሪያዎች በአግባቡ ሥራ ላይ ስለመዋላቸው መረጃ የሚሰበሰብበት፣ የሚተነተንበትና ለውሳኔ ሰጪ አካል በማቅረብ አግባብነት ያለው ውሳኔ ለማሳለፍ ግብዓት የሚሆን መረጃ የሚገኝበት ነው፡፡

በዚህ መሠረት በርካታ የክትትል ጉብኝቶች ባለፉት አመታት ተከናውነዋል፡፡ የፕሮጀክቶች የእንቅስቃሴ ደረጃ በመገምገም ሥራ የማይሠሩትን በመለየት እርምጃ ለመውሰድ አስችሏል፡፡ የአፈጻጸም ችግሮችን በመቅረፍ ረገድም የጐላ አስተዋጽኦ ከማድረጉም በላይ ጉብኝቱ አልሚ ባለሀብቶች እንዲበረታቱ ዕገዛ አድርጓል፡፡

ሆኖም የክትትል ሥራው የራሱ ጉድለቶች የነበሩበት በመሆኑ የግሉን ኢንቨስትመንት ችግሮች ሊፈታ በሚችል መልኩ የተቃኘ አልነበረም፡፡ ጉድለቶችም በሁለት በኩል የታዩ ናቸው፡፡

### ሀ) በባለሀብቶች በኩል የታየ ጉድለት

በባለሀብቶች በኩል የነበረው ችግር ባለሀብቶቹ ጉብኝት እንደሚኖር የቅድሚያ መረጃ ቢሰጣቸውም በፕሮጀክቶቻቸው ሣይት ላይ ተገኝተው የሚፈለገውን መረጃ ያለመስጠትና በሳይት ላይ የተገኙትም ቢሆኑ የሚሰጡት መረጃ በየጊዜው ተመዝግቦ የተያዘ ሳይሆን ግምታዊ መሆኑ እንደችግር ታይቷል፡፡

### ለ) በቢሮው በኩል የታየ ጉድለት

በቢሮው በኩል ዋነኛ ችግር የነበረው ፕሮጀክቶቹ ባሉበት አካባቢ ካሉት አግባብነት ካላቸው መ/ቤቶች ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ባለመኖሩ ቢሮው ካለው የሰው ሃይል፣ የገንዘብና የቁሳቁስ ውስንነት አንፃር ሁሉንም ፕሮጀክቶች በመከታተል ለማዳረስ የተደረገው ጥረት በተፈለገው መጠን ውጤታማ እንዳይሆን አድርጐታል፡፡ በሌላ አንፃር ከየፕሮጀክቶቹ ተሰብስበው የሚመጡት መረጃዎች በየጊዜው በመረጃ ባንክ ውስጥ ገብተው የፕሮጀክቶቹን ወቅታዊነት ለማሻሻል ባለመዋሉ ስለፕሮጀክቶቹ ይዞት ግንዛቤ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደሩ አልቀረም፡፡ በተጨማሪ መጠቀስ ያለበት ችግር ክትትሉ በቁጥጥር (Control) መንፈስ እንጂ በድጋፍ መንፈስ (Care & Support) ያልተቃኘ መሆኑ ነው፡፡

### 3.1.5. የምክክር መድረኮችን በተመለከተ

የክልሉ መንግስት አስፈጻሚ አካላትን፣ ባለሀብቶችንና ሌሎች አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ባካተተ መልኩ በሚከሰቱ የአሰራር፣ የአፈጻጸምና ፖሊሲ ችግሮች ላይ በየዓመቱ የሚወያይ የፓናል ውይይት ሲደረግ ቆይቷል፡፡ በዚህ ውይይት ወቅት ባለሀብቶች ችግሮቻቸውን በቀጥታና በግልጽ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት የሚያቀርቡበትና አሠራሮች እንዲሻሻሉ የመፍትሔ አቅጣጫዎች የሚያመላክቱበት በመሆኑ መቀራረብንና መተማመንን የፈጠረና መበረታታትም ያለበት መድረክ ነው፡፡ ከፖናል ውይይቶቹ ጋር በተጓዳኝ እየተከናወነ የነበረው የኢንቨስትመንት ፎረም ነበር፡፡ ይህ ፎረም በዞንና በክልል ደረጃ የሚከናወን ነበር፡፡ በአባልነት አቅፎአቸው የነበሩት ከየሴክተሩ ኢንቨስት ካደረጉ ባለሀብቶች የተወከሉ ባለሀብቶች የመንግስት አስፈጻሚ አካላት፣ የመንግስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትና አግባብነት ያላቸው የሴክተር መ/ቤቶችን በማካተት የሚደረግ ስብሰባ ነው፡፡

በክልል ደረጃ በነበረው የፎረም ስብሰባ የባለሀብት /የሴክተር/ ወኪሎች በየሴክተራቸው የነበሩትን የአሰራርና የሕግ ችግሮችን በጥልቀት የሚወያዩበትና ብዙ አመርቂ ውጤቶች የታዩበት ነበር፡፡ በነዚህ የስብሰባ ወቅቶች ከሚከሰቱ ዋና ዋና ችግሮች ሳይጠቀስ የማይታለፍ ጉዳይ የሴክተር መ/ቤቶች ለስብሰባው ትኩረት ባለመስጠት በፎረሞቹ ላይ የማይገኙበት ሁኔታ አልፎ አልፎ መከሰቱ ነው፡፡ ይህ

በመሆኑ ከሴክተር መ/ቤቶች በኩል በፎረሙ በሚነሱ ጉዳዮች ላይ የግንዛቤ ጉድለትና የሚጠበቅባቸው የመፍትሔ አቅጣጫ ላይ የሚያበረክቱትን አስተቃጽኦ ጎደሎ አድርጎታል፡፡

### 3.1.6. መሬት የመለካት ሥራዎችን በተመለከተ፣

የእርሻ ኢንቨስትመንት መሬትን ለባለሀብቶች ለክቶ መስጠቱ ተገቢ የመሬት ኪራይ ማስከፈል እንዲቻልና ባለሀብቶች የባለይዞታነት ስሜት እንዲያድርባቸው በማድረግ መተማመንን የሚያጎለብት ተግባር ነው፡፡ በዚህ መነሻ እስከአሁን ድረስ በትንሹ 37,373 ሄ/ር በባለሀብቶች ይዞታ ስር ያለ የእርሻ መሬት ተለክቶ ለተወሰኑት ካርታ የተሰጠ ሲሆን ለሌሎች ሳይሰጥ ያለበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡

በሌላ መልኩ በአለካክ ወቅት የተለያዩ የአሰራርና የአፈጻጸም ችግሮች ተከስተዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ በዋነኛነት የሚጠቀሰው በመሬቱ ጉዳይ ላይ አግባብነት ያላቸው የዞን መስተዳድር አካላት ባለሀብቱንና የኢንቨስትመንት መ/ቤትን በእኩል ደረጃ ያሳተፈ አልነበረም፡፡ በአብዛኛው መሬቶቹ ሲለኩ ባለሀብቱ በሚጠይቀው መሠረት ቢሮው ባለሙያዎች ወደ ቦታው ልኮ ይፈጸማል፡፡ ሆኖም ግን በዞን ደረጃ ከሚመለከታቸው አካላትና ከወረዳ እስከ ቀበሌ ድረስ ባሉት አካላት በቅንጅት የማይሰራ ስለነበር በተለያዩ አካባቢዎች ተለክተው በነበሩት የኢንቨስትመንት መሬቶች ላይ ጭቅጭቆች እና አለመግባባቶች እንዲሁም ጥርጣሬዎች መከሰታቸው አልቀረም፡፡

### 3.1.7. የመረጃ አደረጃጀት ሥርዓትን በተመለከተ

የኢንቨስትመንት መ/ቤት መረጃዎችን በሁለት ፈርጆች ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው ፈቃድ ወስደው በተለያየ ደረጃ የሚንቀሳቀሱ ባለሀብቶችን አጠቃላይ ሁኔታ የሚያሳይ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የክልሉን የኢንቨስትመንት አማራጭ ዕድሎችን የሚገልጽ መረጃ ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት መረጃዎቹ በጽ/ቤቱ ውስጥ ያሉበት ሁኔታ ሲዳሰስ፣ የባለሀብቶች እንቅስቃሴን የሚገልጹ መረጃዎች በተወሰነ ደረጃ ፕሮጀክቶቹ ያሉበትን ወቅታዊና ተጨባጭ ሁኔታ የሚያሳዩ ቢሆንም በየጊዜው በሚደረግ የመስክ ክትትል ሪፖርቶች አማካኝነት በሚጠበቀው ሁኔታ ወቅታዊ የተደረጉ አይደሉም፡፡ ለምሳሌ እንቅስቃሴ ካቆመ ከሁለትና ከዚያ በላይ አመታት ያለውን ፕሮጀክት የካፒታል መጠኑና ሊፈጥር ያለመውን የሥራ ዕድል ዛሬም በእንቅስቃሴ ላይ እንዳለ ፕሮጀክት ተደርጎ መረጃው ተይዞ የሚታይበት ሁኔታ አለ፡፡ ስለዚህ እያንዳንዱ ፕሮጀክት ያለበት ወቅታዊ ሁኔታ ተፈትሾ ዳታ ቤዙ በመ/ቤት ደረጃም ይሁን በሰለጠነ ባለሙያ መስተካከልና በቀጣይነት መሻሻል አለበት፡፡

የክልሉ አጠቃላይ ገፅታና የኢንቨስትመንት አማራጭ ዕድል መረጃዎችን በተመለከተ በዳታ ቤዝነት ካለመያዛቸውም በላይ በመ/ቤት ደረጃ በባለቤትነት የት ማን ዘንድ እንዳሉ ሳይታወቅ ተበታትነው የሚገኙበት ሀኔታ ነው ያለው፡፡ ይህ የመረጃ ዘርፍ ለቢሮው ህልውና ወሳኝ ሆኖ ሳለ በአሰባሰብ፣

በአደረጃጀትና በአያያዝ ረገድ ጉድለት ያለበት ነው። ስለዚህ ስትራቴጂያዊና ወዲያውኑ ጥቅም ላይ የሚውሉትን በመለየት እንደየዞኖችና ወረዳዎች ንፅፅራዊ ተወዳዳሪነት ጠቀሜታ እንዲሁም ክልላዊ የልማት ራዕይን በማሳካት ረገድ ግንባር ቀደም ሚና የሚጫወቱ የልማት ዓይነት መረጃዎችን በማጠናቀር የአሠራር ሥርዓቱን ወደ ኮምፒውተር በመቀየር ቀጣይነት ባለውና ወቅታዊ በሆነ መልኩ ጥቅም ላይ ውሎ ውጤት በሚያመጣበት መልኩ መደራጀት ይኖርበታል። ይህ ካልሆነ ግን ባለሀብቶች መረጃውን በሚጠይቁበት የጊዜ፣ የመጠን፣ የመረጃ አይነትና ጥራት እንዲሁም ተጨባጭነት ማስተናገድ ካለመቻሉም በላይ በመረጃ መረብ ላይ ሲሰራጭም ከግምት በታች የሆነ ግንዛቤ ሊያሳድር ይችላል።

በተጨማሪም በክልሉ ውስጥ የተሰማሩ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች መረጃ አዳዲስ ባለሀብቶችን ወደ ክልሉ ሊስቡ በሚችሉበት መልክ ለማስተዋወቅ እንዲያስችሉ የጂኦግራፊያዊ አቀማመጥን መሠረት ያደረገ /GIS/ በመረጃ መረብ ለመሰራጨት በሚያስችል መልኩ መደራጀት ያስፈልጋቸዋል።

### 3.2. የግሉ ኢንቨስትመንት ልማት መሠረታዊ ችግሮች

ከላይ በተመለከተው መሠረት በአገር አቀፍ ደረጃ የግሉን ኢንቨስትመንት ለማበረታታት በተቀመጠው አቅጣጫ መነሻነት የክልሉ መንግሥት ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ለማበረታታት ዘርፈ ብዙ ጥረቶችን ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ከነዚህም ጥረቶች መካከል ጥቂቶቹ የግል ኢንቨስትመንት ጉዳዮችን በኃላፊነት የሚከታተልና ተገቢ ድጋፍ የሚሰጥ ተቋም መፍጠር፣ የክልሉን የኢንቨስትመንት አዋጅና የገጠር መሬት ደንብ ማዘጋጀት፣ የክልሉን ፅምቅ ሀብት መረጃ በማዘጋጀት በአገር ውስጥና በውጭ ላሉ ባለሀብቶች የማስተዋወቅ ሥራ መሥራት፣ በሪፎርም ከተሞች የተሟላ የመሠረተ ልማት ዝርጋታ የተዘረጋባቸው የኢንዱስትሪ መንደሮች ዝግጅት፣ በኢንቨስትመንት አፈጻጸም ዙሪያ ለሚያጋጥሙ ችግሮች አፋጣኝ መፍትሔ የሚያፈላልግ ክልላዊና የዞን ኢንቨስትመንት ፎረም ማቋቋም፣ ለባለሀብቶች በቅርበት ድጋፍ የሚሰጡ የዞን ኢንቨስትመንት ዴስኮች ማቋቋም፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎት አቅርቦት አሠራር መጀመር ወዘተ ናቸው፡፡

እስካሁን በተደረጉ ጥረቶች የክልሉ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ከተቋቋመበት ከየካቲት 1986 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30/1999 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ 3125 ባለሀብቶች በክልሉ በተለያዩ የኢንቨስትመንት ልማት መስኮች ለመሠማራት ፈቃድ ወስደዋል። ፈቃድ የተሰጣቸው ፕሮጀክቶች 22 ቢሊዮን ብር ካፒታል በማስመዝገብ ወደ ክልሉ የገቡ ሲሆን አገልግሎት መስጠት ሲጀምሩ ለ 450,039 ቋሚና ጊዜያዊ ሠራተኞች የሥራ ዕድል ይፈጥራሉ። ከጠቅላላ ባለሀብቶች መካከል 149 ፕሮጀክቶች የውጭ ባለሀብቶች በተናጠልና በጋራ የተሰማሩበት መስክ በመሆኑ እነዚሁ ባለሀብቶች የውጭ ምንዛሪ ገቢን በመጨመር ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳደረጉ ይታመናል።

የግሉን ኢንቨስትመንት ለማስፋፋት ከፍ ብሎ በተመለከተው መሠረት የተለያዩ ጥረቶች የተደረጉና የተወሰኑ ውጤቶች የተገኙ ቢሆንም ዘርፉ በክልሉ የልማት እንቅስቃሴ የሚጠበቅበትን ሚና በአግባቡ መጫወት እንዲችል ከማድረግ አንፃር ጊዜ ሣይሰጥባቸው መቀረፍ የሚገባቸው ችግሮች ቀጥሎ በዝርዝር ቀርበዋል፡

## 3.2.1. ከባለሀብቱ አንጻር የሚታዩ ችግሮች

የክልሉ የግል ኢንቨስትመንት ጠንካራ ጎኖች እንደተጠበቁ ሆነዉ ደካማ ጎኖችና ዘርፉን ያጋጠሙ ችግሮችም አሉ፡፡ ባለሀብቶችን ስላጋጠሟቸዉ ችግሮች በማንሳትና ደካማ ጎኖችንም በመጠቆም ከባለሀብቶች ጋር በሚደረግ ውይይትና በመንግስት ድጋፍ ችግሮችን መቅረፍ ይቻላል፡፡ በጣም በርካታ የኢንቨስትመንት ችግሮችን መጥቀስ የሚቻል ቢሆንም ዋና ዋና የሆኑት እንደሚከተለው ቀርበዋል ፡፡

### ሀ. የፕሮጀክት ማኔጅመንት ችግሮች

የኢንቨስትመንት ፈቃድና በገጠር ሰፋፊ የእርሻ መሬት የተሰጣቸዉ ባለሀብቶች የተሰጣቸዉን መሬት በዘመናዊ የእርሻ ዘዴ እንደሚያለሙና ከአርሶ አደሩ የተሻለ ማኔጅመንት እንደሚኖራቸዉ ይጠበቃል፡፡ ነገር ግን በተግባር የታየዉ ተሞክሮ ከዚህ የተለየ ነዉ፡፡ በንጽጽር ጥቂት ጠንካራ ባለሀብቶች ቢኖሩም የአብዛኞዎቹ ፕሮጀክት ማኔጅመንት ደካማ ነው፡፡

### ለ. በስትራቴጂክ ዕቅድ አለመመራት ችግር

አብዛኛዎቹ ፕሮጀክቶች በዕቅድ አይመሩም፣ እንዲያዉም የዕቅድ አስፈላጊነቱንም የተረዱ የማይመስሉ አሉ፡፡ ዓመታዊ የዕቅድ ዶክመንትና የእንቅስቃሴ መረጃዎችን አይይዙም፣ መዛግብትም የሏቸውም፣ የረባ የጽሕፈት ሥራና መዛግብት ማስቀመጫ ቢሮዎች እንኳ በየጣቢያዎቹ የሌሉም አሉ፣ ይህንንም የሚያከናውኑና የሚከታተሉ ድጋፍ ሰጪ ባለሙያዎች የሏቸዉም፡፡ ይህም በመሆኑ ከጊዜ አንጻር ኢንቨስትመንቱ ለዉጥ እንዳመጣላቸዉ ወይም እንዳላመጣ፣ ትርፋማ ወይም አክሳሪ ስለመሆኑ በተጨባጭ መረጃ የተደገፈ ኢንፎርሜሽን ስለሌላቸዉ ከየት ተነስተዉ የት ሊደርሱ እንዳሰቡ የሚያሳይ ግልጽ ራዕይ የላቸዉም፡፡ በአጠቃላይ የፕሮጀክቶቹ በዕቅድ የመመራት ሁኔታ እጅግ ደካማ ሆኖ ይገኛል፡፡

### ሐ. የገበያ ጥናት አለማድረግ ችግር

አብዛኛዎቹ ፕሮጀክቶች ስለገበያ ሁኔታ በቂ ጥናት ሳያደርጉና ሰፊ ገበያ ዉስጥ ለመግባት የሚያስችሏቸዉ ዕድሎችን አሟጠዉ ሳይጠቀሙበት በቴክኒካል የማምረት ሥራዎች ላይ ብቻ

ያተኩራሉ፡፡ ለምርቶቻቸው/ አገልግሎቶቻቸው ምቹ ገበያዎች ያሉበት ቦታ፣ የገበያዎችን ፍላጎት አስቀድመው የማወቅና የማስጠናት፣ ስለምርት መጠን ብቻ ሳይሆን ስለምርት ጥራት አውቆ አለመስራት፣ በአካባቢያቸዉ ያለዉን ገበያ አሟጠዉ አለመጠቀም፣ ትኩረት በሚሰጥባቸዉ የወጪ ምርቶች ላይ አለማተኮር፣ ለዉጭ ገበያዎች ወይም ለሀገር ዉስጥ ተቀባዮች በጥራት፣ በተፈለገዉ ጊዜና በተፈለገው መጠን የማቅረብ፣ የመወያየትና የመደራደር፣ ኮንትራት የመዋዋል አቅማቸው ደካማ መሆኑ የተወዳዳሪነት አቅማቸዉም አነስተኛ እንዲሆን አድርጓል ፡፡

### መ. የሰለጠነ የሰው ኃይል ያለመጠቀም ችግር

በክልሉ ከሚገኙ የግል ኢንቨስትመንቶች መካከል እጅግ በርካታዎቹ ፕሮጀክቶች በሙያተኛ የሚመራ ማኔጅመንት የላቸዉም፡፡ በአብዛኛው ባለሀብቶች የሚቀጥሯቸው የሰው ኃይል በልምድ ያካበቱት ዕውቀት እንጂ የትምህርት ዝግጅት የሌላቸውን ጥቂት ሠራተኞች ሲሆን እነዚህን በጊዜያዊነት ከመቅጠር ባሻገር ሌላ የሰዉ ኃይል አቅርቦት ባለመኖሩ በተለይ በገጠር ትልቁንና ፈታኙን የግብርና ሥራ በእነኝህ ሠራተኞች ብቻ በሁለገብነት ለማከናወን ሲጣጣሩ ይታያሉ፡፡ ይህም በመሆኑ በሰዉ ኃይል አቅርቦት ላይ የመጠን ብቻ ሳይሆን የጥራት ችግር አለባቸዉ፡፡

### ሠ. የጥገኝነት አስተሳሰብ መበራከት ችግር (Parasitic Thinking)

በአንዳንድ ባለሀብቶች ዘንድ የሚታየው የጥገኝነት አስተሳሰብ ችግር በክልሉ እንደ አንድ የኢንቨስትመንት ችግር የሚቆጠር ነዉ፡፡ ምንም የማልማት አቅም ሳይኖራቸው መሬት ተረክበው ገና ለገና የፕሮጀክት ፋይናንስ የሚያፈላልጉና በመሬት ሽሚያ ተግባር ዉስጥ የተሰማሩ እንዲሁም የተረከቡትን መሬት ራሳቸው በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በማልማት ፈንታ ከአካባቢው አርሶ አደር ትርፍ የጋራ አይነት ድብቅ ግንኙነት በመመስረት የጥንቱን የመሬት ከበርቴ ሥርዓት የሚመስል አሠራር የሚያራምዱም አሉ፡፡ ከዚህም ሌላ የራሳቸዉን ጉድለትና ድክመት በአካባቢዉ የዞን ወይም የወረዳ አስተዳደሮች ወይም ሌሎች የመንግስት አስፈጻሚ አካላት ላይ የሚያላክኩና አስተዳደራዊ በደል እንደደረሰባቸው በማስመሰል የሚያማርሩ፣ አቤቱታ ይዘው ላይ ታች የሚሉም አልታጡም፡፡

ባለሀብቶች መንግስት ባመቻቸላቸው ማበረታቻዎች ተጠቃሚ የመሆን መብት እንዳላቸዉ ሁሉ በሀገሪቱ ሕግና ለባለሀብቶች ስለሚውል የገጠር መሬት ደንብ በሚደነግገዉ መሠረት የመሬት ኪራይ ዉል የመግባት፣ የገቡትን ዉል በፍትህ አካላት የማስመዝገብ፣ የተከራዩትን መሬት በወቅቱና በአግባቡ የማልማት፣ ማልማት ካቃታቸው ደግሞ መንግሥትን አመስግነው መሬቱን የመመለስ፣ በወቅቱ የመሬት ኪራይና የገቢ ግብር በወቅቱ ቀርበዉ የመክፈል ግዴታዎች

አሉባቸዉ፡፡ከግል ባለሀብቶች ከሚጠበቁ መንግስታዊና ሀገራዊ ግዴታዎች መካከል አንዱ የመሬት ኪራይንና የገቢ ግብርን አሟልቶ በወቅቱ የመክፈል ግዴታ ነው፡፡ ነገር ግን የመሬት ኪራይ ዉል ያልገቡና ኪራይ የማይከፍሉ ከመኖራቸውም በላይ ውል የገቡትም ቢሆኑ ከጥቂቶቹ በስተቀር ያለውጣ ውረድ አስበዉና አቅደዉ ኪራይ በወቅቱ ስለማይከፍሉ መንግስት ከዘርፉ ማግኘት የሚገባውን ገቢ በመሰብሰብ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ልማት እንዳያፋጥን አሉታዊ ሚና ይጫወታሉ፡፡

ከግል ኢንቨስትመንት ጋር በተያያዘ በአንዳንድ ዞኖች ውስጥ በሚገኙ አካባቢዎች የወንዞች ብክለት በተደጋጋሚ የታየ ችግር ሆኗል:: የእሸት ቡና ማዘጋጃ ፕሮጀክቶች ግንባታ በወንዝ ዳርና ተዳፋት በሆኑ መሬቶች ላይ እንዲሆን ስለሚፈቀድ በዚህ አይነት ሁኔታ ከኢንዱስትሪዎቹ የሚወጣዉ ዕጣቢና ገለባ ቀጥታ ወደ ወንዞች እየተለቀቀ ብክለት በማስከተሉ የቡና ጥራትን መጉዳት ብቻ ሳይሆን ለሰውና ለቤት እንስሳት ጭምር የጤና ችግሮች መንስኤ ሆኗል::

ይህንን ችግር ከጅምሩ ለመከላከል እንዲቻል በፕሮጀክት ዝግጅት ወቅት አስፈላጊ የሆኑ የግንባታ ዲዛይኖች የተዘጋጁና ፕላኖቹም ከፈቃዱ ጋር ተያይዘው የሚሰጡ ቢሆንም ባለሀብቶች ቋሚ የንግድ ስራ ፈቃድ እስከሚያወጡ ድረስ ብቻ በፕላኑ መሠረት እየሠሩ ከቆዩ በኋላ ቋሚ የንግድ ስራ ፈቃድ እንዳወጡ  የፕላኑን ተግባራዊነት ከወጪ አንጻር እያዩ የቡና ዕጣቢ ቆሻሻን በጨለማ ወይም የሚያያቸዉ አካል የሌለበትን ወቅትና ጊዜ እየጠበቁ በቀጥታ ወደ ወንዞች ይለቃሉ::

### 3.2.2. ከአገልግሎት አቅርቦት አንጻር ያሉ ችግሮች

#### ሀ. ቢሮክራሲያዊ ውጣውረድ

በክልሉ ምንም እንኳን ከኢንቨስትመንት አፈጻጸም ጋር ተያይዘው ያሉትን ችግሮች በማሻሻል የኢንቨስትመን እንቅስቃሴውን ለመደገፍ ጥረት እየተደረገ ያለ ቢሆንም ቀደም ሲል ተንሰራፍቶ በቆየው የአገልጋይነት ሳይሆን የተገልጋይነት ስሜት የተነሳ በአንዳንድ አካባቢዎች የኢንቨስትመንት መሬት ጠይቀዉ ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ለመግባት ጥረት የሚያደርጉ ባለሀብቶችን በተለያዩ የአፈጻጸምና አስተዳደራዊ/ቢሮክራሲያዊ ውጣ ውረዶች የማስቸገር፣ በመሬት ጉዳዮች ላይ ለባለሀብቶች የመሬት ርክክብ ከተፈፀመም በኋላ ሌላ ሦስተኛ ወገን ጣልቃ መግባት ይታያል፡፡ በመሆኑም ባለሀብቶች ለአላስፈላጊ አቤቱታና እንግልት ይዳረጋሉ፡፡ ይህ የሚያንፀባረቀዉ በየደረጃው የሚገኘው ለባለሀብቶች ድጋፍ የሚሰጠው አስፈጻሚ አካል በሆኑ አንዳንድ የመንግስት አስፈፃሚ አካላትና ተቋማት ለባለሀብቶች በቅድሚያ ድጋፍ ከመስጠት ይልቅ ባለሀብቶችን የመከታተልና የመቆጣጠር ሚናን በማስቀደም የሚንቀሳቀሱ መሆኑ በአንዳንድ አካባቢዎች ስለሚስተዋል ይህ ሁኔታ ልንቀርፋቸው የሚገቡ የመልካም አስተዳደር ችግሮች መኖራቸውን ያሳያል ፡፡

## ለ. የመሬት ነክ መረጃ አቅርቦት ችግሮች

በክልሉ በሚገኙ ዞኖች በገጠር መሬት ኢንቨስት ለሚያደርጉ ባለሀብቶች መሬት ሲሰጥና ውል ሲገባ የውሉን ግልባጭ በመሸኛ ደብዳቤ ለሚመለከታቸው አካላት ሲተላለፍ ለክልሉ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲም እንዲደርስ ያደርጋሉ፡፡ ይህ አሠራር ቋሚ አሠራር ሆኖ እስካሁን ስለሚሠራበት ለባለሀብት የተሰጠ የገጠር መሬት መረጃ በማግኘት በኩል በአብዛኛው ችግር የለም፡፡ ነገር ግን በገጠር ያለው የኢንቨስትመንት መሬት መረጃ ችግር የሚበዛው ለባለሀብት ሊውል የሚችል መሬት አዘጋጅቶ በቅድሚያ ያለማሳወቅ ላይ ነው፡፡ ይህ አሠራር የገጠር መሬትን አዘገጃጀትና አቅርቦት በፍትሐዊ መንገድ እንዳይከናውን ያደርጋል፡፡

በከተሞች ለባለሀብቶች የሚሰጥ መሬት መረጃን አስመልክቶ ያለው ችግር በመሬት ዝግጅትም ሆነ ለባለሀብቶች የተሰጠ መሬት መረጃን በአግባቡ ያለማሳወቅ ችግር ነው፡፡ ይኸውም በከተሞች አካባቢ ለኢንቨስትመንት ተግባር ተዘጋጅተው የሚገኙ ቦታዎች መረጃ ለኢንቨስትመንት አስፈጻሚ አካል የማይተላለፍ ከመሆኑም በላይ ለኢንቨስትመንት አገልግሎት እንዲውሉ የተሰጡ ቦታዎች መረጃ አግባብነት ባላቸው ሰነዶች ተደግፎ ስለማይተላለፍ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወስደው ወደ ከተሞች የሚሄዱ ባለሀብቶች አፈጻጸም በምን ደረጃ ላይ እንዳለ ተከታትሎ በማወቅ ድጋፍ ለመስጠት ያልተቻለበት ሁኔታ አለ፡፡

በከተሞች ለኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች የኢንዱስትሪ ዞን ተከልሎ መሰረተ ልማትም ተዘርግቶ መገኘቱ ጥሩ ጎን ሲሆን በኢንዱስትሪ ዞን የተሰማሩ ባለሀብቶች የመሬት መረጃ በአግባቡ ስለማይተላለፍ የመሬት አጠቃቀም ምን ደረጃ ላይ እንዳለ ለማወቅ የማይቻልበት ሁኔታ አለ፡፡

በአጠቃላይ የመሬት መረጃን በወቅቱ ያለማግኘት የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች አፈጻጸም በመከታተል ተገቢውን ድጋፍ ለማድረግ ማነቆ ሆኗል፡፡

## ሐ. ከደህንነትና ፍትህ አሰጣጥ አንጻር የሚታዩ ችግሮች

ባለሀብቶች ለኢንቨስትመንት ልማት በወሰዷቸው መሬቶችና ባፈሯቸው ንብረቶች ላይ ከህገወጥ ግለሰቦች ጋር ተያይዞ የዋስትናና ጥበቃ ክፍተት የሚታይ ሲሆን ባለሀብቶች ለደረሰባቸው በደል ፍትሕ በሚጠይቁበት ጊዜ ቀና ምላሽ ያለማግኘት ወይም መዘግየት ይታያል፡፡ ስለዚህ ለኢንቨስትመንት ሴክተሩ በተለየ ሁኔታ ፈጣን የሕግና የፍትህ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት ይኖርበታል፡፡

### 3.2.3. የመሠረተ-ልማትና የፋይናንስ አቅርቦት ችግር

### ሀ. የመሠረተ-ልማት አቅርቦት ችግር

የግሉን ኢንቨስትመንት በሚፈለገው መጠን ለማስፋፋት የመሠረተ ልማት አውታሮች ማለትም የመንገድ፣ ውሃ፣ መብራት፣ ቴሌኮሙኒኬሽን ወዘተ አገልግሎቶችን ማሟላት ወሳኝ ነው፡፡ በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ እንደሚታወቀው እነዚህ የመሠረተ ልማት ተቋማት የማሟላት ኃላፊነት የመንግሥት በመሆኑ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ የሚጠይቁ እንደሆኑ ይታወቃል፡፡ መንግሥትም ለዚሁ ትኩረት በመስጠትና ከፍተኛ በጀት በመመደብ እነዚህን ሥራዎች በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ ነገር ግን ካለው ፍላጎት አንጻር በተለይም የኢንቨስትመንት ፖቴንሻል ወደሚገኝባቸው አካባቢዎች በቀላሉ የሚያስገቡ የገጠር መንገዶች ባለመኖራቸው ክልሉ ያለውን ፖቴንሻል መጠቀም ካለመቻሉም በላይ አንዳንድ ባለሀብቶች ያመረቷቸውን የእርሻ ምርት ውጤቶች በወቅቱ ለገበያ ማድረስ አልቻሉም፡፡ በዚህም ምክንያት ለኪሳራ እየተዳረጉ ሲሆን አገሪቱም ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ጥቅም አጥታለች፡፡

ሌሎች የመሠረተ ልማት አውታሮችን በተመለከተ በአሁኑ ጊዜ ያለው ሁኔታ አበረታች ነው፡፡ ይሁንና ክልሉ ካለው ሰፋትና የገጠር መሬት ፖቴንሻል አንጻር ብዙ መሥራት ይጠበቃል፡፡

### ለ. የፕሮጀክት ፋይናንስ ችግር

በክልሉ ከተሰማሩ ባለሀብቶች መካከል አብዛኞዎቹ የፕሮጀክት ፋይናንስ ዕቅዳቸው ከባንክ በሚገኝ ብድር ላይ የተመሰረተ ሲሆን አብዛኞዎቹ የሚፈልጉትን የብድር አገልግሎት ያላገኙ ናቸው፡፡ በተለይ በክልሉ ምዕራባዊ ዞኖች የሚካሄደው ኢንቨስትመንት በቋሚ ተክሎች በመሆኑ በአብዛኛው ከአራት ዓመታት በፊት ምርትና ገቢ ስለማያስገኝ ከፍተኛ የስራ ማስኬጃ እጥረት ያጋጥማል:: ከዚህም ባሻገር በነዚህ አካባቢዎች የሚገኙ ነባር የቡናና ሻይ ተክል ፕሮጀክቶች የሰዉ ጉልበት ተኮር ኢንቨስትመንት በመሆናቸዉና ያለው የጉልበት ፍላጎት ከፍተኛ በመሆኑ ይህንን ችግር ከርቀት በማጓጓዝ ለማቃለል የትራንስፖርት አገልግሎት የተሟላ ስላልሆነ ለዚህ ግብአት የሚያስፈልጋቸው የስራ ማስኬጃ ወጪ በጣም ከፍተኛ ይሆናል:: በተመሳሳይ መልኩ የደረሱትን ምርቶች በወቅቱ በመሰብሰብ ወደ ማዕከላዊ ገበያ ለማጓጓዝ ከፍተኛ የትራንስፖርት ወጪ ስለሚጠይቅ የሥራ ማስኬጃ ፋይናንስ ፍላጎታቸውን ያንረዋል::

በግብርና ልማት ላይ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች በባንኮች በኩል እምነት ማጣትና ብድሩን ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን አዝማሚያ ጎልቶ ይታያል፡፡ በተጨማሪም ከአበዳሪ ባንኮች ብድር ለማግኘት የሚጠየቁ ዶክመንቶችና ቅድመ-ሁኔታዎች ብዙ ዕውቀትንና ሙያን የሚጠይቁ፣ ብዙ ውጣ ውረድም ያለባቸው፣

የዋስትና ማስያዣ ጥያቄዎች ከአብዛኛው ባለሀብት አቅም በላይ በመሆናቸው በአበዳሪ ባንኮች የብድር ፖሊሲና በብድር ፈላጊ ባለሀብቶች መካከል ትልቅ ክፍተት አለ ፡፡

## 3.2.4. ሌሎች ችግሮች

### ሀ. ከገበያ አለመኖር ጋር የሚያያዙ ችግሮች

የግሉ ሴክተር ራሱንና የክልሉን ኢኮኖሚ ለማሳደግ በሚያደርገው ጥረት ውስጥ በዘርፈ ብዙ ችግሮች የታጠረ ሲሆን ከነዚህም አንዱ የሚመረተውን ምርት ወይም አገልግሎት የሚጠቀም ሰፊ ገበያ ዕድል አለመኖር ተጠቃሽ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ምርቱን ለማምረት ከወጣው ወጪ በማይመጥን ዋጋ ለመሸጥ የሚገደድበት ሁኔታ ይስተዋላል፡፡ በተጨማሪም ከኢንቨስትመንት አንጻር በቂና ወቅታዊ የአገር ውስጥና የውጭ አገር የገበያ መረጃ የሚሰጥ አካል በአግባቡ ተደራጅቶ ባለመኖሩና ያለውንም ቢሆን ቀርቦ የመጠየቅ ባህል በባለሀብቶች በኩል ባለመዳበሩ ተጠቃሚ ያልሆኑበት ሁኔታ አለ፡፡ ስለዚህ ይህ ችግር የባለሀብቱ ቁልፍ ችግር መሆኑ ታውቆ መፍትሔ ሊፈለግለት የሚገባ ነው፡፡

### ለ. ከጉልበት ሠራተኞች ጋር የተያያዘ ችግር

ለግሉ ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆን ከሚያስፈልጉ ግብዓቶች አንዱ ሥራውን በብቃት መወጣት የሚችል የሰለጠነና የጉልበት ሥራ የሚሰራ የሰው ኃይል በብዛት መገኘት ነው፡፡ ከክልላችን ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ሲታይ በምዕራብ ዞኖች ለሚካሄድ የኢንቨስትመንት ልማት የሚያስፈልግ የሰው ኃይል በብዛት የሚገኘው በደቡባዊና ማዕከላዊ ቀጣናዎች ነው፡፡ ነገር ግን በነዚህ አከባቢዎች ያለው የሰው ኃይል ወደ ተጠቀሱት አካባቢዎች ተንቀሳቅሶ የመሥራት ፍላጎት ማጣት የተነሳ ፈቃደኛ ያለመሆን ሁኔታ ይታያል፡፡ ሥራው ባለበት አከባቢ በተለይ ተቀጥሮ መሥራት ለወንዶች እንደ ነውር የሚቆጠርበት ሁኔታ በስፋት ይታያል፡፡ ይህ ችግር ለረዥም ዘመናት የቆየ ችግር ከመሆኑ አኳያ በአንድ ጊዜ ለማቃለል የሚያስቸግር ቢሆንም ደረጃ በደረጃ ለመፍታት የግንዛቤ ማስጨበጫ ውይይቶችና ሌሎች ድጋፎች በማድረግ መፍትሔ ሊፈለግለት ይገባል፡

### ሐ. ችግሮችን የሚቀርፍ የአሠራር ሥርዓት ያለመኖር፤

ሌላው የሚታየው ክፍተት በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱትና ሌሎችም ችግሮች ሲከሰቱ አፋጣኝ ምላሽ መስጠት የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ባለመኖሩ ባለሀብቶች ለተለያዩ ውጣ ውረዶች ሲጋለጡ ይታያል፡፡በመሆኑም በክልል፣ በዞንና በወረዳ ደረጃ ችግሮች ከመከሰታቸው በፊትም ይሁን ከተከሰቱ በኋላ እየተከታተለ ፈጣን ምላሽ የሚሰጥ የአደረጃጀትና የክትትል ሥርዓት የሚዘረጋበት ሁኔታ መመቻቸት ይኖርበታል፡፡

# ክፍል አራት

## የግሉ ኢንቨስትመንት መስፋፋት በክልሉ የኢኮኖሚ ልማት የሚኖረው አስተዋጽኦና የትኩረት አቅጣጫዎች

### 4.1. የግሉ ኢንቨስትመንት መስፋፋት በክልሉ የኢኮኖሚ ልማት የሚኖረው አስተዋጽኦ

ይህ ክፍል #የግሉ ኢንቨስትመንት መስፋፋት በክልሉ ኢኮኖሚ ልማት ላይ ምን ፋይዳ ይኖረዋል? ; ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ይሰጣል፡፡

ክልሉ በርካ  የተፈጥሮ ሀብት ክምችትና ሥራን የሚወድ ህዝብ ያለው ሲሆን ይህ የተፈጥሮ ሀብት ለምቶ በጥቅም ላይ ባለመዋሉ የህዝቡ ኑሮ ደረጃ በጣም ዝቅተኛ ከመሆኑም በላይ በአንዳንድ አካባቢዎች በቂ የዕለት ጉርስ  ንኳን የማያገኝ የህብረተሰብ ክፍል ይገኛል፡፡ በተለይ ከድህነት ወለል በታች ያለው ህዝብ ቁጥር ቀላል አይደለም፡፡ ይህንን ሁኔታ በማይቀለበስ መልኩ ለመቀየር የልማት ኃይሎች ማለትም መንግሥት፣ ሰፊው ህዝብ እና የባለሀብቶች በቅንጅት መረባረብን ይጠይቃል፡፡

በተለይም የግሉን ዘርፍ ሚና በተመለከተ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ሰነድ ላይ #አገራችን አሁን የምትገነባው የኢኮኖሚ ሥርዓት የነጻ ገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት በመሆኑ የኢንዱስትሪ ተቋሞችን በማቋቋም የኢንዱስትሪ ዕድገታችን ሞተር መሆን ያለበት የግል ባለሀብት እንደሆነ ምንም የሚያጠራጥር ነገር የለውም ; በሚል በግልጽ ተቀምጧል፡፡ ከዚህ ሐሳብ የምንረዳው መንግሥት በገበያውና በግል ባለሀብቱ በአጥጋቢ ሁኔታ ሊሰሩ የማይችሉ ክፍተቶችን እየለየ በተመረጠ አኳኋን በጊዜያዊነት ጣልቃ በመግባት የሚሞላ መሆኑንና በሂደት ግን የግሉ ሴክተር ሥፍራውን የሚረከብ መሆኑን ነው፡፡

ስለዚህ ዕምቅ የተፈጥሮ ሀብት በማልማትና የህዝቡን ኑሮ ደረጃ በማሻሻል በኩል ወሳኝ ሚና የሚኖረው ህዝብ ራሱ ቢሆንም የግል ባለሀብቶችም ከፍተኛ ድርሻ አላቸው፡፡ ስለሆነም ተለይተው ከተቀመጡት የልማት ሀይሎች ውስጥ የግል አልሚ ባለሀብት አንዱና በልማት ሂደቱ ውስጥ ተኪ የሌለውን ሚና እንደሚጫወት አንጥሮ በማውጣት ይበልጥ ለማበረታታት ቁርጠኛ አቋም የተያዘበት ሁኔታ አለ፡፡

ይህን መነሻ በማድረግ አልሚው ባለሀብት ለክልሉ የኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋጽኦ የሚያበረክትባቸውን ሁኔታዎች ከገጠርና ግብርና ልማት ፣ ከኢንዱስትሪ ልማት ፣ የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ፣ ድህነትን ከመቀነስ እና በከተሞች የህዝቡን ኑሮ ከማሻሻልና ልማትን ከማፋጠን አኳያ ያላቸውን ሚና በዝርዝር መመልከቱ የዘርፉን ሚና በሚገባ ለመረዳት ያስችላል፡፡

## I. የዳበረ የነፃ ገበያ ሥርዓት ከመገንባት አንፃር ያላቸው አስተዋጽኦ

በነፃ ገበያ የኢኮኖሚ ሥርዓት መርህ የኢኮኖሚው ዋነኛ አንቀሳቃሽ ሞተር የግሉ ዘርፍና ባለሃብት ነው፡፡ በዚሁ ሰነድ ላይ የመንግሥት ሚና ለሀገር ኢኮኖሚ ድገት ቁልፍ የሆኑ ተቋማትን ከመገንባትና ከመምራት፣ በግሉ ዘርፍ ሙሉ ለሙሉ ወይንም በከፊል ሊቀርቡ የማይችሉ አገልግሎቶችን ከማቅረብ፣ ለልማት ምቹ የሆኑ ፖሊሲዎችንና ህጎችን ከማውጣት ና በአጠቃላይ የልማት ሃይሎችን ከማስተባበር የማያልፍ ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ በነፃ ገበያ የኢኮኖሚ ሥርዓት ከላይ ከተጠቀሱት ተግባራት ውጭ ያሉ ሥራዎች በሙሉ በግሉ ዘርፍና ባለሃብት የሚከናወኑ ይሆናሉ፡፡ ለዚህም ነው የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ዋነኛ አንቀሳቃሽ ሞተር የግሉ ባለሃብትና ዘርፍ ነው የሚባለው፡፡

በኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ላይ በዝርዝር ንደቀረበው ሀገራችን የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት በመገንባት ላይ መሆንዋ የሚ ወቅ ነው፡፡ በመሆኑም የግሉ ዘርፍና ባለሃብት ደረጃ በደረጃ በኢኮኖሚው ውስጥ ያለው ሚና ያደገ ንዲሄድና የመንግሥት ሚና ቁልፍ የልማት ተቋማትን በማስፋፋት፣ የገበያ ክፍተት ያለባቸውን ዘርፎች ለይቶ በመሙላት ና ለልማት ምቹ የፖሊሲና የሕግ ሁኔ በመፍጠር ላይ ንዲወሰን ጥረት የተደረገ ይገኛል፡፡

የዳበረ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት፣ የዳበረ የግል ዘርፍና ባለሀብት ከመፍጠር ውጭ ሊ ሰብ የሚችል አይደለም፡፡ ሀገራችን ከዚህ ቀደም ትከተለው በነበረው የሶሻሊስት ሥርዓት ምክንያት በሀገራችንም ሆነ በክልላችን የዳበረ የግል ዘርፍ ሊፈጠር አልቻለም፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን ሀገራችን የነፃ ገበያ ሥርዓትን ለመገንባት በም ደርገው ንቅስቃሴ ውስጥ የግሉ ዘርፍና ባለሃብት የተጠናከሩ ይገኛሉ፡፡

በክልላችን የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት የመገንባቱ ጥረት የዳበረ የግል ዘርፍና ባለሀብት ከመፍጠር ውጭ ሊ ሰብ የሚችል አይደለም፡፡ በመሆኑም በክልሉ የግሉን ዘርፍና ባለሀብት ለማጠናከርና ለማስፋፋት መጠነ ሰፊ ንቅስቃሴ ሊደረግ ይገባል፡፡ አሁን ካለንበት የክልላችን ተጨባጭ ሁኔ ለነፃ ገበያ ሥርዓት ግንባ መሰረት የሆነውን የግል ዘርፍና ባለሀብት በሚሊዮኖች መፍጠር ንዲሁም ቀልጣፋ ና ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል ማረጋገጥ የሚቻለው በክልሉ ውስጥ የግል ኢንቨስትመንትን በማጠናከርና በማስፋፋት ነው፡፡ የግል ኢንቨስትመንትን የነፃ ገበያ ሥርዓት ለመገንባት በሚደረገው ጥረት ውስጥ የካፒ ል፣ የሀብት፣ የቴክኖሎጂ ና የሥራ አመራር ዕውቀት ምንጭ በመሆን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረክ ል፡፡ በመሆኑም በክልላችን የሚካሄደው የዳበረ የነፃ ገበያ ሥርዓት ግንባ የዳበረ የግል ዘርፍና ባለሀብት ከመፍጠር ውጭ ሊከናወን ንደማይችልና የሚፈለገውም የግል ዘርፍና ባለሀብት በሥፋት ሊፈጠር የሚችለው የግል ኢንቨስትመንትን በማጠናከርና በማስፋፋት መሆኑን በመቀበል ሰፊ ንቅስቃሴ ሊደረግ ይገባል፡፡

## II. የገጠር ልማት ስትራቴጂ ዕውን ከማድረግ አኳያ

የልማታችን ዕምብርት የሆነውን የግብርናና የገጠር ልማትን ለማፋጠን የተነደፈውን ስትራቴጂ ዕውን በማድረግ አጠቃላይ ሀገራዊ የሆነ ሁለንተናዊ ዕድገት ማምጣት እንደሚቻል ዕሙን ነው፡፡ ይህንን ስትራቴጂ መንግሥት ብቻውን መተግበር ስለማይችል የተለያዩ የልማት አጋሮች ሚና ይፈልጋል፡፡

ስለዚህ ልማታዊ ባለሀብት በዚህ ረገድ ቀጥሎ የተጠቀሱትን ተግባራት በማከናወን ሚናውን ሊጫወት ይችላል፡፡

### ሀ. በምግብ ሰብል ራስን በማስቻል ረገድ

መሬት በስፋት ባለባቸው አካባቢዎች በመስኖ የታገዘ ሰብልን በስፋት በማምረት እንዲሁም የመሬት ጥበት ባለባቸው አካባቢዎች ከፍተኛ ዋጋ ባላቸውና ሰፊ መሬት በማይጠይቁ ልማቶች በመሰማራት አርሶ አደሩ ወደ ስፔሻላይዜሽንና ኮሜርሻላይዜሽን ማምጣት እንዲቻል ሞዴል በመሆን አርሶ አደሩ ገቢውን እንዲያሳድግና ራሱን እንዲችል በሚደረገው እንቅስቃሴ ላይ የግል ባለሀብቱ ከፍተኛ ሚና መጫወት ይችላል፡፡ በሚመረተው ምርት እሴት በመጨመርና ከገበያ ጋር በማገናኘት ለራሱም ተጠቅሞ የአርሶ አደሩን ገበያ ያሳድጋል፡፡

### ለ. ዘመናዊ አሠራሮችና ቴክኖሎጂዎችን ለገበሬው በማስተዋወቅ ረገድ

የባለሀብቶች ልማት ባለበት አካባቢ የሚገኙ አርሶ አደሮች ዘመናዊ የግብርና አሠራርን፣ ግብዓቶችን እና ቴክኖሎጂዎችን እንዲያውቁና እንዲጠቀሙበት የሚያስችል ዕድል ይፈጠራል፡፡ በዚሁም ምክንያት ምርታማነት ስለሚጨምር የአርሶ አደር ገበያና ገቢ ያድጋል፡፡ የባለሀብቱም የምርት ፍላጎት በአስተማማኝና በዘላቅነት ይረጋገጣል፡፡ ከደንበኞች ጋር በሚኖረው ግንኙነትም አስተማማኝ ሠንሠለት መፍጠር ይቻላል፡፡

### ሐ. ከአርሶ አደሩ ጋር የምርት ኮንትራትን በመዋዋል ረገድ

በአገራችንም ሆነ በክልላችን በአርሶአደሩና በባለሃብቱ መካካል ትስስሮችን ሊፈጥሩ ከሚችሉት ግንኙነቶች መካከል የምርት ኮንትራታዊ ትስስር (Outgrower Scheme) አንዱ ነው፡፡ ይህ ኮንትራታዊ አሰራር በአብዛኛው የመሬት ጥበት ባለባቸው ደጋማ የሀገራችን አካባቢዎች ቢሆንም በክልላችንም ተመሳሳይ ኮንትራታዊ ትስስር ሊተገበር የሚችልበት ዕድል አለ፡፡ በቡና፣ በሻይ፣ በቅመማቅመም፣ በጃትሮፓ (ለባዮ-ዲዚል የሚሆን ተክል) በአበባ ልማትና በሌሎችም የግብርና ዘርፎች በባለሃብቱ እገዛ አርሶአደሮች እነዚህን ምርቶች እንዲያመርቱና በኮንትራታዊ ትስስሩ መሰረት ጥራታቸውን ጠብቀው በማምረት ገበያ በማፈላለግ ጊዜአቸውን ሳያጠፉ በቀጥታ ለባለሃብቱ በመሸጥ ራሳቸውንም ሆነ

ባለሀብቱን የሚጠቀሙበት አማራጭና በዓለም ገበያም ተወዳዳሪ በመሆን የተሻለ ገቢ የሚያገኙበት ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

በዚህ ረገድ በክልላችን በስፋት መሥራትን የሚጠይቅ ሥራ የሚጠበቅ ሲሆን አሁን አለ ማለት የሚቻለው አርሶአደሩ ከባለሀብቱ የአሰራር ቴክኖሎጅ ሽግግርን (ምርጥ ዘርን፣በመስመር የመዝራት ልምድን፣ የባለሃብቱን ዘመናዊ የእርሻ መሣሪያዎች በኪራይ መጠቀም መቻልና የመሳሰሉትን) በመጠኑም ቢሆን ማግኘት የቻለባቸው አካባቢዎች ስላሉ ይህ ወደፊት ተጠናክሮ የሚቀጥልበት ሁኔታ በተጠና መልክ ተቃኝቶና ተጠናክሮ የሚቀጥልበት ሁኔታ እንዲፈጠር መደረግ አለበት፡፡ ከዚህም ሌላ ምንም እንኳን በስፋት እየተሰራበት ነው ባይባልም የባለሀብቶች ፕሮጀክቶች ባሉባቸው አካባቢዎች ፕሮጀክቶቹ ለአርሶ አደሩ መጠነኛ የሥራ ዕድል መፍጠር ከመቻላቸውም በላይ በመንግስት፣ በህዝቡና በባለሀብቱ ትብብር ወደ እነዚህ ፕሮጀክቶች የሚወስዱ መንገዶች ሥራ፣ የማህበራዊ አገልግሎት ተቋማት (ክሊኒኮች፣ ት/ቤቶችና የመሳሰሉት) ግንባታ ማካሄድ የተቻሉባቸው አካባቢዎች ይገኛሉ፡፡ ስለዚህ በትስስሩ ረገድ ገና ብዙ የሚቀሩ ሥራዎች ስላሉ ጉዳዩ የሚመለከታቸው በየደረጃው የሚገኙ አመራርና አስፈጻሚ አካላት፣ ባለሀብቱና አርሶአደሩ በቂ ግንዛቤ እንዲይዙ በማድረግ ትስስሩን ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡

### መ. ለአርሶ አደሩ አስፈላጊ ግብዓቶችን በማምረት/ ማቅረብ ረገድ፣

ባለሀብቱ ምርጥ ዘር በማባዛት፣ የእርሻ መሣሪያዎችን በማምረት/ በማቅረብ፣ ጸረ-አረምና ፀረ ተባይ መድሐኒቶችንና ማዳበሪያዎችን በማምረትና ለአርሶ አደሩ በማሰራጨት ረገድ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡

### ሠ. ተጓዳኝ ማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ ልማቶችን በማስፋፋት ረገድ

ባለሀብቶች በክልሉ በተለያዩ የገጠር አካባቢዎች ክሊኒኮች፣ ት/ቤቶች፣ ወፍጮ ቤቶች፣ የገጠር መንገዶች ፣ ምግብ ቤቶች፣ ከመንግስት ጋር በመተባበር የፖሊስ ጣቢያዎች፣ የገጠር መብራት አገልግሎት፣ ንጹህ የመጠጥ ውሃ በመገንባት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ይገኛሉ፡፡

## III. ከኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ አንፃር

የኢንዱስትሪ ልማት እንቅስቃሴ የተሳካ ሊሆን የሚችለው ልማታዊ ባለሀብት የኢንዱስትሪ ልማት ሞተር ሆኖ ሲያንቀሳቅሰውና መንግሥት ቁርጠኛ አመራር ሲሰጥ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ለኢንዱስትሪ ልማት መሳካት ወሳኝ የሆነውን ሀገራዊ የጋራ ርብርብ እውን ለማድረግ መንግሥትና ልማታዊ ባለሀብቱ ድርሻቸውን በየፊናቸውና በቅንጅት መወጣት መቻል አለባቸው፡፡ የግል ባለሀብቱም ከመንግሥት ጎን በመሆን በኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ረገድ በተለይ በአለም ገበያ በብቃት ተወዳዳሪ የሆኑ ሸቀጦችና አገልግሎቶችን አምርቶ በመሸጥ ልማትን የሚያረጋግጥ ክፍል ነው፡፡

እንደ የደ/ብ/ብ/ሕ/ ክልል ተጨባጭ ሁኔታ ስንመለከት ቡና፣ ቅመማ ቅመም፣ ማርና ሰም፣ ጥጥ፣ ጥራጥሬ፣ ቆዳና ሌጦ፣ ወተት የመሳሰሉት የግብርና ምርቶች የክልሉን ኢኮኖሚ በመደገፍ ተስፋ የሚጣልባቸው ምርቶች ናቸው፡፡ ከነዚህም ምርቶች ጋር ተያያዥነትና ተደጋጋፊነት ያላቸው ኢንዱስትሪዎች በተለይ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ከላይ የተገለጹትንና ሌሎች የግብርና ምርቶች በማቀነባበርና እሴት በመጨመር እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ ቴክኖሎጂዎችን አምርተው ለገበያ እንዲያቀርቡና በግብይት ተግባር ላይ እንዲሰማሩ በመንግሥት በኩል ምቹ ሁኔታዎችን ከመፍጠር አልፎ አስፈላጊ ድጋፎችን በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ በመንግሥት ሲነደፍ ግብርና መር የሆነ የኢንዱስትሪ ልማት ሥራ ሊሠራ የሚችለው ልማታዊ ባለሀብት ከመንግሥት ጎን በመሆን በሞተርነት ይህንን ክፍለ ኢኮኖሚ ሊያንቀሳቅስ እንደሚችል ታሰቢ በማድረግ ነው፡፡ በዚህ ረገድ አልሚው ባለሀብት ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ሚናዎች እንደሚጫወት ይጠበቃል፡፡

ሀ. ከፍተኛ የካፒታል መጠን በሚጠይቁ ኢንዱስትሪዎች በመሠማራት የቴክኖሎጂና የማኔጅመንት ክህሎትን ለሚቀጥረው የሠው ኃይል ያስተላልፋል፡፡

ለ. አለም የደረሰባቸውን የቴክኖሎጂ /መሣሪያዎች ዕውቀትና አሠራር/ ወደ ሀገሪቱ ብሎም ወደ ክልላችን በማሸጋገር ረገድ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

ሐ. በከተሞች አካባቢ ያለውን የሥራ አጥ ቁጥር እንዲቀንስ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

መ. መንግስት መሸፈን ባልቻላቸው የማህበራዊና ኢኮኖሚዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት በመሰማራት ለህብረተሰቡ ጥራት ያለው አገልግሎት ያቀርባሉ፡፡

ሠ. ከግብርናው ጋር የተቆራኘና ኤክስፖርት ላይ የተመሠረተ ምርት በማምረት ኢኮኖሚያችን በተሳሰረ መልኩ እንዲያድግ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

ረ. ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ሰብ ኮንትራክት በማድረግ የገበያ ማዕከልና የቴክኖሎጂ አሠራርን በተመለከተ ልምድ እንዲቀስሙ ያደርጋል፡፡

ሠ. የመንግስትን ገቢ በታክስና በሌሎች ተጓዳኝ ክፍያዎች ከፍ በማድረግ መንግስት ሌሎች የልማት ሥራዎችን እንዲያከናውን አጋዥ ኃይል ይሆናል፡፡

## IV. ለዘላቂ ልማትና ለድህነት ቅነሳ ያላቸው አስተዋጽኦ

በአገራችን ከሚታዩ መሠረታዊ ችግሮች ውስጥ ድህነት አንዱ ነው፡፡ ይህንንም መሠረታዊ ችግር በመቅረፍ ከድህነት ለመላቀቅ መንግሥት የተለያዩ ፖሊሲዎችንና ስተራቴጂዎችን ነድፎ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡ ከነዚህም ተግባራት ውስጥ አንዱ የግሉ ባለሀብት ከመንግሥት ጎን በመሆን በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማቱ በተለይ በድህነት ቅነሳ ረገድ ከፍተኛ ሚና በሚጫወቱ በግብርና፣ በኢንዱስትሪ፣ በትምህርትና ጤና ዘርፎች በሰፊው እንዲሳተፉ ምቹ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል፡፡ የግሉ ኢንቨስትመንት መስፋፋትና ማደግ በነፃ

ገበያ ወድድር በመሣተፍ ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት እንዲመጣና በተለይ ከፍተኛ የሰው ኃይል ጉልበት ተጠቃሚ የሆኑ የኢንቨስትመንት መስኮችን በማስፋፋት ተጨማሪ የሥራ ዕድሎች እንዲፈጠሩ በማድረግ በሀገሪቱ እየተካሄደ ያለውን የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ይደግፋል፡፡ በሚፈጠረውም የሥራ እድል በመስኩ የተሰማሩ ሰዎች የገቢ ሁኔታና የመግዛት አቅም በሂደት ስለሚሻሻል እንቅስቃሴው የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥና ድህነትን ለመቀነስ የሚደረገውን ጥረት በከፍተኛ ሁኔታ የሚደግፍ ሲሆን የህብረተሰቡ የኑሮ ደረጃ እንዲሻሻል በማድረግ በኩል ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡

## V. የክልሉን ሰፊ የተፈጥሮ ሀብት ጥቅም ላይ ከማዋል አንፃር

በክልሉ በባለሀብቶች ሊለማ የሚችል ሰፊ መሬት አለ፡፡ ከመሬት ጋር በተጓዳኝ የሚታየው የገፀ ምድር የውሃ ሀብት ነው፡፡ ክልሉ በርካታ ለመስኖ ፣ ለሀይል ማመንጨነትና ታሽጎ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል የውሀ ሀብት አለ፡፡ በአጠቃላይ 374,586 ሄ/ር በላይ በመስኖ ማልማት የሚችል አቅም ያላቸው ወንዞች እያሉ ከዚህ ውስጥ ተገድበው በባለሀብቶች ጥቅም ላይ ውሎ እየለማ ያለው የመሬት መጠን ከ5,600 ሄ/ር የሚበልጥ አይደለም፡፡
ከመስኖ ጠቀሜታቸው ባሻገር የክልላችን ወንዞች ለሀይድሮ ኤሌክትሪክ ሀይል ማመንጫነት ምቹ መሆናቸውን በርካታ ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡ በአጠቃላይ በተጠኑ ትናንሽ ወንዞች አማካኝነት 111.5 ሜጋ ዋት ሀይል ማመንጨት እንደሚቻልም የተረጋገጠ ሲሆን ከኦሞ ወንዝ ብቻ ግን 36,560 ሜጋ ዋት ማመንጨት እንደሚቻል ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡ ከወንዞች በተጨማሪ ያሉን በሶስቱ የስምጥ ሸለቆ ሀይቆች ውስጥ በርካታ የአሳ ሀብት የሚገኝ ሲሆን በቱሪዝም ሀብትነታቸውም የጎላ አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ ይችላሉ፡፡

ከገፀ ምድር ሀብታችን ውስጥ የደን ሀብት አንዱ ነው፡፡ ከአጠቃላይ የደን ሀብት ውስጥ በተለያየ መንገድ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ከ25 እስከ 55 ሺህ ሄክታር ደን ያለ ቢሆንም እስካሁን በአግባቡ ጥቅም ላይ አልዋለም፡፡ በተለይ ለወረቀትና ለቺፕውድ ፋብሪካዎች ግብዓት መሆን የሚችል ከ120,000 ሺህ ሄክታር በላይ የቀርከሀ ደን በክልሉ በተለያዩ አካባቢዎች ትላንት በነበረበት ሁኔታ ዛሬም አለ፡፡

በሌላ በኩል ክልላችን በርካታ የከርሰ ምድርና የገፀ ምድር የማዕድን ሀብት ባለቤት ነው፡፡ ከነዚህ ውስጥ ለተለያዩ ኢንዱስትሪዎች ግብዓት ሊሆኑ የሚችሉ ብረት ነክና ብረት ነክ ያልሆኑ ለግንባታ የሚውሉ/ እብነበረድ አግኒዎብራይት ወዘተ/ የጌጣጌጥ ማዕድናት ተሰራጭተው ይገኛሉ፡፡ ስለሆነም አልሚ ባለሀብቶችን በማበረታታት የተፈጥሮ ሀብታችንን ሥራ ላይ ማዋል የሚቻልበት ሰፊ ዕድል አለ፡፡

## VI. ለዜጐች የሥራ ዕድልን ከመፍጠር አኳያ

ከኢንቨስትመንት አላማዎች አንዱ ለዜጐች ሰፊ የሥራ ዕድል መፍጠርና ለሀገሪቱ ዕድገት የሚያስፈልገውን የቴክኒክ ሙያ የሥራ አመራር ዕውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ማስፋፋት ነው፡፡

የሥራ ዕድል ከመፍጠር አንጻር ወደ ማምረትና አገልግሎት መስጠት የተሸጋገሩት አጠቃላይ ፕሮጀክቶች ለ8,866 ቋሚና ለ92,934 ጊዜያዊ በድምሩ ለ101,802 ሰዎች የሥራ ዕድል መፍጠር ችለዋል፡፡

የግሉን ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም ለዘርፉ በሚመች መልኩ በመቅረጽ ኢንቨስተሮች ከፍተኛ የሥራ ዕድል መፍጠር በሚችሉባቸው ሴክተሮች እንዲሰማሩ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር የሥራ አጥ ቁጥርን በከፍተኛ ሁኔታ መቀነስ ይቻላል፡፡

## VII. የወጪ ምርትን በዓይነትና በጥራት እንዲጨምር ከማድረግ አንፃር

የወጪ ምርቶችና አገልግሎቶችን በመጠን፣ በአይነትና በጥራት እንዲጨምሩ በማበረታታት የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ማሳደግና ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በማምረት የውጭ ምንዛሪን ማዳን ከኢንቨስትመንት ዓላማዎች አንዱ ነው፡፡

እስካሁን ካለው የኤክስፖርት እንቅስቃሴ ለመረዳት እንደሚቻለው በክልሉ የተለየዩ ባለሀብቶች ኤክስፖርት ተኮር በሆኑ የኢንቨስትመንት ዓይነቶች የተሰማሩ ሲሆን ለምሳሌ ቡና፣ ሻይ ቅጠልና ቅመማ ቅመም በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ በነዚህ ዘርፎች በርካታ ባለሀብቶች በመሰማራታቸው ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቡና፣ ሻይ ቅጠል፣ ቅመማ ቅመም ወዘተ ምርቶች መጠን እንዲያድግ አስተዋጽኦ ያደረገ ሲሆን በእነዚህና በሌሎችም ዘርፎች የግሉ ኢንቨስትመንት በስፋት መግባት ወጪ ምርቶችን በዓይነት፣ በብዛትና በጥራት በመጨመር ከፍተኛ ዕገዛ እንደሚያደርግ ይታመናል፡፡

## VIII. በዞኖች መካከል የተመጣጠነ ዕድገትን ከማምጣት አንፃር

ከክልላችን የኢንቨስትመንት አላማዎች አንዱ በዞኖች መካከል የኢኮኖሚ እንቅስቃሴና ቅንጅት በመፍጠር የተመጣጠነ ዕድገት እንዲኖር በማበረታታትና በኢኮኖሚ ዘርፎች መካከል ያለውን ትስስር ማጠናከር ነው፡፡ በሁሉም የክልሉ ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች የኢንቨስትመንት ፍቃድ የወሰዱ ባለሀብቶች ያሉ ሲሆን የግል ኢንቨስትመንት እየሰፋ መሄዱ ሁሉንም አከባቢዎች በማካለል ጥቅም ላይ ያልዋለ ጥሬ ሀብት በመጠቀምና የሥራ ዕድል በመፍጠር የኢኮኖሚ ዕድገትን ያፋጥናል፡፡

ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች ባላቸው የኢንቨስትመንት ፖቴንሻል እና ንጽጽራዊ ጠቀሜታ አኳያ የግል ኢንቨስተሮች በተለያዩ ዘርፎች እንዲሰማሩ በማበረታታት አካባቢዎቹን በማልማት ለኢኮኖሚ ዕድገት የላቀ አስተዋጽኦ በማበርከት እንዲሁም የምግብ ዋስትና እንዲረጋገጥ በማድረግ በዞኖችና ልዩ ወረዳዎች መካከል ያለውን የዕድገት ክፍተት ማጥበብ እንደሚቻል ይታመናል፡፡

### IX. በሴክተሮች መካከል የኋላና የፊት ትስስር ከመፍጠር አንጻር

የግል ኢንቨስትመንት እየተስፋፋ በሄደ ቁጥር እርስ በርሳቸው ተደጋጋፊ የሚሆኑ የሴክተር እንቅስቃሴዎችም በዚያው መጠን እየተበራከቱ ይሄዳሉ፡፡ ከዚህም አኳያ የግብርናው ዘርፍ የግብርናውን ምርት በጥሬ ዕቃነት የሚጠቀሙ ንዲሁም መልሰውም ለግብርናው ልማት ገዛ ሊያደርጉ በሚችሉ ዘርፎች ላይ የቅድሚያ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ ጅግ በጣም ጠቃሚ ይሆናል፡፡ አሁን ከገባንበት የድህነት አዙሪት ወጥተን የምግብ ዋስትናችንን አረጋግጠን የዛሬውን ግብርና መር የልማት ስትራቴጂ ወደ ኢንዱስትሪ መር የልማት ስትራቴጂ ለማሸጋገር ካለን ሀብትና አቅም መጀመር ይኖርብናል፡፡ ይህንን ውን ለማድረግ የግብርናውን ዘርፍ ምር ማነት ለመጨመር ምርቱን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ ፕሮሰስ አድርገው የሚጠቀሙ በሌላም በኩል ደግሞ የግብርናውን ምር ማነት ሊያሳድጉ የሚችሉ የማምረቻ መሳሪያዎችን፣ ቴክኖሎጂዎችን፣ ግብዓቶችን ወዘተ ሊያቀብሉ የሚችሉ የኢንቨስትመንት ዘርፎችን በስፋት በማፍራት ሁለቱም ተደጋግፈው ዕድገትን፣ ልማትንና ብልጽግናን ማምጣት የሚችሉበትን ሁኔ ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም የግሉን ሴክተር ልማት ፕሮግራም ቀርጾ መንቀሳቀስ በክፍላተ ኢኮኖሚዎች መካከል የኋላና የፊት ትስስር በመፍጠር ጉልህ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት ይጠበቃል፡፡

## 4.2. የግሉ ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም የትኩረት አቅጣጫ

ከመንግስት የልማት ስትራቴጂዎችና የፖሊሲ አቅጣጫዎች አንፃር በክልላችን የግል ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎችን እንከተላለን፡፡

### 1. የነጻ ገበያ ፖሊሲ አቅጣጫ መከተል፣

የሀገራችን አጠቃላይ የኢኮኖሚ ልማት አቅጣጫ የነጻ ገበያ ፖሊሲ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ በክልላችንም ውስጥ የሚካሄደው የግሉ ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም ይኸንን የነጻ ገበያ ሥርዓት የተከተለ ይሆናል፡፡ በዚህም መሠረት በዘርፉ የተሰማሩና ወደፊት የሚሰማሩ የግል ባለሀብቶች ዋንኛ የልማት እንቅስቃሴው ሞተር ይሆናሉ፡፡ በዘርፉ የሚካሄደው የልማት እንቅስቃሴ በገበያ ኃይሎችና በገበያ ውድድር ላይ የተመሠረተ ይሆናል፡፡ ይህም ሲባል ምርትና አገልግሎትን በአካባቢ፣ በክልል፣ በሀገር ና በዓለም አቀፍ ገበያ በጥራት፣ በዋጋ፣ በመጠንና በጊዜ ብቁ ተወዳዳሪ ሆኖ መገኘትን ይመለከ ል፡፡ ይህንን የነፃ ገበያ ፖሊሲ መርህ የተሳካና ውጤ ማ ንዲሆን ከማድረግ በተጨማሪ የክልሉ መንግሥት የግሉን ኢንቨስትመንት ችግሮች ለመፍ ት ና ተቋማቱ ለውድድር ብቁ ንዲሆኑ የሚያስችሉ የተለያዩ ሥልቶችንና ፕሮግራሞችን ነድፎ ይንቀሳቀሳል፡፡

## 2. ግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫ መከተል፣

ከሀገራችንና ከክልላችን ተጨባጭ የሀብት ሁኔታ በመነሳት ግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጅ ተነድፎ እንቅስቃሴ በመደረግ ላይ መሆኑ የሚታወቅ ነው:: በዚህም እንቅስቃሴ የአጠቃላይ ኢኮኖሚያችንም ሆነ የኢንዱስትሪው ዘርፍ እድገትና የእድገት አቅጣጫ የሚወሰነው በግብርናው ዘርፍ ዕድገትና የእድገት አቅጣጫ ነው:: የግብርናው ዘርፍ ፈጣን ዕድገት ካላስመዘገበ በስተቀር በኢንዱስትሪውም ሆነ በሌሎች የልማት ዘርፎች ፈጣን እድገት ማስመዝገብ  የሚቻል አይሆንም:: በመሆኑም የአጠቃላይ የኢንዱስትሪው ዘርፍም ሆነ በሥሩ የሚገኘው የግሉ ኢንቨስትመንት ንዑስ ዘርፎች ዕድገታቸውን ለማፋጠን የግብርናውን ዘርፍ የዕድገት ሞተርነትና መሪነት ተቀብለው በልማቱ አቅጣጫ ላይ የበኩላቸውን ሚና መጫወት ይጠበቅባቸዋል::

የግብርናው ዘርፍ ለግሉ ኢንቨስትመንት የጥሬ ዕቃ፣ የገበያ እና የካፒታል ምንጭና ለዕድገ ቸው መሰረት ነው:: የግሉ ኢንቨስትመንት አስፈላጊ የሆኑትን ግብዓቶች፣ የማምረቻ መሣሪያዎች፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች፣ የፍጆታ እቃዎች ወዘተ... በማምረት የግብርናውን ልማት ለማፋጠን መመገብ ይጠበቅበታል:: በግብርናው ዘርፍ የሚደረገው የልማት ርብርብና ከዚያም የሚገኘው ዕድገት የግሉ ኢንቨስትመንት ሰፊና ምቹ የገበያ ሁኔታ  ንዲያገኙና ጥራት ያለውን የግብርና ምርት በስፋት በመቀበልና ተጨማሪ እሴት በመፍጠር በሀገር ውስጥና በውጭ ገበያ ተወዳዳሪ ምርቶችን  ንዲያመርትና የካፒታል አቅሙንም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሳደገ  ንዲሄድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል:: በመሆኑም ግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫንና ስትራቴጂን መከተል በክልላችን ለሚካሄደው የግሉ ኢንቨስትመንት ልማት ስኬ  ማነት ወሳኝ ነው::

## 3. ኤክስፖርት መር የኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫ መከተል፣

አሁን በምንከተለው የልማት አቅጣጫ በግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጅ ማዕቀፍ ሥር ሆኖ የኢንዱስትሪውን ዘርፍ የሚመራው የኤክስፖርት ንዑስ ዘርፍ መሆኑ ይታወቃል:: የዕድገቱን ቀጣይነት ለማረጋገጥና አስተማማኝ ለማድረግ የግብርናም ሆነ የኢንዱስትሪ ልማት እንቅስቃሴዎች በገበያ በተለይም በአለም ገበያ ፍላጐት መመራት አለበት:: የግብርናው ዘርፍ በአለም ገበያ ተፈላጊና ተወዳዳሪ የሆኑ ምርቶችን በማምረት ለአለም ገበያ ለማቅረብ በሚያደርገው ጥረት የኢንዱስትሪው ዘርፍ በተለይም የግሉ ኢንቨስትመንት ንዑስ ዘርፍ ለውጭ ገበያ በሚቀርቡ የግብርና ምርቶች ላይ ተጨማሪ እሴት መፍጠር አለበት:: ይህም ለኢንዱስትሪ ልማታችንም ሆነ ለሌሎች የልማት ሥራዎች የሚውል የውጭ ምንዛሪ ግኝት በማዳበር በአለም ገበያ ላይ የመወዳደር ብቃታችን  ንዲያድግ  ና ተጨማሪ  ውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ከማድረግ አኳያ ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል:: በመሆኑም ከ ነዚህ መሰረ  ዊ ነጥቦች በመነሳት በክልሉ የሚካሄደው የግሉ ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም የኤክስፖርት መር የኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫና ስትራቴጂ የተከተለ ይሆናል::

## 4. ንጽጽራዊ ጥንካሬ ያለውን የአካባቢ ሀብት የመጠቀም አቅጣጫ መከተል

ክልሉ ሰፊ ሰብአዊና ተፈጥሮዊ ሀብት እንዳለው የሚታወቅ ነው፡፡ በክልሉ ውስጥ የሚካሄደው የግሉ ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም ሁሉንም ሀብት በእኩል መጠን በመጠቀም ሁሉንም የምርትና የአገልግሎት አይነት በእኩል ደረጃ የማምረትና አገልግሎት የመስጠት ዓላማ የለውም፡፡ ይልቁንም ትኩረት የሚያደርገው በስፋት የሚገኘውን ሀብት (ጥሬ ዕቃ ና የሰው ጉልበት) በብዛት በመጠቀምና በውስን ደረጃ የሚገኘውን ሀብት /ካፒታል/ በቁጠባ በመጠቀም ተጨማሪ እሴት በሚፈጥሩና ክልሉ በሀገራዊም ሆነ በአለም ገበያ ንጽጽራዊ ጥንካሬ ኖሮት ተወዳዳሪነቱን በሚያረጋግጡ ምርቶችና አገልግሎቶች ላይ ነው፡፡ ይህም ሲባል የክልሉን ምቅ ሀብት ጥናት (Resource potential study) መሰረት በማድረግና ሥራ ላይ በማዋል በስፋት ያለውን ሀብት በላቀ ደረጃ መጠቀም ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ይሆናል፡፡ የክልሉ መንግስት ክልሉ ካለው የልማት ንጽጽራዊ ጥንካሬ በመነሣት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የገበያ ክፍተት ባለበት አካባቢ ኢኮኖሚውን ለማነቃቃትና ለማንቀሳቀስ በራሱ ወይም ከግል ባለሀብቶች ጋር በሽርክና በኢንቨስትመንቱ ሊሳተፍ ይችላል፡፡ በመሆኑም የክልሉን የግሉ ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም ይህን አቅጣጫ የተከተለ ይሆናል፡፡

## 5. የህዝብ ተሳትፎና ተጠቃሚነትን የማረጋገጥና ጉልበት ተኮር አቅጣጫ መከተል

የህዝብ ተሳትፎና ተጠቃሚነት በስፋት ያልተረጋገጠበት የልማት ፕሮግራም ውጤታማና ዘላቂ ሊሆን አይችልም፡፡ በመሆኑም በክልሉ የሚካሄደው የግሉ ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም ህዝቡ በተለይም በዘርፉ የተሰማሩና የሚሰማሩ የህብረተሰብ ክፍሎች በየደረጃው በስፋት የሚሳተፉበትና ተጠቃሚ የሚሆኑበት መሆን አለበት፡፡ የልማት ፕሮግራሙ ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ከመግባቱ በፊት ሰፊ የህዝብ ንቅናቄና ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ መሠራት አለበት፡፡ ህዝቡ የግሉ ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም ለኑሮው መሻሻል ምን ፋይዳ እንዳለው በአግባቡ ተረድቶ፣ ለተግባራዊነቱም የሚጠበቅበትን ድርሻ አውቆና አምኖ እንዲንቀሳቀስ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተለይ አብዛኛው የከተማ ህዝብ በአነስተኛ ኑሮ ደረጃና በከፍተኛ ሥራ አጥነት ችግር ውስጥ የሚገኝ መሆኑ ሙን ነው፡፡ በዚህም የተነሳ በግሉ ኢንቨስትመንት ውስጥ በመሳተፍ ኑሮውን ከማሻሻል ውጪ ሌላ የተሻለ አማራጭ እንደሌለው አውቆና አምኖ በስፋት በዘርፉ እንዲሰማራ ና ውጤ ማ ንዲሆን ማድረግ ተገቢ ነው፡፡

በገጠርም ሆነ በከተሞች ውስጥ የሚገኘው አብዛኛው ህዝብ የግሉ ኢንቨስትመንት በሚከፍተው የሥራ ዘርፍ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በመሳተፍ በሚፈጠረው የምርትና የአገልግሎት መስፋፋት ና ብሎም የሥራ እድል ተጠቃሚ ይሆናል፡፡ ህብረተሰቡ በፕሮግራሙ ላይ ከሚያደርገው ተሳትፎ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ የግሉ ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም አንዱና ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ ነው፡፡

## 6. የማስፈፀም አቅምን የመገንባት አቅጣጫ መከተል

እንደማንኛውም የልማት ሥራ የግሉ ኢንቨስትመንት ልማት ያለ በቂ የአቅም ግንባታ ሥራ ውጤ ማና ተግባራዊ ሊሆን አይችልም። በዘርፉ የሚነደፍ የልማት ዕቅድ ያለበቂ የሰው ኃይል፣ አደረጃጀት ና አሰራር በተሟላ መልኩ ተግባራዊ መሆን የሚችል አይሆንም። በዘርፉ የሚፈለግ ብቃትና ጥራት ያለው የሰው ኃይል በአንድ ጊዜ የሚገነባ ሳይሆን በሂደት የሚፈጠርና በዋነኛነት በተግባር አፈጻጸም ሂደት ውስጥ የሚፈጠር እንደመሆኑ መጠን ረዘም ያለ ጊዜ መውሰዱ የማይቀር ነው።

በግሉ ኢንቨስትመንት ላይ ለተሰማሩና ለሚሰማሩ ግለሰቦች፣ ማህበራት፣ አደራጅ አካላት ና ድጋፍ ሰጪ ባለሙያዎች የተለያዩ የቴክኒክ፣ የሙያ እና የሥራ አመራር ሥልጠናዎችን በመስጠት አቅማቸውን ማጐልበት ወሳኝ ነው። ለግሉ ኢንቨስትመንት ከሚሰጡ ድጋፎች ውስጥ በመስኩ የተሰማሩ ግለሰቦችን የአመራር፣ የቴክኒክና የሙያ ክህሎ ቸውን በተግባርና በንድፈ ሃሳብ የሚያጠናክር ስልጠና መሆን አለበት። በዘርፉ የሚሰማሩ አካላት የበለጠ ምርታማና በገበያ ተወዳዳሪ ሊያደርጋቸው ለሚያስችል የቴክኒክና የሥራ አመራር ሥልጠና ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል።

በክልሉ ውስጥ የግሉ ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራምን ለማስተባበር በሚያስችል መልኩ ከክልል እስከ ዞን/ልዩ ወረዳ ድረስ ግልጽ የሆነ አደረጃጀት መፍጠር ያስፈልጋል። ይህም አደረጃጀት ሁለት አይነት መልክ ሊኖረው ይችላል። አንደኛው መንግሥት በየደረጃው ባለው መዋቅሩ በራሱ ሥራውን የሚመራበትና የሚያስተባብርበት አደረጃጀት ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አጋርና ተባባሪ አካላት ጋር ፕሮግራሙን በቅንጅት ለመምራት ንዲያስችለው የሚፈጥረው አደረጃጀት ነው።

ከአቅም ግንባታ አኳያ ሌላው ትኩረት ማግኘት ያለበት ጉዳይ መንግሥት የግሉን ኢንቨስትመንት የሚያደራጅበት የገበያ፣ የፋይናንስ፣ የሥልጠናና የምክር አገልግሎት፣ የማበረታቻ ... ወዘተ ድጋፎች የሚሰጥበት ግልጽ የሆነ ፖሊሲና አሰራር ሊኖረው ይገባል። በመሆኑም የአቅም ግንባ ሥራን በተገቢው አኳኋን ማከናወን የግሉ ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራምን ለማሳካትና ለማፋጠን አንዱ የትኩረት አቅጣጫ ነው።

## 7. የፕሮግራሙን ቀጣይነት የማረጋገጥ አቅጣጫ መከተል

ግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫ፣ ኤክስፖርት መር የኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫ፣ የህዝብ ተሳትፎንና ተጠቃሚነት የማረጋገጥ እና የማስፈጸም አቅም ግንባታ አቅጣጫ በሙሉ አቅም ተግባራዊ በማድረግ የፕሮግራሙን ቀጣይነት ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

ክፕሮግራሙ ቀጣይነት አኳያ የተለየ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሠራ የሚገባው የግሉ ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የሚያመርቱት ምርትና የሚሰጡት አገልግሎት ከአጭር ጊዜ አኳያ የአካባቢ ገበያን እና ከረ|ም ጊዜ አኳያ ደግሞ የውጪ ገበያን መሰረት ያደረገ መሆን አለበት። በግሉ ኢንቨስትመንት የሚመረቱ ምርቶችና የሚሰጡ አገልግሎቶች ገበያ ተኮር መሆን አለባቸው ሲባል በዋነኛነት በጥራታቸው፣ በዋጋቸው፣ በአቅርቦታቸው፣ በስታንዳርዳቸው፣ በዲዛይናቸው ና በአገልግሎት ስፋ ቸው መሆኑ ታውቆ እነዚህን ለማሻሻልና ተቋማቱን በገበያ ተወዳዳሪ ለማድረግ ሰፊ ሥራ መሠራት አለበት።

የግሉ ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የሚያመርቱት ምርትና የሚሰጡት አገልግሎት ገበያን መሠረት ያላደረገና ተወዳዳሪ መሆን ያልቻለ ከሆነ ተቋማቱም ሆኑ የልማት ፕሮግራሙ ዘላቂነት ሊኖራቸው አይችልም።

ሌላው ከፕሮግራሙ ዘላቂነት አኳያ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው በመንግሥትና በሌሎች በሚመለከታቸው አካላት ለግሉ ኢንቨስትመንት የሚሰጠውን ድጋፍ ገበያ ተኮር የማድረጉ ጉዳይ ነው። ይህም በሁለት መልክ ሊታይ የሚችል ነው። የመጀመሪያው በመንግሥትም ሆነ በሌሎች አካላት ለግሉ ኢንቨስትመንት የሚሰጠው ማንኛውም ዓይነት ድጋፍ ተቋማቱን ይበልጥ በጥራት፣ በዋጋ፣ በአቅርቦት… ወዘተ በገበያ ውስጥ ተወዳዳሪ ና ብቁ ሊያደርጋቸው የሚችል መሆን አለበት። ሁለተኛው በመንግሥትም ሆነ በሌሎች አካላት ለግሉ ኢንቨስትመንት ለሚሰጡ አገልግሎቶችና ድጋፎች ግልጽ አሠራር እና ደረጃ በደረጃ ተመጣጣኝ የሆነ የአገልግሎት ክፍያ በማከፈል የፕሮግራሙን ዘላቂነት ማረጋገጥ ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት የመንግስትና የባለሀብቱ የጋራ የምክክር መድረክ ነው። የመንግስትና የባለሀብት የምክክር መድረክ በተለያየ ደረጃ መፍጠር ይቻላል። በየዓመቱ የሚካሄዱ ፎረሞችና ሲምፖዝየሞች ተጠናክረው፣ በቂ ቅድመ ዝግጅትና ተሳትፎ የሚደረግባቸው ሆነው መቀጠል አለባቸው። መንግስት ከባለሀብቱ ጋር የግሉን ኢንቨስትመንት የተለያየ አደረጃጀት (የአምራች ኢንዳስትሪዎች፣ የዘርፍ ማህበራት፣ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ወዘተ) መሠረት ያደረገ የግንኙነት መስመር መዘርጋት አለበት። የመድረኮቹም መሠረታዊ ዓላማም የባለሀብቱን የተወዳዳሪነት አቅም የሚያጠናክርና የተቀመጡ አቅጣጫዎችን ለማስተግበር የሚያስችል መሆን ይገበዋል።

# ክፍል አምስት

# የግሉ ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም ራዕይ፣ዓላማና ግብ

ቀደም ባሉት ክፍሎች ለመግለጽ እንደተሞከረው በክልሉ ኢንቨስመንት ኤጀንሲ በተደረገው ጥናት መሠረት የሥልጠናና የምክር አገልግሎት፣ የፋይናንስ፣ የገበያ፣ የጥገኝነት አስተሳሰብ፣ የመረጃ፣ የመልካም አስተዳደር አለመኖር፣ የቢዝነስ ማኔጅመንት ችግሮች ወዘተ.. የክልሉ የግል ኢንቨስትመንት ዋነኛ ችግሮች ሲሆኑ በክልሉ ውስጥ ለግል ኢንቨስትመንት ዘርፍ የሚሰጡ ድጋፎች ነዚህን መሰረት ያደረጉና ችግሮቹንም የሚቀርፉ መሆን ይጠበቅባቸዋል:: በዚሁ መሠረት በክልሉ ውስጥ ለግል ኢንቨስትመንት የሚሰጡ ዋና ዋና ድጋፎች በአንድ ማዕቀፍ የተደራጁና የሚከተሉትን የሚያካትቱ ይሆናል:-

1. *የአንድ ማዕከል አገልግሎት፣*
2. *የመሠረተ ልማት አቅርቦት፣*
3. *የግብአቶች አቅርቦት፣*
4. *የኢንቨስትመንት መሬት አዘገጃጀትና አቅርቦት አገልግሎት፣*
5. *የኢንተርፕርነርሽፕ ልማት፣*
6. *የመረጃ አገልግሎት፣*
7. *ዉስን የፕሮሞሽን ሥራ ፣*
8. *የምርት ጥራትና ምርታማነት ማሻሻያ፣*
9. *የማስፈጸም አቅም ግንባታ፣*
10. *የጉልበት ሠራተኛ አቅርቦት፣*

ነዚህ ከላይ የተዘረዘሩትን የድጋፍ ዓይነቶች በአንድ የፕሮግራም ማዕቀፍ ውስጥ አጠቃሎ ማቅረቡ የግሉን ኢንቨስትመንት ልማት ከማጠናከር አ‹ዕያ እጅግ በጣም ወሳኝ በመሆኑ የግሉ ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም ተዘጋጅቷል:: በፕሮግራሙ ውስጥ ለግሉ ሴክተር ሊሰጡ የ ሰቡ ድጋፎችን በማጠቃለል 7 ዋና ዋና ንዑሳን ፕሮግራሞች ተዘጋጅተዋል:: በየንዑስ ፕሮግራሞቹም ውስጥ የሚከናወኑ አበይት ሥራዎች በዝርዝር በፕሮጀክት መልክ ተቀምጠዋል::

## 1. የግሉ ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም ራዕይ

በክልሉ ኢኮኖሚያዊና ማኀበራዊ ልማት ውስጥ የላቀ ሚና በመጫዎት ተወዳዳሪ የሆኑ እና በክልሉ ከተሰማሩ ባለሀብቶች 90 ከመቶ ስኬት ያስመዘገቡ ልማታዊ ባለሀብቶች /የግል ኢንቨስትመንትን/ በማስፋፋት የግሉ ሴክተር የኢኮኖሚው አንቀሳቃሽ ሞተር ሆኖ በክልሉ ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች መካከል የተመጣጠነ ዕድገት ተፈጥሮ በ2008 ዓ.ም ክልላዊ ድህነት በግማሽ ቀንሶ ማየት፣

## 2. የግሉ ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም ዓላማ

የግሉ ኢንቨስትመንት በክልሉ ኢኮኖሚያዊና ማኀበራዊ ልማት ውስጥ የላቀ አስተዋጽኦ ንዲያበረክት ማስቻል ነው፡፡

## 3. የግሉ ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም ግብ

የግሉ ኢንቨስትመንት ሴክተር ልማት ፕሮግራም የበርካታ ዓመታት ሥራና ጥረት የሚጠይቅ ሲሆን በክልሉ በሚገኙ ዞኖችና ወረዳዎች እስከ 2008 ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ 8,612 ባለሀብቶች በልዩ ልዩ ሴክተሮች እንዲሰማሩ በማድረግ ለ 1.6 ሚሊዮን ቋሚና ጊዜያዊ ሰዎች የሥራ ዕድል በመፍጠር፣በሴክተሮች መካከል የፊትና የኋላ ትስስር እንዲፈጠር በማድረግ ፣ በውጭ ምንዛሪ ግኝት፣ በድህነት ቅነሳ፣ ዘላቂ ልማት በማፋጠን ወዘተ እንዲሁም በክልሉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንባታ ጉልህ ድርሻ እንዲያበረክቱ ይደረጋል፡፡

### 3.1..የልማት ፕሮግራሙ ዝርዝር ግቦች፡-

#### 1) የአቅም ግንባታ ዝርዝር ግቦች

1.1) በልማት ፕሮግራሙ ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና በ2000 ዓ.ም. ይደረጋል፡፡

1.2) በፕሮግራሙ ዘመን ውስጥ የአንድ ማዕከል አገልግሎት እስከ 2002 ዓ.ም ድረስ በሁሉም ዞኖች ደረጃ በተሟላ መልኩ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

1.3) የክልሉን የግል ኢንቨስትመንት ልማት ከማስፋፋት አንፃር የተሻለ ልምድና የኢንቨስትመንት ተሞክሮ ያላቸውን 8 ሀገሮች በመምረጥ የልምድ ልውውጥ ይደረጋል፤ በዚህ ፕሮግራም በክልሉ የኢንቨስትመንት አፈጻጸም የተሻለ ተሞክሮ ያላቸው 16 ባለሀብቶች ተመርጠው ይሳተፋሉ፡፡ ሀገሮቹም ከአፍሪካ 2፣ ከሩቅ ምስራቅ 4፣ ከደቡብ አሜሪካ 2 ይሆናሉ፡፡

1.4) በፕሮግራሙ ዘመን 5000 ባሀብቶች የኢንተርፕሬነርሽፕ ስልጠና፣ 10,000 ባለሀብቶችና ሠራተኞቻቸው የፋይናንስ አድሚኒስትሬሽን፣ ጠቅላላ ጥራት ሥራ አመራር፣ የሠራተኛ አያያዝ፣ ቢዝነስ ፕላን አዘገጃጀትና እንዲሁም የስትራቴጅክ ዕቅድ ወዘተ ሥልጠና ይሰጣቸዋል፡፡

1.5) በክልሉ ለግል ኢንቨስትመንት መስፋፋት ከሚጫወቱት ሚና አንጻር 900 የክልልና የዞን ባለድርሻ አካላትን በመለየት የግንዛቤ ማስጨበጫን ጨምሮ የተለያዩ የአቅም ግንባታ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡

1.6) በፕሮግራሙ ዘመን የክልሉ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲና የዞን ኢንቨስትመንት ዴስኮች ባለሙያዎችን አቅም ከመገንባት አንፃር በሥራ አመራር፣ በፕሮጀክት ዕቅድ፣ በፕሮጀክት ክትትልና ድጋፍ፣ በፕሮሞሽን ፣ በአስተዳደርና የጽህፈት አገልግሎት፣ ወዘተ ዘርፎች ቢያንስ ለአንድ ጊዜ በኢትዮጵያ የሥራ አመራር ተቋም፣ በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ፣ በክልሉ የሥራ አመራር ተቋምና በመሳሰሉት ተቋማት የአጭር ጊዜ ስልጠና ይሰጣል፡፡

1.7) በፕሮግራሙ ዘመን የኢንቨስትመንት ኤጀንሲ 4 ባለሙያዎች በፒ.ኤች. ዲግሪ ፕሮግራም፣ 16 ባለሙያዎች በሁለተኛ ዲግሪ ፕሮግራም፣ 8 ባለሙያዎች በመጀመሪያ ድግሪ ፕሮግራም፣ እንዲሁም ከዞን ኢንቨስትመንት ዴስኮች 13 ባለሙያዎች በሁለተኛ ዲግሪ፣ 13 ባለሙያዎች በመጀመሪያ ዲግሪ በተለያዩ ዘርፎች በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገሮች የረዥም ጊዜ ስልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

1.8) በፕሮግራሙ ዘመን እስከ 2001 ዓ.ም. ድረስ ሁሉም የዞን ኢንቨስትመንት ዴስኮች አንዳንድ ፋክስ ማሽን፣ አንዳንድ ፎቶ ኮፒ ማሽን፣ አምስት አምስት ኮምፒውተሮች ከነፕሪንተሮቻቸውና የስልክ መስመር እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡

1.9) በፕሮግራሙ ዘመን 24 ተስማሚ ቴክኖሎጂዎችንና የማምረቻ መሣሪያዎችን በተለያዩ ዘርፎች እንዲገቡ ይደረጋል፡፡

1.10) ከነባርና አዳስ ባለሀብቶች መካከል 2500 የሆኑት የንግድ ልማት አገልግሎት /Business Development Service/ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

1.11) የካፒታል እጥረት ካለባቸው ባለሀብቶች መካከል እስከ 2500 ያህሉ ከባንኮች ጋር በሚደረግ ድርድር ብድር የሚያገኙበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

1.12) በፕሮግራሙ ዘመን በክልሉ የኢኮኖሚ ልማት ውስጥ በጣም ወሳኝ በሆኑ ዘርፎች የሚደረገውን ኢንቨስትመንት ከመደገፍ አንጻር በተመረጡ 8 ፕሮጀክቶች የክልሉ መንግስት እስከ 51 ፐርሰንት ሼር በመግዛት ይሳተፋል፡፡

1.13) በፕሮግራሙ ዘመን ብር 65.9 ቢሊዮን ካፒታል ያስመዘገቡ ባለሀብቶች በተለያዩ የኢንቨስትመንት መስኮች የሚሰማሩ ሲሆን ለፕሮጀክቶቹ ማስፈፀሚያ የሚሆን ካፒታል በአማካኝ 60% ከባንክ በብድር እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ ከዚህ ብድር ዉስጥ የማይመለስ ብድር /non performance loan/ 5 ፐርሰንትና ከዚያ በታች እንዲሆን ይሠራል፡፡

1.14) እስከ 2000 ዓ.ም. መጨረሻ ድረስ አዲስ መዋቅር ተጠንቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

## 2) የጥራት ደረጃ ዝርዝር ግቦች

2.1 በፕሮግራሙ ዘመን በክልሉ ውስጥ በ6 የተመረጡ ከተሞች የደረጃ መዳቢ መ/ቤት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንዲቋቋም ይደረጋል፡፡

2.2 በፕሮግራሙ ዘመን በክልሉ በተለያዩ ዘርፎች የተሰማሩ 1000 ባለሀብቶች ለሚያመርቷቸው ምርቶችና ለሚሰጧቸው አገልግሎቶች የ#ISO# 9001 የጥራት ደረጃ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ያገኛሉ፡፡

2.3 እስከ 2008 ድረስ ባለው ጊዜ 20 ምርቶች የአገር ውስጥ ጥራት ደረጃ እንዲሁም 10 ምርቶች አለም አቀፍ የጥራት ደረጃ መስፈርት እንዲያሟሉ ይደረጋል፡፡

### 3) የጉልበት ሠራተኞች አቅርቦት ዝርዝር ግቦች

3.1 በክልሉ ውስጥ በተሰማሩ ሰፋፊ ፕሮጀክቶች አካባቢ የሚገኘው የጊዜያዊ ሰራተኞች ችግር እስከ 2003 ድረስ 90% ይቀረፋል፡፡

3.2 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች አካባቢ የሚከሰተውን የወቅት ሰራተኛ /የጉልበት ሠራተኛ/ እጥረት ከመቅረፍ አኳያ ፕሮጀክቶች በሚገኙባቸው 5 ዞኖች እና የሰው ኃይል ላኪ በሆኑ 5 ዞኖች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች በፕሮግራሙ ዘመን በተከታታይ ይሰራሉ፡፡

### 4) የፕሮሞሽንና የውጭ ገበያ ሥራ ዝርዝር ግቦች

4.1) በፕሮግራሙ ዘመን የክልሉን ንጽጽራዊ ጠቀሜታ አንጻር የተመረጡ 3000 ባለሀብቶች ጋር በአገር ውስጥ ግንባር ግንኙነት በማድረግ የማስተዋወቅ ሥራ ይሠራል፡፡

4.2) የክልሉ ተወላጆች በብዛት የሚኖሩባቸውን 5 የውጭ ሀገሮች በመለየት በተመረጡ የኢንቨስትመንት መስኮች በሚደረግ የግንባር ግንኙነት 500 ባለሀብቶች በማነጋገር 100 ባለሀብቶች ወደ ክልሉ ገብተው ኢንቨስት እንዲያደርጉ ይደረጋል፡፡

4.3) የክልሉን እምቅ ሀብት /potential/ የሚያሣዩ ፕሮግራሞችን በቴሌቭዥን ከማስተዋወቅ አኳያ በዘርፍ፣ በምርትና በአገልግሎት ዓይነት ያነጣጠረ ፕሮግራም በተለየ ሁኔታ ተዘጋጅቶ በየዓመቱ ለ4 ጊዜ በቴሌቪዥን ይተላለፋል፡፡

4.4) የክልሉን ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴና ያለውን ምቹ ሁኔታ በተመለከተ ፕሮግራም እየተዘጋጀ በየሣምንቱ ለ30 ደቂቃ በደቡብ ኤፍ ኤም /FM/ና ሬዲዮ ይተላለፋል፡፡

4.5) የክልሉን የግል ኢንቨስትመንት ልማት ከማስፋፋት አንፃር በ2001 ዓ.ም. በአዲስ አበባ አገናኝ ቢሮ /Laison office/ ይከፈታል፡፡

4.6) ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የሚረዳ ዶክመንታሪ ፊልም 4 ጊዜ ተዘጋጅቶ በሲዲ ለኢንቨስተሮችና ለኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ለወዳጅ አገር ኤምባሲዎች ይሰራጫል፡፡

4.7) በፕሮግራሙ ዘመን በውጭ አገር በሚካሄዱ አለም አቀፍ ኤግዚቢሽኖች 4 ጊዜ ይሳተፋል፡፡

4.8) በፕሮግራሙ ዘመን 500 ባለሀብቶች ለጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ኢንተርፕራይዞች ሰብ ኮንትራት ያደርጋሉ፡፡ በዚሁ የ10,000,000 ብር ዋጋ የሚያወጡ ሥራዎች ሰብ ኮንትራት ይደረጋሉ፡፡

4.9) በፕሮግራሙ ዘመን 80 ባለሀብቶች ከውጭ ባለሀብቶች ጋር የቅንጅት ኢንቨስትመንት እንዲጀምሩ ይደረጋል፡፡

4.10) በፕሮግራሙ ዘመን 1000 ፕሮጀክቶች ወደ ኤክስፖርት ገበያ እንዲገቡ ይደረጋል፡፡ በዚህም 2.5 ቢሊዬን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ዋጋ የሚያወጡ የተለያዩ ምርቶችና አገልግሎቶች ወደተለያዩ የውጭ ሀገሮች ይላካሉ፡፡

4.11) ቋሚ ክልላዊ ፎረም በማዘጋጀት ባለሀብቶችን መሸለምና ከነዚህም መካከል የተመረጡ 20 ኢንቨስተሮች ሥራና ሕይወት ዙሪያ መጽሐፍና ሲ.ዲ ታትሞ ይሰራጫል፡፡

5) **የመረጃ ሥራ ዝርዝር ግቦች**

5.1) በፕሮግራሙ ዘመን እስከ 2002 ድረስ በክልሉ የሚገኙ 13 ዞኖችና 8 ልዩ ወረዳዎች የአዋሳ ከተማን ጨምሮ በመረጃ መረብ /Net work/ ይገናኛሉ፡፡

5.2) የክልሉን እምቅ ሀብት በተለያዩ ሀገሮች ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን እንዲሁም የውጭ ሀገር ኢንቨስተሮችን /FDI/ ከመሳብ አንጻር በተመረጡ 50 ሀገሮች ተቀማጭ ለሆኑ የኢትዮጵያ ሚሲዮኖች የተሟላ የመረጃ ሰነድ /Information Directory/ ተዘጋጅቶ ይሰጣል፡፡ እንዲሁም በቀጥታ በዌብ ሳይት /web site/ በመገናኘት የክልሉን ኢንቨስትመንት የማስፋፋት ተግባር ይከናወናል፡፡

5.3) በፕሮግራሙ ዘመን በተለያዩ ዘርፎች የተሰማሩ 6000 ባለሀብቶች የውጭ ገበያ መረጃ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

5.4) የኤጀንሲው የመረጃ ድረ ገጽ /Web site/ የማሻሻልና የመረጃ ማዕከል /Data base/ የማደራጀት እንዲሁም የመረጃ ሶፍትዌር የማስጠናት ሥራ በፕሮግራሙ የመጀመሪያ ዓመት /2000 ዓ.ም/ ይጠናቀቃል፡፡

5.5) የውጭ ገበያ መረጃ ከሚያቀርቡና ከሚሸጡ 10 ድርጅቶች ጋር ግንኙነት በማድረግ ወቅታዊ መረጃ የመግዛትና ለባለሀብቶች የማቅረብ ሥራ ይሠራል፡፡ የኤጀንሲውን ድረ ገጽ ከነዚሁ ድርጅቶች ጋር የማያያዝና/Linking/ አባል የመሆን/Membership/ ተግባር ይከናወናል፡፡

6) **የፕሮጀክት ክትትልና ግምገማ ሥራ ዝርዝር ግቦች**

6.1) በእያንዳንዱ የኢንቨስትመንት ቀጠና ከየአካባቢው ተነጻጻሪ ጠቀሜታ አንጻር በጥንቃቄ በመለየት ከ3 እስከ 7 የምርት ዓይነቶች በመለየት በዚሁ ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች ልዩ ድጋፍ ተደርጎላቸው በምርቶቹ ስፔሻላይዝ እንዲያደርጉ ይደረጋል፡፡

6.2) እስከ ፕሮግራሙ መጀመሪያ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወስደው መሬት ያላገኙ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን በመከታተል 80 ፐርሰንት መሬት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

6.3) በክልሉ ለኢንቨስትመንት አገልግሎት የሚሆኑ ቦታዎችን በከተማም ሆነ በገጠር ወስደው ወደ ልማት ያልገቡና ባዶ ቦታ ይዘው የተቀመጡ ባለሀብቶችን የሚለይ ጥናት እስከ 2001 ዓ.ም. ተጠናቆ ሕጋዊ እርምጃ ይወሰዳል፡፡

6.4) በኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ሂደት በልማቱ ቦታና በአስፈጻሚ መ/ቤቶች ችግር ከሚያጋጥማቸው ባለሀብቶች መካከል 95% ፈጣን የፍትህ ውሳኔ የመስጠት ሥራ ይከናወናል፡፡

6.5) ነባርና አዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከሚያወጡ ባለሀብቶች መካከል 70% ወደ ማምረት/አገልግሎት መስጠት እንዲሸጋገሩ ሁሉ አቀፍ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

## 7) የመሬትና የመሠረተ ልማት አቅርቦት ዝርዝር ግቦች

7.1 በፕሮግራሙ ዘመን በገጠር 700,000 ሄክታር መሬት በከተማ 2400 ሄክታር መሬት በጋይድ ማፕ ተደግፎ ይዘጋጃል፡፡

7.2 በክልሉ የግል ኢንቨስትመንት ልማት በሚካሄድባቸውና በቀጣይ ሊካሄድባቸው በተዘጋጁ ቦታዎች /አካባቢዎች/ ያለውን የመሰረተ ልማት ችግር በተለይም የመንገድ ችግር ከመቅረፍ አኳያ በፕሮግራሙ ዘመን ወደ ኢንቨስትመንት ሳይቶች የሚያስገባ 500 ኪሎ ሜትር መንገድ በፌደራል የመንገድ ባለስልጣን እንዲሁም 500 ኪሎ ሜትር መንገድ በክልሉ መንገዶች ባለስልጣን ይሰራል፡፡

7.3 ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የመስሪያና የገበያ ቦታ ከማዘጋጀት አንጻር በተመጣጣኝ ዋጋ ለማቅረብ ፕሮጀክቶች ቀርጸው ለሚቀርቡ 200 ባለሀብቶች የከተማ ቦታ በእያንዳንዱ ከተማ መነሻ ዋጋ እንዲሰጣቸው ይደረጋል፡፡

7.4 በክልሉ በተለይም ከአዋሳ ውጪ በሚገኙ 17 ከተሞች ተከልለውና ለምተው የሚገኙ የኢንዱስትሪ መንደሮች ላይ በፕሮግራሙ ዘመን 63 ፐርሰንት ኢንዱስትሪዎች እንዲገነቡ ይደረጋል፡፡

7.5 የገጠር ኢንቨስትመንት መሬትን የመለየትና የማዘጋጀት እንዲሁም ለኢንቨስትመንት አስፈጻሚ መ/ቤት የማስተላለፍ ተግባር የክልሉ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ከ2001 ዓ.ም. ጀምሮ ሙሉ በሙሉ ያከናውናል፡፡

7.6 ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው የግብርና ልማት ፕሮጀክቶች በሚከናወኑባቸው አካባቢዎች የሚኖሩ አርሶ አደሮች የያዙትን መሬት ለግሉ ኢንቨስትመንት ልማት ከማዘጋጀት አንፃር ከባለሀብቶች ጋር በሁለት ዓይነት መንገድ የሚሰሩ ሲሆን፡-

ሀ/ 250,000 ሄክታር መሬት በቅንጅት /out growers scheme/ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

ለ/ 10,000 ሄክታር ላይ የሚኖሩ አርሶ አደሮች መሬታቸውን ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውን ምርቶች ለሚያመርቱ ባለሀብቶች በማከራየት ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

## 8) የኢንቨስትመንት ፈቃድ የመስጠት ዝርዝር ግቦች

8.1) በፕሮግራሙ ዘመን 8,612 አዳዲስ ባለሀብቶች በልዩ ልዩ ሴክተሮች በመሠማራት ለ 485,005 ቋሚና ለ 1,131,678 ጊዜያዊ ሠራኞች የሥራ ዕድል እንዲፈጥሩ ይደረጋል፡፡ እነዚሁ ባለሀብቶች ወደ ክልሉ 65.9 ቢሊዮን ካፒታል ይዘው እንዲመጡ ይደረጋል፡፡

## 4. የግሉ ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም አፈፃጸም ወሰን (Scope):-

1. ፕሮግራሙ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል በሚገኙ ለግል ኢንቨስትመንት በሚ ሰቡ አካባቢዎች ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
2. ፕሮግራሙ ተፈፃሚ ንዲሆን በግል ኢንቨስትመንት ልማት የተሰማሩ የልማት ይሎች ንዲሳተፉበት ሁኔ ዎች ይመቻቻሉ ፡፡
3. ይህ ፕሮግራም የምዕተ ዓመቱን የክልሉን የግል ኢንቨስትመንት ፕሮግራም ለማሳካት ንዲያስችል ከ2000 ዓ/ም ጀምሮ ለ9 ዓመ ት ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል፡፡
4. በዚህ ፕሮግራም ጀማሪና ነባር የግል ባለሀብቶች ና በዘርፉ የተሰማሩ አካላት ሁሉ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

5. ይህንን ፕሮግራም ለማስፈጸም በክልል፣ በዞን፣ በወረዳ፣ በከተሞችና በክፍለ ከተሞች ደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ የመንግስት መዋቅሮች፣ መንግስ ዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ሕብረተሰቡ የሚሳተፉበት ሁኔ ይዘረጋል/ይመቻቻል፡፡

## 5. የግሉ ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም የአፈጻጸም ጊዜ ሰሌዳና ግምታዊ በጀት፤

### .1 የአፈጻጸም ጊዜ ሰሌዳ

ይህ የልማት ፕሮግራም ተፈጻሚ የሚሆነው ከ2000 ዓ.ም እስከ 2008 ዓ.ም ድረስ ባሉት ዘጠኝ ዓመታት ውስጥ ይሆናል፡፡

### 5.2 ግምታዊ በጀት

ፕሮግራሙን ለማስፈጸም የሚያስፈልግ ግምታዊ በጀት 1,101,851,736 (አንድ ቢሊዮን አንድ መቶ አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ሀምሳ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሰላሳ ስድስት) ብር ይሆናል፡፡

| የወጪ አርዕስት | በጀት | መግለጫ |
|---|---|---|
| ለፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ | 918,209,780 | |
| መጠባበቂያ (20%) | 183,641,956 | |
| ድምር | 1,101,851,736 | |

# ክፍል ስድስት

## የግሉ ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም ንዑሳን ፕሮግራሞች

በክልሉ የግሉ ኢንቨስትመንት ሴክተር ሊያበረክት የሚገባውን አስተዋጽኦ የሚገድቡ ዘርፈ ብዙ ችግሮች እንዳሉ ከባለሀብቱ፣ ከአገልግሎት አሰጣጥ አቅርቦትና ከሌሎች ችግሮች አኳያ ከፍ ብሎ በቀረቡት ክፍሎች በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ ስኬታማና ዘላቂ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ማካሄድ የሚቻለውና የዘርፉም አስተዋጽኦ ፍሬያማ ሊሆን የሚችለው እነዚህ ችግሮች ከሥር መሠረቱ ደረጃ በደረጃ ሲቀረፉ ነው፡፡ ስለሆነም እስከ 2008 ዓ.ም. ባለው የፕሮግራም ዘመን ውስጥ ችግር ፈቺ የሆኑ የግሉ ሴክተር ልማት ፕሮግራምና ንዑሳን ፕሮግራሞችን መቅረጽ ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህም አኳያ 7 ንዑሳን ፕሮግራሞች እና በውስጣቸውም የተለያዩ ፕሮጀክቶች የተቀረጹ ሲሆን ዝርዝራቸውም ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

### 1. የአንድ ማዕከል አገልግሎት /One stop shop service/ ንዑስ ፕሮግራም

የአንድ ማዕከል አገልግሎት ማለት ተገልጋዮች  የተለያዩ አገልግሎቶችን በአንድ  ጊዜ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ በተለያዩ ጊዜያት ከአንድ ማዕከል ሊያገኙ የሚችሉበት ሁኔታ ተመቻችቶ የተዘረጋ የአሰራር ስርዓት  ማለት ነው፡፡ የዚህ ዓይነት የአሰራር ስርዓት የተገልጋዩን ጊዜ፣ ጉልበትና ገንዘብ  ከመቆጠቡም በላይ ስለተገልጋዩ አጠቃላይ ሁኔታ የሚያመለክቱ መረጃዎች በአንድ  ቦታ ወይም ማዕከል ስለሚገኙ በአገልግሎት አሰጣጡ ሂደት አገልግሎት ሰጪውም አካል የሚቸገርበት ሁኔታ አይኖርም፡፡ የሚሰጠው አገልግሎትም በአንጻራዊ ሁኔታ በአንድ ማዕከል በተደራጀ መረጃ ላይ የተመሰረተ ስለሚሆን ቀልጣፋ ግልጽና ትክክለኛ ይሆናል፡፡

በመሆኑም በክልሉ የሚገኙትን የግል ኢንቨስትመንት ልማቶችን ለማጠናከርና በተግባር አፈጻጸም የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በመቅረፍ ውጤታማና ተፎካካሪ ለማድረግ ወሳኝ  ናቸው የተባሉ የፕሮሞሽንና የመረጃ ሥርዓት፣ የኢንተርፕረነርሽፕ፣ የስትራቴጂክ ፕላኒንግና የፋይናንስ አቅርቦት፣ የግብዓትና የጉልበት ሠራተኞች አቅርቦት፣ የመሬት ዝግጅት አቅርቦትና የመሰረተ ልማት አገልግሎት፣ የጥራት ስታንዳርድና የውጭ ገበያ ዝግጅት፣ የማስፈፀም አቅም ግንባታ፣ ንዑሣን ፕሮግራሞች ተዘጋጅተዋል፡፡ እነዚህን ንኡሳን ፕሮግራሞች ለመተግበር የሚያስችሉ  የተለያዩ ፕሮጀክቶችም ተለይተው ቀርበዋል፡፡ ንኡሳን ፕሮግራሞቹና ፕሮጀክቶቹ ሰፊ ሲሆኑ በባህርያቸውና

በይዘታቸው በአንድ ማዕከል የሚገኙም አይደሉም፡፡ ስለሆነም ፕሮግራሙን ውጤታማ ለማድረግና በዘርፉ የሚታየውን ችግር በተገቢ መንገድ በመቅረፍ ውጤታማ ስራ ለመስራት እንዲቻል አገልግሎቶቹ በተበታተነ መልኩ እየተሰጡ እንዲቀጥሉ አይጠበቅም፡፡

ይህ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ንዑስ ፕሮግራም በግል የኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም ውስጥ በንኡስ ፕሮግራምነት የተቀመጡትን ፕሮግራሞችና በንኡሳን ፕሮግራሞቹ ውስጥ ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር የሚገናኙትን ፕሮጀክቶች በመለየት፣ በአጠቃላይ የግል ኢንቨስትመንት ልማት ችግሮችን በመቅረፍ የተሻለ የኢንቨስትመንት አፈጻጸምን ለማምጣት የታሰቡ ድጋፎችንና አገልግሎቶችን በአንድ ማዕከል አደራጅቶ የግሉ ኢንቨስትመንት ዘርፍ አስፈላጊውን አገልግሎትና ድጋፍ ሁሉ ከአንድ ማዕከል የሚያገኝበትን ሁኔታ ማመቻቸትን ቁልፍ ዓላማው በማድረግ የተዘጋጀ ነው፡፡ ንዑስ ፕሮግራሞቹንና በውስጣቸው ያቀፏቸውን ፕሮጀክቶች ተግባራዊ በማድረግ ለዘርፉ ለመስጠት የታቀዱ አገልግሎቶችንና ድጋፎችን በአንድ ማዕከል ማደራጀቱ ለልማት ፕሮግራሙ ስኬታማነት ወሳኝ ድርሻ ያለው ከመሆኑም በላይ አገልግሎቱንና ድጋፉን ቀልጣፋ፣ ጊዜንና ወጪን ቆጣቢ ግልጽነት ያለው እና የተቀናጀ ያደርገዋል፡፡

በዚህ መሰረት የተለያዩ አገልግሎትና ድጋፍ ሰጪ ተቋማት ለግል ኢንቨስትመንት የሚሰጡት አገልግሎትና ድጋፍ በቅርብ ርቀት ተደራሽ /accessible/ ጊዜና ወጪ ቆጣቢ እና ቀልጣፋ ሊሆን ይገባል፡፡ ስለሆነም የግል ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ከመንግስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ማግኘት የሚገባቸውን አገልግሎትና ድጋፍ በተቀናጀ መልኩ ከቅርብ ርቀት የሚያገኙበት ሁኔታ መመቻቸት አለበት፡፡ በክልላችን ተጨባጭ ሁኔታ ይህንን አገልግሎት ከአንድ ማዕከል እንዲያገኙ ማድረግ የሚቻለው በዋናነት የዞን ኢንቨስትመንት ዴስኮች ተጠናክረው አገልግሎቶቹን በአንድ ማዕከል መስጠት እንዲችሉ በማድረግ ነው፡፡ የክልል ኢንቨስትመንት ኤጀንሲም በበኩሉ ዞኖች ይህንን የአንድ ማዕከል አገልግሎት እንዲሰጡ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡ በአጠቃላይ በክልሉ ውስጥ ለግሉ ኢንቨስትመንት ዘርፍ የተለያዩ ድጋፎችንና አገልግሎቶችን የሚሰጡ ተቋማት፣ ድርጅቶችና መ/ቤቶች ለዚሁ ዘርፍ የሚሰጡትን አገልግሎቶች በመለየት በዚህ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ውስጥ ገብተው አገልግሎታቸውን የሚሰጡበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡ ሲጠቃለል የግሉን የኢንቨስትመንት ልማት አቅም ለማሳደግና አፈጻጸሙን በማሻሻል ተጨማሪ ዕድገት እንደ ሀገርም ሆነ እንደ ክልል ለማምጣት እንዲቻል ለዘርፉ የሚያስፈልጉ አገልግሎቶችና ድጋፎች በተቀላጠፈና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ ሊሰጡ ይገባል፡፡ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ አገልግሎቶቹና ድጋፎቹ ተቀናጅተውና ተደራጅተው የሚሰጡበት ግልጽ የሆነ አደረጃጀት ሊፈጠር ይገባል፡፡ ለዚህም ነው በዚህ ሰነድ ላይ የተመለከቱ ንኡሳን ፕሮግራሞችና በውስጣቸው ከያዟቸው ፕሮጀክቶች ውስጥ ከአገልግሎት አሰጣጥና ድጋፍ ጋር የሚዛመዱት ተለይተው በዚህ

የአንድ ማዕከል የአገልግሎት አሰጣጥ ንዑስ ፕሮግራም ዉስጥ ተካተው በፕሮጀክት ደረጃ እንዲቀረፁ የተደረጉት፡፡ በመሆኑም የአንድ ማዕከል አገልግሎት ንዑስ ፕሮግራም በአጠቃላይ በግሉ ኢንቨስትመንት የልማት ፕሮግራም ውስጥ ለተካተቱ ንኡሳን ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ስኬታማነት ወሳኝ ከመሆኑ ባሻገር ለግሉ ኢንቨስትመንት ዘርፍ ቀልጣፋ፣ ጊዜና ወጪ ቆጣቢ እንዲሁም ግልጽነት ያለው እና የተቀናጀ ድጋፍ ለመስጠት ያስችላል፡፡

የአንድ ማዕከል አገልግሎት ንዑስ ኘሮግራምን ይበልጥ ውጤታማና ስኬታም ለማድረግ እንዲቻል በንዑስ ኘሮግራሙ ስር በዋናነት የሚከተሉት ኘሮጀክቶች ይኖራሉ፡፡

## 1.1 የግሉን ኢንቨስትመንት ልማት ዘርፍ የአንድ ማዕከል አገልግሎት አቅርቦት የማጠናከር ፕሮጀክት

ይህ ፕሮጀክት በግል ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም ውስጥ የተቀመጡትን አጠቃላይ ንኡሳን ፕሮግራሞችን በተገቢው ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ስራዎች የሚሰሩበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የተቀረጸ ፕሮጀክት ነው፡፡ በዚህ ፕሮጀክት ለዘርፉ የሚሰጡ ድጋፎችን ለማጠናከር የሚያስችሉ የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራዎች እንዲከናወኑ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ፡፡ ፕሮጀክቱን ከማስፈጸም አቅም ግንባታ ንዑስ-ፕሮግራም ጋር ተቀናጅቶ የሚከናወን ይሆናል፡፡ የአንድ ማዕከል አገልግሎቱን በህግ፣ በማቴሪያል፣ በመረጃ መረብና በሰው ኃይል ማደራጀት ተገቢ ይሆናል፡፡ ከሌሎች ከሚመለከታቸው መ/ ቤቶችም በሕግም ሆነ በውክልና ተገቢ አገልግሎቶች እንዲማከሉ ይደረጋል፡፡

## 1.2. የከተማና የገጠር የኢንቨስትመንት መሬት አቅርቦት የአንድ ማዕከል አገልግሎት ፕሮጀክት

ለግሉ የኢንቨስትመንት ልማት እንደ ፕሮጀክቱ ሁኔታ በከተማም ሆነ በገጠር የልማት መሬት ያስፈልጋል፡፡ በዚህ መነሻ ለግሉ የኢንቨስትመንት ልማት የሚሰጡ ለልማት የሚያስፈልጉ ቦታዎች ለገጠር ኢንቨስትመንት በግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ በኩል ለከተማ ኢንቨስትመንት በሥራና ከተማ ልማት ቢሮ በኩል ተከልለውና ተዘጋጅተዉ፣ በጋይድ ማፕና ሌሎች ደጋፊ መረጃዎች ጋር ተደራጅተዉ ለኢንቨስትመንት አስፈጻሚ መስሪያ ቤት ይተላለፋሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የኢንዱስትሪ መንደሮች በተሟላ መረጃ ተደግፈው ይተላለፋሉ፡፡ መሬቶቹ እንደ ልማቱ ሁኔታና እንደ ኢንቨስትመንቱ ዓይነት ተገቢው የማስተዋወቅ ሥራ ተሠርቶ ማልማት ለሚፈልጉ ባለሀብቶች በአንድ ማዕከል አገልግሎት አሰጣጥ ማዕቀፍ ውስጥ በማስገባት በተጠናከረ ሁኔታ ለዘርፉ አገልግሎት የሚሰጡበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

## 1.3 የፈቃድ ምዝገባና አፈጻጸም ተግባራትን በአንድ ማዕከል የማጠናከር ፕሮጀክት

ለግሉ ኢንቨስትመንት ዘርፍ ከሚሰጡ የአገልግሎት አሰጣጥ ተግባራት መካከል ለምሳሌ የፈቃድ አፈጻጸም፣ የንግድ ምዝገባና እድሳት ማበረታቻ መፍቀድ ፣ ወዘተ በተጠናከረ ሁኔታ በአንድ ማዕከል የሚሰጥበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡ እነዚህን ተግባራት በተጠናከረ መልኩ በአንድ ማዕከል አገልግሎት የሚሰጥ የተጠናከረ መዋቅር በዞን ደረጃ እንዲዘረጋ ይደረጋል፡፡ ኤጀንሲውም በዚህ ዘርፍ የተጠናከረ የክትትልና ድጋፍ ሥራ ይሠራል፡፡

## 1.4 የፍትህ አካላት የአንድ ማዕከል አገልግሎት ማጠናከሪያ ፕሮጀክት

የግሉ ኢንቨስትመንት ዘርፍ ከውጪ ከተለያዩ አካላትም ሆነ እርስ በርስ ለሚፈጠሩ የህግ ነክ ጉዳዮችና ክርክሮች አግባብ ያለው የተቀላጠፈ የህግ አገልግሎት የሚያገኙበት የተለየ ችሎት የህግና የፍትህ አገልግሎት የሚፈጠርበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡ በተጨማሪም የግሉ ኢንቨስትመንት የሚፈጽማቸው የውልና ማስረጃ አገልግሎቶችና ምዝገባዎች በአንድ ማዕከል እንዲከናወኑ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ፡፡ በተለይ ባለሀብቶች አንድ ላይ እየሠሩ ያለመተማመን ወይም አንዱ ሌላውን የማጭበርበር ሁኔታ ሲኖር ፍ/ቤቶች በተለየ ትኩረትና ፍጥነት በፍትሐዊነት የሚዳኙበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡ የነፃ ሥርዓት ማለት ኮንትራት ወይም ስምምነት በገዢና ሻጭ መካከል መፈጸም ማለት ስለሆነ የተለየ ትኩረት በመስጠት ሥርዓቱን ማጠናከር ይገባል፡፡

## 1.5 የታክስና ታሪፍ ነክ ጉዳዮች የአንድ ማዕከል አገልግሎት የማጠናከር ፕሮጀክት

የግሉ ኢንቨስትመንት ዘርፍ ከገቢ ግብር ጋር የሚያነሷቸው ስሞታዎችን በማስወገድ የተቀላጠፈ አገልግሎት በመስጠት የዘርፉን እንቅስቃሴ ለማሳደግ ፍትሃዊና የተቀላጠፈ የታክስና የታሪፍ አገልግሎት የሚያገኙበት ሁኔታ በአንድ ማዕከል ይመቻቻል፡፡

## 1.6 የመሠረተ ልማት ተቋማት የአንድ ማዕከል አገልግሎት አቅርቦት የማጠናከር ፕሮጀክት

የፌዴራል መ/ቤቶች ለግሉ ኢንቨስትመንት በፋይናንስ አቅርቦት፣ በመሰረተ ልማት (በስልክና መገናኛ፣ በመብራት አገልግሎት) አቅርቦት፣ በተሻሻሉ የቴክኖሎጂ መሳሪያዎች አቅርቦት፣ በኤክስፖርት ገበያ ድጋፍ አገልግሎት፣ በቴክኖሎጂ ሽግግርና አጠቃቀም የምክር አገልግሎት ወዘተ...ላይ በተጠናከረ ሁኔታ የአንድ ማዕከል አገልግሎት የሚሰጡበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡ ለግሉ የኢንቨስትመንት ዘርፍ የአንድ ማዕከል አገልግሎት የሚሰጥ መዋቅር ይህንኑ አገልግሎት በአንድ ማዕከል አቀናጅቶ ለመስጠት በሚያስችል ደረጃ ተጠናክሮ ይደራጃል፡፡

## 2 የፕሮሞሽን ሥራና የመረጃ ሥርዓት ንዑስ ፕሮግራም

የግሉ ኢንቨስትመንት ዘርፍ ለፈጠራ ውጤቶች መስፋፋት፤ ለኢኮኖሚያዊ ዕድገትና ለድህነት ቅነሳ በሚደረግ የትግል ሂደት ውስጥ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ መሆኑ የተለያዩ ጥናቶች ያረጋግጣሉ፡፡ ሆኖም የአገራችንና የክልላችን ተጨባጭ ሁኔታ መነሻ ተደርጎ ዘርፉ ሲገመገም ከተለያዩ ችግሮች የተነሳ በኢኮኖሚ ልማት ሂደት ዘርፍ የሚጠበቀውን ውጤት እያስገኘ ነው ማለት አያስደፍርም፡፡

በተለይም ክልላች ለኢንቨስትመንት ያለውን አጠቃላይ ምቹ ሁኔታዎችን በመለየት ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገር ባለሀብቶች በማሳወቅ ኢንቨስትመንትን በመሳብ በክልሉ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ኑሮ የሚጠበቅበትን ሚና እንዲጫወት ማድረግ ይጠበቃል፡፡ በዚህ ረገድ ሊጠቀስ የሚገባው ችግር እስከ አሁን በክልሉ እየተከንወነ የነበረው የፕሮሞሽን ተግባር ክልሉን የተሻለ ትርፋማ ሊያደርጉ በሚችሉ ሴክተሮች፣ አገሮችና ባለሀብቶች በማተኮር ሳይሆን በጅምላ የሚደረግ መሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም የክልሉን አጠቃላይ ገፅታና ለኢንቨስትመንት የተፈጠረውን ምቹ ሁኔታ፣ የኢኮኖሚ ሴክተሮችን፣ ንፅፅራዊ ጠቀሜታ ሊገኝባቸው የሚችሉ አገሮችንና ተመራጭ የኢንዱስትሪ ዓይነቶችንና ደረጃዎችን በለየ መልኩ ስፋት ያለው የማስተዋወቅ ሥራ /Focused Promotion/ በዚህ ንዑስ ፕሮግራም በኩል ይሰራል፡፡ ለዚህም የሀገር ውስጥና የውጭ ሚዲያዎች፣ ጋዜጦች፣መጽሄቶች፣ የውጤታማ ባለሀብቶችን ምስክርነት በመጠቀም ማስተዋወቅ፣ ብሮሸሮች፣ ኢንተርኔትና ሌሎች የጋራ መድረኮች በመሳሪያነት በመጠቀም ይከናወናል፡፡

ከፕሮሞሽንና የህዝብ ግንኙነት ሥራ ባሻገር በዚህ ንዑስ ፕሮግራም ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ሥራ የመረጃ አቅርቦት ጉዳይ ነው፡፡ አሁን ካለንበት ነባራዊ ሁኔ አንጻር ሲታይ ዓለም አንድ መንደር የሆነች መጥታለች፡፡ ለአንድ መንደርነቷ አስተዋጽኦ ካበረከቱት ቁልፍ ጉዳዮች ዋንኛውና አንዱ መረጃ ነው፡፡ በተለይም የኢንተርኔትና ድህረ-ገጽ መረጃ በመጠቀም ምርትን፣ አገልግሎትን፣ ሐሳብን ወዘተ መሸጥና መግዛት በቦታና በጊዜ ሳይገደብ የሚከናወንበት ወቅት ላይ ተደርሷል፡፡ ይህም የሚያሳየው በዘመናዊ መረጃ ባልታገዘ አካሄድ ብቁ ተወዳዳሪ ሆኖ መገኘት አዳጋች መሆኑን ነው፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ በክልላችን ተጨባጭ ሁኔታ የግሉ ኢንቨስትመንት ሴክተር በማስፋፋትና በማበረታታት ሂደት ውስጥ ከመረጃ አኳያ የሚያጋጥሙ መሠረታዊ ችግሮችን በሁለት ከፍሎ መመልከት ይቻላል፡፡ አንዱ በግል ባለሀብቶች በኩል ያለው በመረጃ ጠቀሜታ ላይ በቂ ግንዛቤና ውቀት አለመኖር ሲሆን ግንዛቤው ያላቸውም ቢሆኑ መረጃውን የማግኘት ዕድላቸው የጠበበ መሆኑ ነው፡፡ ሌላኛው ችግር ደግሞ በዘመናዊ መልኩ የተደራጀና የተሟላ የመረጃ አገልግሎት ለሚፈልጉ የግሉ ሴክተር በአንድ ማዕከል ውስጥ በመታቀፍ የሚፈለገውን መረጃ የሚያቀርብ አካል አለመኖር እና ቢኖርም እንኳ ወጥ በሆነ መልኩ አለመገኘት ችግር ነው፡፡ ለምሳሌ የኢንቨስትመንት አማራጭ ዕድል መረጃዎችን በተመለከተ በዳታ

ቤዝነት ካለመያዛቸውም በላይ መረጃዎቹ በመ/ቤት ደረጃ በባለቤትነት የትና ማን ጋር እንዳሉ ሳይታወቁ ተበታትነው የሚገኙበት ሁኔታ ይታያል፡፡

በመሆኑም የግሉ ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም አፈፃፀም የተሳካ እንዲሆን የተሟላ የመረጃ አገልግሎት መኖር ወሳኝ ነው፡፡ ስለዚህ በሁሉም የአስተዳደር ርከን ደረጃ (ክልል፣ዞን፣ልዩ ወረዳ) የተለየ ትኩረት ተሰጥቶበት መረጃን የመሰብሰብ፣ የማደራጀትና የማሰራጨት ተግባር በተጠናከረና ተሳትፎአዊ በሆነ ሁኔ መከናወን እንዳለበት ይታመናል፡፡

የመረጃን አገልግሎት ለማጠናከር ከክልል ጀምሮ ስከ ዞንና ልዩ ወረዳ ድረስ ባለው መዋቅር የመረጃ ማዕከላት በማቋቋም ና የመረጃ ልውውጥ መረብን በመዘርጋት የክልሉን ምቅ ሀብት፣ የውጭና የአገር ውስጥ ገበያ መረጃ፣ የጥሬ ዕቃ፣ የግብር፣ የፖሊሲ፣ የመሠረተ ልማት ሁኔታ በተጠናከረ መልክ የሚደራጅበት ምቹ ሁኔ ይፈጠራል፡፡

ነዚህ መረጃዎች በመረጃ ቋት (Data Base) በማደራጀትና በኮምፒውተር የመረጃ መረብ አማካይነት ማዕከላቶች ርስ በርስ ንዲተሳሰሩና ከሀገር አቀፍና ከዓለም አቀፍ የመረጃ ማዕከላትና መረቦች ጋር ግንኙነት ንዲፈጥሩ ምቹ ሁኔ ይፈጠራል፡፡ የሚደራጁ መረጃዎችም የክልሉን ምቅ ሀብት፣ የክልል፣ የሀገር አቀፍና የዓለም አቀፍ ገበያ፣ የመሣሪያና የቴክኖሎጂ አቅርቦት፣ የሰው ሃይል፣ የስልጠና አገልግሎት፣ የቦታ፣ የፋይናንስ አቅርቦት፣ የመንግስት ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ደንቦች፣ የጨረታ ሂደት፣ የታክስ አከፋፈል፣ የጥሬ ዕቃ አቅርቦት፣ እና ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶችን የተመለከቱ መረጃዎች ይሆናሉ፡፡

የፕሮሞሽንና የመረጃ ሥርዓት ንዑስ ፕሮግራምን ውጤ ማና ስኬ ማ ለማድረግ ንዲቻል በንዑስ ፕሮግራሙ ሥር የሚከተሉት ዋና ዋና ፕሮጀክቶች ይኖራሉ፡-

## 2.1 የልማታዊ ባለሀብትና የኢንተርኘሪነርሽፕ ባህል የማሳደግና የማስፋፋት ፕሮጀክት

ከክልል እስከ ቀበሌ ድረስ ያለው የመንግስት አስፈጻሚ አካላት ድህነትንና ሥራ አጥነትን ከማስወገድ አንጻር ኢንቨስትመንት ያለውን ጠቀሜታ ተረድተው የባለቤትነት ስሜት በመፍጠር የሚንቀሳቀሱበት ሁኔታ እንዲኖር ለማድረግና ልማታዊ ባለሀብት ከማፍራትና የኢንተርፐሪነርሽፕ ባህል ከማስረጽ አኳያ ልዩ ልዩ ሚዲያዎችን በመጠቀም የህዝብ ግንኙነት አገልግሎት ሥራ ይሠራል፡፡ እንዲሁም የግምባር ግንኙነቶች ማለትም ሴሚናሮች፣ ፎረሞችና የፓናል ውይይቶች በተከታታይ እንዲካሄዱ ይደረጋል፡፡

## 2.2 የተለየ ትኩረት የሚሰጠው የፕሮሞሽን ሥራ ፕሮጀክት፣

በዚህ ፕሮጀክት አማካይነት ቀደም ሲል እንደሚደረገው ጅምላ የሆነ የማስተዋወቅ ሥራ ሳይሆን ልዩ ትኩረት የሚያሻቸውን መንገዶች /Focused Promotion/ በመጠቀም የተሟላ መረጃ በማቅረብ በሚከተለው ሁኔታ በስፋት የማስተዋወቅ ሥራ ይሠራል፡፡

### ሀ. ኢንቨስተር ተኮር የማስተዋወቅ ሥራ፣

በክልላችን ንፅፅራዊ ጠቀሜታ አላቸው ተብለው በሚታሰቡ የኢንዱስትሪ፣ የአግሮ ኢንዱስትሪና የግብርና፣ የማዕድን ልማት፣ የኃይል ማመንጫና የኮንስትራክሽን ሥራዎችን የቴክኒክና የሥራ አመራር ብቃት ሊኖራቸው የሚችሉትን ኢንቨስተሮች በማነጣጠር በግንባርና በሌሎች የግንኙነት መድረኮች በመጠቀም የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ሥራ ይሠራል፡፡

### ለ. የኢኮኖሚ ሴክተሮችን ባገናዘበ መልኩ የሚካሄድ የማስተዋወቅ ሥራ፣

በክልላችን ባሉ ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች አካባቢ ከመሬት አቅርቦት፣ ከኢንዱስትሪ ግብአት አቅርቦት፣ ከዓመታዊ የሰብል፣ አትክልትና ፍራፍሬ ልማት አንጻር ያላቸው ንፅፅራዊ ጠቀሜታ እየተገመገመ በግብርና፣ በኢንዲስትሪና አግሮ- ኢንድስትሪ፣ እንዲሁም በእንስሳት ሀብት ልማትና በሌሎችም ትኩረት በሚሰቡ መስኮች ላይ ያነጣጠረ የተጠናከረ የፕሮሞሽን ሥራ ይሠራል፡፡

### ሐ. ንፅፅራዊ ጠቀሜታ ሊገኝባቸው በሚችሉ አገሮች ላይ ያነጣጠረ የማስተዋወቅ ሥራ፣

ከጂኦግራፊያዊ ቅርበት፣ ከደረሱበት የቴኮኖሎጂ የዕድገት ደረጃ፣ በዓለም አቀፍ የገበያ ውድድር ከሚኖራቸው ሚናና የወዳጅነት ታሪካቸው ወዘተ ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ንፅፅራዊ ጠቀሜታቸው ጎልተው በሚታዩ የምዕራብ አውሮፓ፣ የሰሜን አሜሪካ፣ እስያና ፓሲፊክ፣ እንዲሁም ሰሜን፣ መካከለኛና፣ ምስራቅ የአፍሪካና ሌሎችም አገሮች በማነጣጠር የኢንቨስትመንትን መልእክት የያዙ ልኡካን በመላክ የማስተዋወቅ ሥራ ይሠራል፡፡

### መ. የኢንዱስትሪ አይነትና ደረጃ በመለየት የሚደረግ የማስተዋወቅ ሥራ፣

ክልላችን ለኢንዱስትሪ ልማትና አግሮ ፕሮሰሲንግ የሚውሉ፣ የጥጥ፣ የቅባት እህሎች፣ ቅመማ ቅመም፣ አትክልትና ፍራፍሬ፣ እንስሳትና የእንስሳት ተዋጽኦ በስፋት የሚመረትበት ክልል ሆኖ እያለ የኢንዱስትሪ ውጤት የሆኑ ጨርቃ ጨርቅና አልባሳት፣ የከፍተኛ ኢንዱስትሪ ውጤት የሆኑ ሌሎች ምርቶች፣ የአግሮ ፕሮሰሲንግና ምግብ ነክ ምርቶች ከውጭ ተረካቢዎች መሆናችን ኢንቨስትመንትን በማስፋፋትና በማስተዋወቅ በኩል ገና ምንም እንዳልተሠራ አመልካች ነው፡፡

ስለሆነም ለጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ምርት፣ የቅባት ሰብሎች፣ የቅመማ ቅመምና አትክልትና ፍራፍሬ፣ የዓሣ ምርት፣ የእንስሳት እርባታና የእንስሳት ምርት ተዋጽኦ ማቀነባበሪያ፣ ለቆዳና ሌጦ ኢንዱስትሪዎችና ለሌሎችም የኢንዱስትሪ ልማቶች ትኩረት በመስጠት የማስተዋወቅ ሥራ በስፋት የሚካሄድበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

## 2.3 የመረጃ ኔትወርክና ሥርዓት የመዘርጋት ፕሮጀክት

በዚህም ፕሮጀክት አማካይነት ለግሉ ኢንቨስትመንት ቀልጣፋና ውጤ ማ የመረጃ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የመረጃ መሰረተ ልማትና ሥርዓት /Wide Area Network, Local Area Network, Management Information System/ ደረጃ በደረጃ ከክልል ስከ ዞን ኢንቨስትመንት ዴስኮች እና ልዩ ወረዳ ኢንቨስትመንት አካል ድረስ ይዘረጋል፡፡

## 2.4 የመረጃ ማጠናቀሪያና ሪፖርት ማቅረቢያ ሶፍትዌር ፕሮጀክት

ከክልል፣ ከዞኖችና ልዩ ወረዳዎች መረጃ በተቀላጠፈ መንገድ እንዲለዋወጥ የሚያግዝ እንዲሁም የክልሉ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ከፌዴራል ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ጋር መረጃ ለመለዋወጥ የሚያግዝ በአማካሪ የሚጠና ዳታ ቤዝ ማኔጅመንት እና ሪፖርት ማድረጊያ ሶፍትዌር (Software Development) የማዘጋጀት ሥራ ይከናወናል፡፡

## 2.5 የመረጃ ድረ-ገጽ ዝግጅት ፕሮጀክት

ከኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ዋና ዋና ተግባራት ውስጥ አንዱ የፕሮሞሽን ሥራ ሲሆን በዚህ ፕሮጀክት አማካኝነት የክልሉን እምቅ ሀብት፣ ፖሊሲዎች፣ ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞች በአገር ውስጥና በውጭ ላሉት ነባርና አዳዲስ ባለሀብቶች በተቀላጠፈ መንገድ ለማስተዋወቅ የሚረዳ የድረ-ገጽ ማጎልበት (Web-Page Development) ሥራ ይሠራል፡፡

## 2. 6 የመረጃ አገልግሎት ፕሮጀክት

በዚህ ፕሮጀክት አማካይነት ለግሉ ኢንቨስትመንት የገበያ፣የክልሉ እምቅ ሀብት፣ የመሣሪያና የቴክኖሎጂ አቅርቦት፣ የሰው ኃይል፣ የስልጠና አገልግሎት፣ የዲዛይን፣ የዋጋ፣ የጥራት ደረጃ፣ የቦታ፣ የፋይናንስ አቅርቦት፣ ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞች፣ የመንግስት ፖሊሲዎች፣ ህጎችና ደንቦች፣ የጨረታ፣ የታክስ አከፋፈል፣ የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ወዘተ ላይ የመረጃ አገልግሎት ይሰጣል፡፡ መረጃዎች በመረጃ ቋት (Data Base) በማደራጀትና በኮምፒውተር የመረጃ መረብ አማካኝነት ማዕከሎቹ ርስ በርስ ንዲተሳሰሩና ከሀገር አቀፍና ከዓለም አቀፍ የመረጃ ማዕከላትና መረቦች ጋር ግንኙነት ንዲፈጥሩ ምቹ ሁኔ ይፈጠራል፡፡

## 3. የግብዓቶችና የጉልበት ሠራተኞች አቅርቦት ንዑስ ፕሮግራም

ቀደም ሲል በቀረቡት ክፍሎች በዝርዝር ለማየት እንደተሞከረው የግብዓት አቅርቦት ማነስ በኢንቨስትመንት ልማት ላይ ከሚ ዩ ዋና ዋና ችግሮች አንዱ ነው ፡፡ በግል ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም ሥር ከ ቀፉ ንዑስ ፕሮግራሞች መካከል አንዱ የግብዓትና የጉልበት ሠራተኛ አቅርቦት ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም ነው ፡፡ የግብዓት አቅርቦት ሲባል በርካ ነገሮችን የሚያጠቃልል ሲሆን በውስጡ የፕሮጀክት ፋይናንስ፣ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎች፣ የጥሬ ዕቃ አቅርቦት፣ የሠራተኛ ጉልበትና የኢንቨስትመንት መሬት አቅርቦት የሚካተቱ ቢሆንም የኢንቨስትመንት መሬት አቅርቦትና የፕሮጀክት ፋይናንስ ካላቸው ልዩ ባህሪይ የተነሳ በሌሎች ንዑሳን ፕሮግራሞች ውስጥ ተካተው የተቀረጹ ሲሆን የተቀሩት ግብአቶችና በሥራቸው የሚከናወኑ አበይት ሥራዎች ወይም የፕሮጀክቶች ሀሳቦች በዚህ ንዑስ- ፕሮግራም ውስጥ በዝርዝር እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ስለሆነም በዚህ ንዑስ-ፕሮግራም ውስጥ ከሚታዩ ጉዳዮች አንዱ የግል ባለሀብቶች ተስማሚ ቴክኖሎጂንና የማምረቻ መሳሪያዎችን ከማግኘትና ከመጠቀም አኳያ ያለው ችግር ሲሆን ይኸው በጥልቀት ሲታይ ሁለት መሰረ ዊ ችግሮች ያሉበት ነው፡፡ አንደኛው ምንም ንኳን ባለሀብቶች ተስማሚ ቴክኖሎጂንና መሳሪያዎችን በግላቸው ለመግዛት አቅሙ ቢኖራቸውም መሳሪያዎቹ የሚገኙበትን ቦ ፣ የጥራት ደረጃ፣ ለፕሮጀክ ቸው የሚስማማ ቴክኖሎጂ መሆኑን ንዲሁም ዋጋቸውን የሚያሳይ መረጃ በቀላሉ የማግኘት ችግር አለባቸው፡፡ ይህም ችግር ከውጭ በሚገቡ መሳሪያዎችና ቴክኖሎጂዎች ላይ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ሀገር በቀል በሆኑ መሳሪያዎችና ቴክኖሎጂዎ-ችም ላይ የሚ ይ ነው፡፡ ሁለተኛው ችግር መሳሪያዎቹና ቴክኖሎጃዎቹ መኖራቸውን ቢያውቁም ለመግዛት የአቅም ውስንነት ያለባቸው መሆኑ ነው፡፡

በንዑስ-ፕሮግራሙ ውስጥ ከሚታዩ ጉዳዮች ሌላኛው ከጥሬ ዕቃ አቅርቦት ጋር የተያያዘ ችግር ሲሆን ጥሬ ዕቃ የሚባሉት በርካ ዓይነቶች ቢሆኑም በተለይ ለግል ኢንቨስትመንት ወሳኝ የሆኑ ንደ ሲሚንቶ፣ የግንባ ቁሳቁስ፣ ምርጥ ዘር፣ ማዳበሪያ፣ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችና ነኝህን የመሳሰሉ ሲሆኑ እነዚህ ጥሬ ዕቃዎች በአብዘኛው የግሉ ኢንቨስትመንት ችግሮች ሆነው የሚቀርቡበት ጊዜ ይበዛል፤፤

በንዑስ-ፕሮግራሙ ውስጥ ከሚታዩ ጉዳዮች ሶስተኛው ከጉልበት ሠራተኞች እጥረት ጋር ተያይዞ የሚነሣ ችግር ሲሆን የጉልበት ሠራተኞች ጉዳይ ሲነሳ በዋናነት የሚነሳው በእርሻና በአግሮ ኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ የተሰማሩ የግል ኢንቨስትመንት ልማት ድርጅቶች ያለባቸውን የሰው ኃይል እጥረት ነው፡፡ ክልሉ ካለው ተነጻጻሪ የኢንቨስትመንት ምቹነት አኳያ ሰፋፊ መሬቶችና ሰፋፊ የግል ኢንቨስትመንቶች በተለይም በግብርናና አግሮ ኢንዱስትሪ የልማት ዘርፍ ተሰማርተው የሚገኙበት ክልል ነው፡፡ ለወደፊትም ክልሉ በዚህ ዘርፍ ሰፊ እምቅ አቅም አለው፡፡ ሆኖም ግን በተለይም በሰፋፊ መሬቶች ላይ የኢንቨስትመንት ስራዎች በተከናወኑባቸው በምዕራብ፣ በደቡብና

በማዕከላዊ ዞኖች አንዳንድ አካባቢዎች ከፍተኛ የሆነ የሰው ሀይል አቅርቦት ችግር ተከስተዋል፡፡ በግብርና ልማትና በአግሮ ኢንዱስትሪ ዘርፍ በግል ኢንቨስትመንት ፕሮግራም ተሰማርተው የሚገኙ ብዙ ድርጅቶች በሰው ኃይል እጥረት ችግር የተነሳ ወቅቱን ጠብቆ መሰብሰብ የሚገባው ከፍተኛ የምርት መጠን ለብክነት ሲዳረግ ይስተዋላል፡፡ የሠራተኛ እጥረት እንደምክንያት የሚጠቀሱ ጉዳዮችን በተመለከተ በአንጻራዊ ሁኔታ የተሻለ የሰው ሀይል የሚገኙባቸው ማዕከላዊ ዞኖች ከልማት አካባቢው መራቅ፣ በአካባቢው  የሚገኘው ህዝብ የግንዛቤ ችግር፣ በአንዳንድ ፕሮጀክቶች አካባቢ ሰራተኞችን በቀላሉ ለማጓጓዝ  የመንገድ ችግር መኖር፣ የፕሮጀክቶቹ  የክፍያ ሁኔታ ካለው ርቀትና  ቤታቸውን ጥለው የሚሄዱ ከመሆኑ አንጻር ለሠራተኞቹ በቂ ወይም ሳቢ ያለመሆን፣ በአብዛኞቹ የግል ኢንቨስትመንት ሳይቶች የሚሰሩ ሰራተኞች ደህንነታቸውና ጤንነታቸዉ ተጠብቆ  የሚኖሩበት ሁኔታ በአግባቡ ያልተደራጀ መሆን፣ ሰራተኞች የሰሩበትን ገንዘብ በወቅቱ ያለመከፈልና ጠፍተው እንዳይሄዱ በሚል በመያዣነት መያዝ፣  በአብዛኞቹ ፕሮጀክቶች አካባቢ ያለው የምርት መሰብሰቢያ ጊዜ ተመሳሳይና አጭር ከመሆኑ  የተነሳ ሰራተኞች ወደ አካባቢው ለመሄድ ያለመፈለግ፣ በሌሎች ክልሎች በተመሳሳይ ሁኔታ የጉልበት ሰራተኞች ከሚቀጥሩ የተለያዩ ፕሮጀክቶች ጋር ሲነጻጸር የሚከፈለው ክፍያ አነስተኛ መሆን በመሰረታዊነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ስለዚህ  የግሉን ኢንቨስትመንት ልማት  የሰው ኃይል እጥረት  ችግሮች በመፍታት በዘርፉ የተሰማሩ የልማት ፕሮጀክቶች ያመረቱትን ምርት በአግባቡ ወቅቱን ጠብቆ በመሰብሰብ በመጠን፣ በጥራት፣ በዋጋ፣ በጊዜና በአቅርቦት ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማስቻል ነው፡፡

ስለሆነም በክልሉ በእርሻና በአግሮ ኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማሩ የግል ኢንቨስትመንት የልማት ተቋማት ከሰው ኃይል እጥረት አኳያ ያሉባቸውን  ዋና ዋና ችግሮች በመለየት ችግሮቹን ለመፍታት የሚያስችል የተደራጀና ወጥ የሆነ ውጤታማ የሰው ኃይል አቅርቦት ስርዓት በመዘርጋትና የእርሻ ልማት ድርጅቶች ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ለክልሉ ልማት የሚያበረክቱትን አስተዋጽኦ በማጎልበትና የክልሉን ወጪ ምርቶች አቅርቦት በማሳደግ የክልሉን ብሎም የሀገሪቱን የኢኮኖሚ እድገት ለማፋጠን የሚያስችል ሁኔታ ይመቻቻል፡፡ ይህንን ግብ ለመምታት በክልሉ በእርሻና በአግሮ ኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች ለሥራቸው ተስማሚ፣ ውጤታማና ትጉህ ሰራተኞችን የሚያገኙበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡ በክልላችንም ሆነ በሀገራችን ዋንኛ  ሀብት የሆነውን የሰው ኃይል ጉልበት በተደራጀና በተቀናጀ ሁኔታ በማስተባበርና ምርታማ ስራ ላይ በማሰማራት ለግሉ ኢንቨስትመንት ሴክተር በከፍተኛ ሁኔታ በችግርነት የሚታየውን የአምራች ኃይል የስራ እጥነት ችግር ለማቃለል የሚያስችል አሰራር ይፈጠራል፡፡

ስለሆነም ከፍ ብሎ በዝርዝር የተቀመጡትን ችግሮች ለመቅረፍ በሚያስችሉ መልኩ ያነጣጠሩ ፕሮጀክቶች በዚህ ንዑስ ፕሮግራም ውስጥ ተቀርጸው ተግባራዊ ይደረጋሉ ። ከዚህ በመነሳት የግል ኢንቨስትመንት የግብዓትና የጉልበት ሠራተኛ እጥረትን ለመቅረፍ የተዘጋጀዉን ንዑስ ፕሮግራም ስኬታማ ለማድረግ የሚከተሉት ፕሮጀክቶች ይተገበራሉ፡፡

## 3.1. የተስማሚ ቴክኖሎጂና የማምረቻ መሳሪያዎች ፕሮጀክት፣

የግል ባለሀብቶች ተስማሚ ቴክኖሎጂንና የማምረቻ መሳሪያዎችን ከማግኘትና ከመጠቀም አኳያ ሁለት መሰረ ዊ ችግሮች እንደሚስተዋልባቸው ከላይ ተመልክቷል። ከችግሮቹ አንድኛው ከመረጃ ጋር የተያያዘ ሲሆን ይህንን የመረጃ ችግር ለማቃለል በየደረጃው የሚቋቋሙ የመረጃ ማዕከላት የተጠናከረ የቴክኖሎጂ መረጃዎችን የሚይዙበትና አገልግሎት የሚሰጡበት ሁኔ ይፈጠራል። በመሆኑም በፕሮግራሙ ዘመን በቀዳሚነት በክልሉ ለግል ኢንቨስትመነት በወሳኝነት ተፈላጊ የሆኑ መሳሪያዎችን ዝርዝር በዓይነት፣ በምንጭና በቴክኖሎጂ ደረጃ ንዲለይ ይደረጋል። ከዚህም በተጨማሪ በውጭም ሆነ በሀገር ውስጥ ስለሚገኙ የሊዝ መሳሪያዎች ሻጮችና አከራዮች መረጃ ቋት ይደራጃል። በየጊዜውም ይሻሻላል።

ከሊዝ መሳሪያ ሽያጭና ኪራይ ጋር በተያያዘ በክልሉ ስካሁን የተጀመረ ተጨባጭ ንቅስቃሴ የሌለ በመሆኑ በፕሮግራሙ ዘመን በመሳሪያ ሊዝና የኪራይ ግዥ አገልግሎት የግሉ ዘርፍ በስፋት የሚንቀሳቀስበት ሁኔ ይበረ ል። የክልሉ መንግሥት በዚህ ዘርፍ ለሚሳተፉ የግል ባለሃብቶች የተለያዩ ገዛዎችን ከመስጠት ባሻገር የማበረ ቻ ሥርዓት ይዘረጋል።

አንዳንድ ባለሀብቶች በተለያዩ አጋጣሚዎች ያገኟቸውን ቴክኖሎጂዎች በሙሉ አቅም ለመጠቀም የአቅምና የዕውቀት ውስንነት አለባቸው። ቴክኖሎጂውን የማግኘት ችግር ያለባቸው ባለሀብቶች በማህበር ተደራጅተውም ሆነ በግላቸው ቴክኖሎጂውን የሚያገኙበት ምቹ ሁኔ ይፈጠራል። ቴክኖሎጂው ኖሯቸው ከአቅም በ ች ለሚያመርቱት የምክርና የስልጠና አገልግሎት ይመቻችላቸዋል። ከኮሌጆች፣ ከዩኒቨርሲቲዎችና ከምርምር ተቋማትና ማዕከላት ጋር በሚፈጠሩ የተለያዩ ቅንጅ ዊ ሥራዎች የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን ለማራባት የሚያስችሉ የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ ስልጠናዎችና ትምህር ዊ ጉብኝቶች በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ለባለሀብቶች ይሰጣሉ ።

በመንግሥት በኩል የተለያዩ ዕገዛዎች በተለይም የማምረቻ መሣሪያዎችና መለዋወጫዎች ከቀረጥ-ነፃ የሚያገኙበት ሁኔ ተጠናክሮ ንዲቀጥል ይደረጋል። በባለሀብቶችና በሌሎች አጋር ኃይሎች አማካይነት ተስማሚ ቴክኖሎጃዎች በሊዝ/በኪራይ/በግዢ የሚቀርቡበት ሁኔ ይፈጠራል። በተስማሚ ቴክኖሎጂ ምርምርና ልማት የተፈጠሩ፣ አዶብት የተደረጉና የተኮረጁ ተስማሚ ቴክኖሎጂዎች

ለግል ባለሀብቶች የመስጠትና ድጋፍ የማድረግ ተግባር በዚህ ንዑስ ፕሮግራም አማካኝነት ይከናወናል፡፡

### 3. 2. የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ፕሮጀክት፣

ከጥሬ ዕቃ ጋር ተያይዞ የሚገኘውን ችግር ለመቅረፍና ባለሀብቶች ጥሬ ዕቃን በጥራት፣ በብዛትና በተመጣጣኝ ዋጋ ንዲያገኙ ለማድረግ የጥሬ ዕቃ ምርትና አቅርቦት የሚያድግበትን ሁኔ ማመቻቸት አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በዚህም መሠረት ከጥሬ ዕቃ አምራቾች፣ ከአርሶ አደሮች፣ ከግብርና የምርምር ተቋማት ና ከኢንዱስትሪዎች ጋር በመቀናጀትና ውል በመግባት ባለሀብቶች ጥሬ ዕቃን በጥራት፣ በብዛትና በተመጣጣኝ ዋጋ ንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

ከጥሬ ዕቃ አቅርቦት ጋር በተያያዘ መልኩ ባለሀብቶች ካሉባቸው ችግሮች ውስጥ አንዱ የጥሬ ዕቃ ግብይት ነው፡፡ የጥሬ ዕቃ ግብይትን በተመለከተ ባለሀብቶች በጋራና በማኀበር ተደራጅተው ጥሬ ዕቃው በተመጣጣኝ ዋጋ ከሚገኝበት አካባቢ በጅምላ ገዝተው የሚጠቀሙበት ሁኔ ይመቻቻል፡፡ ይህንኑ ለማመቻቸትም በየደረጃው የሚቋቋሙት የመረጃ ማዕከላት ትልቅ ገዛ ያደርጋሉ፡፡ ሌላው ከጥሬ ዕቃ ጋር በተያያዘ ያለው ችግር የትራንስፖርት ወጪ ከፍተኛ መሆን ነው፡፡ ይህንን ችግር በመሠረተ-ልማት ንዑስ ፕሮግራም አማካይነት ለመፍ ት ጥረት ይደረጋል ፡፡

ከባለሀብቶች ጋር የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ቁርኝት ያላቸውን አካላት በዝርዝር በመለየት በእያንዳንዱ የቁርኝት ደረጃ /value chain/ ላይ ያለ የጥሬ ዕቃ አምራች፣ ጥሬ ዕቃን በጥራት፣ በተመጣጣኝ ዋጋ፣ በሚፈለገው ዓይነትና መጠን እንዲያመርት ሁሉ አቀፍ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

ከጥሬ ዕቃ አኳያ ባለሀብቶች ካሉባቸው ዋንኛ ችግሮች ውስጥ አንዱ የተቀላጠፈ የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ሥርዓት ያለመኖር ነው፡፡ በግል ባለሀብቶች የሚፈለጉ ጥሬ ዕቃዎች ቢኖሩም የተቀላጠፈ የአቅርቦትና የግዥ ሥርዓት ባለመኖሩ ባለሀብቶቹ ጥሬ ዕቃን በሚፈለገው ጥራት፣ ዋጋ፣ አይነትና ብዛት የማግኘት ችግር አለባቸው፡፡ ስለሆም ባለሀብቶች በተቀላጠፈና አጭር በሆነ የጥሬ ዕቃ አቅርቦትና ግዥ ሰንሰለትና ሥርዓት አማካኝት ጥሬ ዕቃ የሚያገኙበት ሥርዓት ይመቻቻል፡፡

በተለይ የአርሶ አደሩ ምርት የሆኑ የግብርና ውጤቶች ከልማታዊ ባለሀብቱ ጋር ዘላቂ ውል (out growers scheme) በመፍጠር አስተማማኝ የገበያ ትስስር ለባለሀብቱም ለአርሶ አደሩም ስለሚሆን በዚህ ረገድ የተለየ ትኩረት ተሠጥቶ ይሠራል፡፡የአርሶ አደሩ የግብርና ውጤቶች ለፋብሪካ ወይም የውጭ ገበያ ላለው ባለሀብት መሸጥ አርሶ አደሩን ለሥራ ያነቃቃል፡፡ ይህ ሥራ በዚህ ፕሮጀክት መሠራት ያለበት ሥራ ነው፡፡

## 3.3. ኢንቨስትመንቱ በሚካሄድበት አካባቢ የሚኖረው ህብረተሰብ በልማቱ እንዲሳተፍ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮጀክት

በግል ኢንቨስትመንት ልማት ዘርፍ በእርሻና አግሮ ኢንዱስትሪ ልማቶች የጊዜያዊ ሰራተኞች የሰው ሀይል እጥረት ችግር ለማቃለል ቀዳሚና ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ የመፍትሄ አቅጣጫ በእርሻ ልማቶች አካባቢ የሚገኘውን አርሶ አደር /አርብቶ አደር/ እንዲሁም በሰፈራ ፕሮግራም ከተለያዩ አካባቢዎች ወደዚያ አካባቢ በመሄድ ሰፍረው የሚገኙ ሰፈሪዎችንና መላውን ህብረተሰብ ግንዛቤ በመፍጠር የየራሳቸውን የማሳ ስራ በማያስተጓጉል ሁኔታ በማንቀሳቀስ በየእርሻ ልማቶቹ ላይ እንዲሰማሩና በሚገኘው ገቢ የራስንና የቤተሰብን ኑሮ በማሻሻል ተጠቃሚ የሚያደርግ አሰራር ይፈጠራል፡፡ ህብረተሰቡን የመቀስቀስና የማስተማር ስራ በአካባቢው ያለው የዞንና የወረዳ የመንግስት አካል በተጠናከረ መልኩ እንዲሰራ ይደረጋል፡፡ የእርሻ ልማቶቹ የሰዉ ኃይል በሚፈልጉበት ወቅት የሚፈለገዉን ያህል ሠራተኛ በእርሻ ልማቶቹ አካባቢ ከሚገኘው አርሶ አደር /አርብቶ አደር/ እና ሌላ ህብረተሰብ ክፍል የማቅረብ ተግባር በተደራጀና ተቋማዊ በሆነ መልኩ የሚከናወንበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ አሰራሩም ወጥ በሆነ መልኩ እንዲከናወን የአሰራር ስርዓት ይመቻቻል፡፡ በእነዚህ አካባቢዎች ወይም ልማቶቹ በሚገኙባቸው ዞኖች የሰው ሀይል አቅርቦት ግብረ ኃይል እንዲቋቋምም ይደረጋል፡፡

## 3.4. የሰው ኃይል በብዛት ከሚገኙባቸው አካባቢዎች የሰራተኛ አቅርቦት ፕሮጀክት

የሰው ኃይልን በስፋት የሚፈልጉ የግል ኢንቨስትመንቶች የሚፈልጉትን የሰው ኃይል ልማቱ ከሚገኝበት አካባቢ ለማግኘት የሚያስችሉ አስፈላጊ የሆኑትን ዘዴዎች ሁሉ በመጠቀም ማግኘት ካልቻሉ ሁለተኛ አማራጭ በክልሉ በአንጻራዊ ሁኔታ የተሻለ የሰው ሀይል በብዛት ከሚገኝባቸው የክልሉ መካከለኛና ደቡብ ምዕራብ ዞኖች ይህንን የሰው ኃይል ምልመላና አቅርቦት ተግባር በተደራጀና ተቋማዊ በሆነ ሁኔታ ለማከናወን የሚችል አደረጃጀት ይመቻቻል፡፡

በአንጻራዊ ሁኔታ የተሻለ የሰው ኃይል በሚገኝባቸው አካባቢዎች በህጋዊ መንገድ ተደራጅተው ሥራና ሰራተኛ በማገናኘት ተግባር ላይ ተሰማርተው ህግና ስርዓትን በመከተል የሚሰሩ የግል ተቋማት እንዲፈጠሩና የሰው ኃይል የሚፈልጉ የግል ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የሰው ኃይል ፍላጎታቸውን እያሳወቁ አገልግሎት የሚያገኙበት የአሰራር ስርዓት ይፈጠራል፡፡

## 3.5. የግል ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የሰራተኞች አያያዝ ፕሮጀክት

የግል ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የሚያጋጥሟቸውን የሰው ኃይል እጥረት ለመቅረፍ የሚፈልጉትን የሰው ኃይል በብዛትና በብቃት ማቅረብ እንዲቻል ድርጅቶቹ ለሰራተኛው ማሟላት የሚገባቸዉን የሥራ ሁኔታዎች በጽሁፍ በማቅረብ ዉል መፈራረም የሚገባቸው መሆኑና ለሰራተኛው ማነቃቂያና ማትጊያ ስርዓት ቢዘረጋና በአጠቃላይ ምቹ የሥራ ሁኔታዎች ቢፈጠሩ የሚፈለገውን የሰው ኃይል በቀላሉ ማግኘት ይቻላል፡፡

በዚህ መሰረት የጊዜያዊ ሰራተኞችን የሙያ ደህንነትና ጤንነት መጠበቅ የመሰረታዊ ስራ ሁኔታዎችን ማክበርና ለሰራተኛ ደመወዝ በወቅቱ መክፈል በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ህግ መሰረት አስፈላጊውን የስራ ሁኔታና አገልግሎት ጥቅማ ጥቅሞችን መጠበቅና ምቹ የስራ ሁኔታ ለመፍጠር የሚያስችል አሰራር እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡
በአጠቃላይ የሰው ኃይል የሚፈልጉ የግል ኢንቨስትመንት የልማት ድርጅቶች የሚያጋጥሟቸው የሰው ኃይል እጥረት ለመቅረፍ በግላቸው የሚያደርጉት ጥረት ብቻውን የተሳካ ስራ እንዲሰሩ ሊያደርጋቸው የማይችል በመሆኑ በአካባቢው ካለው የመንግስት መዋቅርና በአንጻራዊ ሁኔታ የተሻለ የሰው ሀይል ያለበት አካባቢ ከሚገኙ የመንግስት መዋቅሮች ጋር በቅንጅት መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

# 4. የኢንቨስትመንት መሬት ዝግጅት፣ አቅርቦትና የመሰረተ ልማት ንኡስ ፕሮግራም

የግሉን ኢንቨስትመንት ልማት የማጠናከርና የማስፋፋት ጉዳይ ሲታሰብ በዋናነት የመሬት ዝግጅትና አቅርቦት የግድ አብሮ የሚታሰብ ጉዳይ ነው፡፡ ይህም የሚሆነው ለኢንቨስትመንት የልማት ሥራ መሬት ዋናው ግብአት በመሆኑ ነው ፡፡ የግሉን የኢንቨስትመንት የልማት ፕሮግራም ተግባራዊ ለማድረግና የዘርፉን የመሬት ችግር ለማቃለል በከተሞችም ሆነ በገጠር አካባቢዎች ለልማት አገልግሎቱ ይውላሉ ተብለው ከሚታሰቡ መሬቶች ጋር ተያይዘው የሚገኙ መረጃዎች ተሰብስበው በአግባቡ መጠናቀር ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በከተሞች ከተሞቹ የደረሱበትን የዕድገት ደረጃ መሰረት በማድረግ የተዘጋጀውን ማስተር ፕላንና የእድገት ፕላን አስቀድሞ ማጥናትና ይህንኑ መነሻ በማድረግ የየከተማውን ተጨባጭ ሁኔታ ባገናዘበ ሁኔታ ለግሉ ኢንቨስትመንት የሚሆን መሬት የመለየት ስራ በጋይድ ማፕ አስደግፎ መስራት ግድ ይላል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በገጠር አካባቢም ለሚካሄደው የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የሚሆኑ

ቦታዎች መለየትና በጋይድ ማፕ አስደግፎ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ ይህ ከተደረገ በኋላ በወረቀት ላይ ተቀምጦ የቀረበው ቦታ በተጨባጭ መኖሩን በመለየት የትኛው ቦታ ለምን አይነት ተግባር ሊውል እንደሚችል መጠኑንም ጭምር የለየ ጥናት መደረግ ይኖርበታል፡፡ ለግሉ ኢንቨስትመንት ልማት አገልግሎት ሊውሉ የሚችሉ ቦታዎች በየስራ መስኩ በግልጽ ተለይተው፣ ተከልለውና ለምተው የሚቀመጡበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡ በተለይም ቦታዎቹ ሲዘጋጁ ከሌላ የይዞታ ወይም የይገባኛል ክርክር ነጻ ሆነው ተዘጋጅተው እንዲጠብቁ ይደረጋል፡፡

በገጠር ለኢንቨስትመንት በተከለለ መሬት ላይ ሊመረት የሚችል ምርት ወይም ሊለማ የሚገባው የልማት አይነት በአግባቡ ተለይቶ ከተገቢው መረጃ ጋር ተደራጅቶ እንዲዘጋጅ ይደረጋል፡፡ በግሉ የኢንቨስትመንት ዘርፍ በገጠር የሚከናወኑ የኢንቨስትመንት ተግባራት የእያንዳንዱን አካባቢ ተጨባጭ ሥነ-ምህዳራዊ ሁኔታን ባገናዘበ መልኩ እንዲከናወን ይደረጋል፡፡ በገጠር ለሚከናወኑ የግል ኢንቨስትመንት ልማት ስራዎች የሚዘጋጀው መሬት እያንዳንዱ አካባቢ ካለው ተነጻጻሪ ጠቀሜታና አግሮ ኢኮሎጂያዊ ጠቀሜታ አንጻር እየተለየ ይዘጋጃል፡፡ ልማቶቹም የአካበባቢውን አርሶ አደርና አርብቶ አደር ኑሮ በተለያየ ሁኔታ ሊለውጡ የሚችሉና የቴክኖሎጂና የአሰራር ስርዓት ሽግግርን ሊያመጡ የሚችሉ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ በመሆኑም ለግል ኢንቨስትመንት ልማት የሚሆኑ ቦታዎች በገጠር አካባቢዎች ሲዘጋጁ ይህንኑ ከግንዛቤ ውስጥ ያስገቡ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

በከተሞችም እንደ ዕድገት ደረጃቸው በግሉ ኢንቨስትመንት ሊሰሩ የሚገባቸው ስራዎች ተለይተው ከተገቢው መረጃ ጋር ተደራጅተው እንዲዘጋጁ ይደረጋል፡፡ ይህ በሚደረግበት ጊዜ በተቻለ መጠን እንደየስራው አይነት የከተማውን ዉበት የሚጠብቅ እና ቦታ ቆጣቢ የሆነ አማካይ የግንባታ ቦታ መጠንን ከግምት ውስጥ ያስገባ ዝግጅት ቦታዎቹ በሚዘጋጁበት ጊዜ ተግባራዊ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ ስለሆነም በከተማ ዉስጥ ለሚገነቡ ግንባታዎች ቦታን በቁጠባ መጠቀም ፤የከተማዉን ዉበት በማያበላሽ መልኩ ደረጃውን በጠበቀና ለመጪው ትውልድ ጭምር ጥሩ መሰረት ለመጣል ይቻል ዘንድ ወደ ጎን ከሚሰፉ ግንባታዎች ይልቅ ወደ ላይ ለሚያደርጉ ሥራዎች ልዩ ትኩረት ይሰጣል፡፡

በተወሰኑ ከተሞች ተዘጋጅተውና ለምተዉ የሚገኙ የኢንዱስትሪ መንደሮችም ላይ በተለይም የግብርናውን ምርት በግብዓትነት በመጠቀም እሴት ጨምረው ለሚሰሩና ምርታቸውን ለውጭ ገበያ ለሚያቀርቡ ልዩ ትኩረት ይሰጣል፡፡ በኢንዱስትሪ መንደሮች ሳይሟሉ ያሉ የመሰረት ልማት አዉታሮች ተለይተው እንዲሟሉ ይደረጋል፡፡

በዚህ መልኩ በከተማም ይሁን በገጠር ለኢንቨስትመንት ልማት የተዘጋጁ ቦታዎች አስፈላጊውን የመሰረተ-ልማት አገልግሎት የሚያገኙበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡ በዚህ ረገድ ተጠቃሚዎቹ አቅማቸውን ባገናዘበ ሁኔታ በጋራ በመደራጀት ወይም በግል መሰረተ ልማት መዘርጋት የሚችሉበት ሁኔታ ቅድሚያ ተሰጥቶ የማስተባበር ስራ ይሰራል፡፡ በዚህ ዙሪያ መንግስትም የሚጠበቅበትን ድጋፍ ያደርጋል፡፡ ምክንያቱም በክልሉ አጠቃላይ ገፅታና በኢንቨስትመንት አፈጻጸም ችግር ዙሪያ ቀደም ሲል በስፋት እንደተመለከተው የመሠረተ-ልማት ችግር ለግሉ ኢንቨስትመንት መስፋፋት እንቅፋት ከሆኑት ዋና ዋና ችግሮች መካከል አንዱ ነው ፡፡ መሠረተ-ልማት ብዙ ጉዳዮችን የሚያጠቃልል ሲሆን በዚህ ንዑስ ፕሮግራም በመሰረተ ልማት በኩል ማተኮር የተፈለገው በኢኮኖሚ መሠረተ-ልማት ላይ ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም በመንገድና የመንገድ ትራንስፖርት፣ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት፣ የኤሌክትሪክ ይልና የው አገልግሎት ላይ ይህ ንዑስ ፕሮግራም ያነጣጥራል ፡፡

ስለሆነም ባለሀብቶች መረጃን ወደሚፈለገው አካል በአፋጣኝ ለማስተላለፍ የሚያስችል የመገናኛ ሥርዓት ከሌላቸው፣ ምርቶቻቸውን ወደገበያ፣ ግብዓቶችን ደግሞ ወደ የፕሮጀክቶቻቸው በሚፈለገው ፍጥነትና ተወዳዳሪ በሆነ ዋጋ ማንቀሳቀስ ካልቻሉ፣ ንዲሁም በዋጋ ተወዳዳሪ የሆነ የ ይል ምንጭ ካላገኙ በገበያ ተወዳዳሪ መሆን አይችሉም፡፡

ይህም ብቻ ሳይሆን በክልሉ የመሠረተ-ልማት ችግር ካልተወገደ በስተቀር የውጭ ኢንቨስትመንትንም በብቃት መሳብ አይቻልም፡፡ ይህም በመሆኑ አሁን የሚ ዩትን የመሠረተ-ልማት ችግሮች ደረጃ በደረጃ በተቀናጀ አሠራር ለማቃለል የሚያስችሉ ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡ የሚገነባውም መሠረተ-ልማት አሁን ላለው ችግር ማቃለያ ብቻ ሳይሆን ወደፊት ይመጣል ተብሎ ለሚጠበቀዉም የኢንቨስትመንት ልማት ጭምር የሚያገለግል ይሆናል ፡፡

በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ካላቸው ዝቅተኛ የፋይናንስ አቅም አኳያ እነዚህን መሠረተ ልማቶች በእራሳቸው አቅም ብቻ ሊያሟሏቸው አይችሉም፡፡ ይህንም ችግር በዋነኝነት ለመፍ ት መንግስት፣ ህብረተሰቡ ና የግል ባለሃብቶች በቅንጅት ንዲረባረቡ ይደረጋል ፡፡

የግል ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም ሥራ አጥነትንና ድህነትን ከመቀነስ አኳያ ያለውን ጠቀሜ ኀብረተሰቡ ተገንዝቦ መሰረተ ልማትን ለማዳረስ የሚደረገውን ጥረት ንዲደግፍና ንዲሳተፍ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም የመሰረተ ልማት ችግርን ለመፍ ት በመንግሥትና በህብረተሰቡ ከሚደረገው ጥረት ባሻገር ባለሀብቶች በየኢንቨስትመንት ቀጠናዎቻቸው ተደራጅተው ያለባቸውን የመሰረተ ልማት ችግር በራሳቸው አቅም ለመፍ ት ጥረት ንዲያደርጉ የማመቻቸትና የማበረ ት ሥራዎችም ይከናወናሉ፡፡

በአጠቃላይ መልኩ ሲ ይ በክልሉ የግል ባለሀብቶች ያለባቸው የመሰረተ ልማት ችግር ሰፊ ንደመሆኑ መጠን አቅርቦቱን በመጠንም ሆነ በጥራት ለማሳደግ የብዙ አካላትን ጥረትና ቅንጅት የሚፈልግ ብቻ ሳይሆን ጊዜም የሚወስድ ነው፡፡ በዚህም መሠረት ሥራው በአጭርና በመካከለኛ ጊዜ በመለየት ይከናወናል፡፡ የመሰረተ-ልማት ንዑስ ፕሮግራምን ለማሳካትና ይበልጥ ውጤ ማ ለማድረግ ንዲቻል የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ይኖራሉ፡፡

ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ከግሉ ኢንቨስትመንት ልማት ጋር ቁርኝት ለመፍጠር በሚቻልበት አቅጣጫ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፡፡ በዚህ ረገድ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የመስሪያ ቦታና ቤት ችግር ከመቅረፍ አኳያ ዕቅድ ነድፈው በከተሞች አካባቢ ለሚሰሩ የግል ኢንቨስትመንት ፕሮግራሞች መሬት አግኝተው ወደ ልማቱ ሥራ የሚገቡበት የተለየ ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

ለግል ኢንቨስትመንት ልማት የቦታ ዝግጅትን በተመለከተ በከተሞችም ሆነ በገጠር የቦታ ዝግጅቱን የተቀላጠፈ ለማድረግ ቦታዎቹ በሚዘጋጁበት ጊዜ የአካባቢው ህብረተሰብ በአግባቡ እንዲሳተፍበት ይደረጋል፡፡

ለግሉ ኢንቨስትመንት አገልግሎት ተለይቶና የተከለለው አስፈላጊው መሠረተ-ልማት ተሟልቶለት የተዘጋጀው መሬት በየደረጃዉ ለሚገኝ የኢንቨስትመንት አስፈጻሚ አካል ከተላለፈ በኋላ አስፈላጊው የማስተዋወቅ ሥራ ተሠርቶ ተገቢዉን መስፈርት አሟልተው ለሚቀርቡ ባለብቶች የማልማት ብቃት፣ የሚያቀርቡትን የፕሮጀክት ዕቅድ መነሻ ሀሳብ፣ ወዘተ በመገምገም በአንድ ማዕከል አገልግሎት አሰጣጥ መርሀ መሬቱን የሚረከቡበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡ ስለሆነም በከተማም ሆነ በገጠር ለግሉ ኢንቨስትመንት ልማት ተዘጋጅተው የሚቀርቡ መሬቶችን ለግሉ ኢንቨስትመንት አገልግሎት እንዲውሉ የማድረግ ተግባርን በተመለከተ መሬቱ ለአልሚ ባለሀብቶች የሚሰጥበት የአንድ ማዕከል አገልግሎት ሥርዓት ይበጃል፡፡ በዚህ ረገድ የአልሚዉ ጊዜና ወጪ በሚቆጥብ መልኩ የመሬት አቅርቦቱ ተግባር በተጠናከረ ሁኔታ በዚህ ፕሮግራም ላይ ከተቀመጡት ሌሎች ንዑሳን ፕሮግራሞች ጋር በአንድነት በአንድ ማዕከል አቅርቦት ይከናወናል፡፡ የኢንቨስትመንት መሬት አሠጣጥ ሂደትን ፍትሃዊ ለማድረግ ለአንድ ለኢንቨስትመንት ለተከለለ መሬት በተመሣሣይ ጊዜ ከአንድ በላይ ባለሀብት በሚቀርብበት ጊዜ ባለሀብቶችን በማወዳደር የሚሰጥበት ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

በግሉ የኢንቨስትመንት ልማት የቦታ ዝግጅትና አቅርቦትና መሠረተ-ልማት ጋር የተያያዙ ከላይ በዝርዝር የቀረቡ ስራዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ይህን የግሉን የኢንቨስትመንት ልማት የቦታ ዝግጅት አቅርቦትና የመሠረተ-ልማት ንዑስ ፕሮግራምን ለማሳካትና ይበልጥ ዉጤታማ ለማድረግ እንዲቻል በንዑስ ፕሮግራሙ ስር በዋናነት የሚከተሉት ፕሮጀክቶች ይኖራሉ፡፡

## 4.1. የገጠር መሬት ዝግጅትና አቅርቦት ፕሮጀክት

የዚህ ፕሮጀክት ዋናው ዓላማ ለግሉ ኢንቨስትመንት ልማት የሚዉል የገጠር መሬት የሚዘጋጅበትን ግልጽ አሰራር ማስቀመጥ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ለግሉ ኢንቨስትመንት ልማት የሚሆኑ የገጠር መሬቶች በእያንዳንዱ አካበቢ የአካባቢውን ተነጻጻሪ ሥነ-ምህዳራዊ ሁኔታን ባገናዘበ መልኩ ይዘጋጃል፡፡ የገጠር መሬት ለግሉ ኢንቨስትመንት ልማት በሚዘጋጅበት ጊዜ በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙ የገጠር መሬትን የሚያስተዳድሩ አካላት በባለቤትነት ይሳተፋሉ፡፡ ዝግጅቱንም በአግባቡ እንዲመሩት ይደረጋል፡፡ መሬት በዚህ መልኩ ሲዘጋጅ በየአካባቢው ሊኖር የሚገባውን ስፔሻላይዜሽንና ዳይቨርሲፊኬሽን እንዲሁም የመንግስት የልማት ትኩረት አቅጣጫ መሰረት ባደረገ መልኩ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ መሬቱ የሚገኝበት አካባቢ ህብረተሰብም በመሬት መከለልና ማዘጋጀት ስራው ይሳተፋል፡፡ በዚህ አይነት መንገድ ተለይቶ ለግሉ የኢንቨስትመንት ልማት የተከለለው መሬት ተገቢው ኢንቨስተር መጥቶ አስፈላጊዉን በማሟላት ወደልማቱ እስኪገባ ድረስ ጥበቃ ይደረግለታል፡፡ የገጠር መሬትን ለግሉ የኢንቨስትመንት ልማት ለማዘጋጀት እንዲቻል ለዚሁ ስራ ትኩረት ሰጥቶ የሚሰራ ተቋማዊ አደረጃጀት ይፈጠራል፡፡

## 4.2. የከተማ መሬት ለግሉ ኢንቨስትመንት ልማት ዝግጅትና አቅርቦት ፕሮጀክት

የዚህ ፕሮጀክት ዋናው ዓላማ ለግል ኢንቨስትመንት ተግባር የሚዉል የከተማ ቦታ የሚዘጋጅበትን ግልጽ አሰራር መዘርጋት ነው፡፡ የከተማ መሬት ለግሉ ኢንቨስትመንት ልማት በሚዘጋጅበት ጊዜ በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙ የከተማ መሬቶችን የሚያስተዳድሩ አካላት በባለቤትነት ይሳተፋሉ፡፡ ዝግጅቱንም በአግባቡ እንዲመሩት ይደረጋል፡፡ በዚህ መሰረት በእያንዳንዱ ከተማ የከተማውን ማስተር ፕላንና የእድገት ደረጃ መሰረት ባደረገ መልኩ ለግሉ ኢንቨስትመንት ልማት የሚውል ቦታ እንዲዘጋጅ ይደረጋል፡፡ በተለይም በየከተሞቹ ለሪልስቴት፣ ለሆቴልና ቱሪዝም፣ ለንግድ ማዕከላት ግንባታ ወዘተ የሚዉሉ ቦታዎች ተከልለዉና ተዘጋጅተዉ እንዲቀርቡ ይደረጋል፡፡ የከተሞችን ደረጃ ከማሰደግና ከተሞችን ከማደስ አኳያ ያረጁና የደከሙ የከተማ መንደሮች የተቀናጀ የከተማ ልማት ፕሮግራም እየተዘጋጀላቸው እንዲታደሱ ቦታው ለግል ኢንቨስትመንት ልማት ክፍት እንዲሆን ይደረጋል፡፡ በከተሞች ቁልፍ ቦታዎች የሚገኙ፣ ያረጁና የደከሙ በመንግስት ይዞታ ሥር የሚገኙ ቤቶች የከተማውን የዕድገት ፕላን መስረት ባደረገ መልኩ ለግሉ የኢንቨስትመንት ልማት ተሰጥተው እንዲለሙ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ፡፡

## 4.3. ለኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም የኢንዱስትሪ መንደር ዝግጅትና አቅርቦት ፕሮጀክት

የዚህ ፕሮጀክት ዋና ዓላማ በመንግስት ትኩረት ለተሰጣቸው በኤክስፖርት ላይ ለተሰማሩና በተለይም የግብርና ምርቶችን በግብዓትነት የሚጠቀሙ አግሮ ኢንዱስትሪዎች በስፋት የሚገቡባቸው ኢንዱስትሪ መንደሮች በየአካባቢው እንዲዘጋጅ ማድረግ ነው፡፡ በዚህ መሰረት እስከ አሁን ድረስ በየአካበቢዉ በተዘጋጁ ኢንዲስትሪ መንደሮች ሊገቡ የሚገባቸው የኢንዱስትሪ አይነቶች መለየት የዚህ ፕሮጀክት አካል ይሆናል፡፡ በመሆኑም እስከአሁን የተዘጋጁ ኢንዱስትሪ መንደሮች ያሉበት ደረጃ ግምገማ ይደረጋል፡፡ ስኬቶቻቸውና ያጋጠሟቸው ችግሮች ተለይተው እንዲቀርቡ ይደረጋል፡፡ በዚህ መነሻ በነባር ኢንዱስትሪ መንደሮች ላይ ያሉ ችግሮች ተለይተዉ የሚፈቱበት መንገድ ይመቻቻል፡፡ መሰረተ ልማት ያልተዘረጋላቸው የኢንዱስትሪ መንደሮች ተለይተው መሰረተ ልማት እንዲዘረጋላቸዉ ይደረጋል፡፡ የኢንዱስትሪ መንደር የሚስፈልጋቸው አካባቢዎች ተለይተው ተጨማሪ ኢንዱስትሪ መንደሮች ተዘጋጅተው እንዲለሙ ይደረጋል፡፡ የኢንዱስትሪ መንደሮቹን በተደራጀ ሁኔታ የሚመራና የሚያስተዳድር አካል ይፈጠራል፡፡

## 4.4. ለግሉ ኢንቨስትመንት ልማት መሬት አሰጣጥ ፕሮጀክቶች

የዚህ ፕሮጀክት ዓላማ በከተሞች፣ በኢንዱስትሪ መንደሮችም ሆነ በገጠር ለግል ኢንቨስትመንት ልማት ተከልለዉ የተዘጋጁ መሬቶች ለግሉ ኢንቨስትመንት ፕሮግራም እንዴት መሰጠት እንዳለበት ግልጽ የሆነ የአሰራር ስርዓት ማስቀመጥ ነው ፡፡ በዚህ መሰረት በከተማም ሆነ በገጠር ለኢንቨስትመንት ተግባር እንዲዉሉ ተለይተዉ የተዘጋጁ መሬቶች ለባለሀብት የሚሰጡበት ግልጽ የሆነ የአሰጣጥ መስፈርትና የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ የገጠር፣ የከተማም ሆነ በከተሞች የሚገኙ የኢንዱስትሪ መንደሮች ለግሉ የኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም የሚዘጋጁ ቦታዎች በተሟላ መረጃ ተደግፈው በየደረጃው ላለው የኢንቨስትመንት መ/ቤት እንዲተላለፍ ተደርጎ የኢንቨስትመንት መ/ቤት አስፈላጊ የሆነ የማስተዋወቅ ስራ በመስራት አልሚ ባለሀብት በሚመጣበት ጊዜ በአንድ ማዕከል አገልግሎት አሰጣጥ መርህ መሰረት ከሌሎች አገልግሎቶች ጋር መሬቱን ለአልሚ ባለሀብት ይሰጣል፡፡ ለኢንቨስትመንት አገልግሎት ተከልለው ከተገቢ መረጃ ጋር ለኢንቨስትመንት መ/ቤት የተላለፉ የገጠር ፣ የከተማም ሆነ በከተሞች የተዘጋጁ የኢንዱስትሪ መንደሮች አስተዳደር በሚመለከተው የኢንቨስትመንት መ/ቤት በኩል ይሆናል፡፡ ለኢንቨስትመንት አገልግሎት ተዘጋጅተው ለኢንቨስትመንት መ/ቤት የተላለፉ መሬቶች ቦታዎቹ የሚጠይቁትን አይነት ልማት የሚያከናዉን አካል የሚያገኙበት አግባብ እንዲፈጠር ሁኔታዎች ይመቻቻሉ፡፡ ለግል ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም በሚሰጡ ቦታዎች ላይ ልማቱ ስለሚካሄድበት ሁኔታም ግልጽነት እንዲኖር የሚያስችል አሰራር ይዘረጋል፡፡

## 4.5. የመንገድና የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ፕሮጀክት፣

በፌዴራል፣ በክልል፣ በዞንና በወረዳ ደረጃ በሚገኙ የመንግሥት አካላት አማካይነት ንደየደረጃቸውና አቅማቸው ከፍተኛ ወጪን ከሚጠይቁ መንገዶች አንስቶ መለስተኛ መጋቢ መንገዶችን ስከ ማስፋፋት ያሉ ሥራዎች ተጠናክረው ንዲሰሩ ይደረጋል::

በክልሉ ጥራ ቸውን የጠበቁ መንገዶች አለመኖርና የመንገድ መረባችን ጅግ በጣም ውስን መሆኑ በባለሀብቶች ላይ የትራንስፖርት ወጪና ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ ንዲጨምር አድርጓል። ይህንን ችግር ለማቃለል መንግስት ባለፉት ዓመታት ለመንገድና የመንገድ ትራንስፖርት ሥራ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ባለፉት ዓመ ት የመንገዶችን ደረጃ ለማሻሻልና መጠናቸውንም ለመጨመር ከፍተኛ ወጪ በማውጣት ሲንቀሳቀስ ንደቆየ ሁሉ ወደፊትም ይህንኑ አጠናክሮ ይቀጥላል ::በተለይም የክልሉ ገጠር መንገድ ባለስልጣንና የፌዴራል መንገዶች ባለስልጣን በቅንጅት በመንቀሳቀስ በክልሉ ከፍተኛ የኢንቨስትመንት ፖቴንሻል ወዳለባቸው አካባቢዎች መንገዶች ንዲገነቡ ይደረጋል ::

ይህ ፕሮጀክት በክልሉ ቀደም ሲል ተጀምረው ወይም ቅደው በሂደት ላይ የሚገኙትን መንግስ ዊ የመንገድና የመንገድ ትራንስፖርት ፕሮጀክቶችንና ፕሮግራሞችን ለመተካት የ ሰበና የ ቀደ ሳይሆን በክልሉ ውስጥ ለማንኛውም የልማት ተግባር ስበው የተወጠኑና የተከናወኑም የሚገኙትን ወይም በሂደት ላይ የሚገኙትን ተመሳሳይ ፕሮጀክቶች በቅንጅት በማራመድ ለግል ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም የሚጠቀሙበትን ሁኔታ ለማጎልበትና ለማመቻቸት ነው::

ንዲሁም ስካሁን ግንዛቤ ያልተወሰደባቸውና ቅድሚያ ያልተሰጣቸው ግን በክልሉ የመንገድና ትራንስፖርት ችግርን የሚያባብሱ ሁኔ ዎችን በመለየት ችግሮቹን ለማቃለል የሚከናወኑ ሥራዎች ይኖራሉ :: ከአጭር ጊዜ ዕቅድ አንፃር በቅንጅት ሊሠሩ የሚችሉ መጋቢ መንገዶችን በሴፊቲኔት ፕሮግራም፣ በምግብ ለሥራ፣ የአካባቢዉ ሕብረተሰብ የጉልበት አስተዋጽኦ ንዲያደርግ በማድረግና፣ የአካባቢዉ አስተዳደር ሥራውን የማደራጀትና የማስተባበር ተግባራት በማከናወን የሚፈፀም ሆኖ ባለሀብቶችም በዚህ መስክ ንዲሳተፉ በማበረ ትና ድጋፍ በማድረግ የመንገድና የትራንስፖርት ችግሮችን ከሕብረተሰቡ ጋር በቅንጅት ለመፍ ት ጥረት ይደረጋል::

ባለሀብቶችን በየኢንቨስትመንት ቀጠናዎቻቸው በማደራጀት ችግሩን በተደራጀ ሁኔ ከመንግስትና ከሕብረተሰቡ ጋር ተቀናጅተው ንዲፈቱ ይደረጋል:: ቅንጅት ሲባል ባለሀብቶች ጉልበታቸውን፣ ገንዘባቸውን፣ ውቀ ቸውንና ጊዜያቸውን በማቀናጀት በጋራ ያሉባቸውን የመሠረተ-ልማት ችግሮች ለማቃለልና የኢንቨስትመንት ዓላማቸውን ለማሳካት የሚፈጥሩት ጊዚያዊ ወይም ቋሚ ትብብር ማለት ነው::

## 4.6 የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፕሮጀክት፣

በአሁኑ ወቅት የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ከኮምፒዩተሮችና ከኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ጋር በመጣመር ምርትና ምር ማነትን ማሻሻል ብቻ ሳይሆን የትምህርትና ስልጠና አገልግሎትን፣ የሕክምና አገልግሎትን፣ የመረጃ አገልግሎትን ወዘተ ከርቀት በመለዋወጥ ንዲሰጡና ጥራቱ ጅግ አስተማማኝ በሆነ መንገድ ንዲፈፀም የሚያስችል፣ የንግድ ንቅስቃሴዎች በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ በቀላሉ የሚከናወንበት ዋነኛ መሣሪያ ሆኗል ።

መንግስትም ይህንን በመገንዘብ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎትን ለማስፋፋትና ለማሻሻል የተለያዩ ጥረቶችን እያደረገ ይገኛል ። የቴሌፎን መስመሮችን ብዛትና ስርጭት ማሳደግ፣ የሞባይል ቴሌፎን አገልግሎት ማስፋፋት፣ የኢንተርኔትና የብሮድባንድ አገልግሎቶችን ማስጀመር፣ ወዘተ፣ በምሳሌነት የሚጠቀሱ መንግስ ዊ ክንውኖች ናቸው። በተመሳሳይ ሁኔታ በክልሉ ውስጥ ነኝህና ሌሎች መሰል የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች ባልተዳረሱባቸው ለግል ኢንቨስትመንት ከፍተኛ ፖቴንሻል ባለባቸው አካባቢዎች ሁሉ ለማዳረስ ጉዳዩ ከሚመለከ ቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ይሠራል።

በክልሉ ገጠራማ አካባቢዎች ስለሚበዙበትና ሰፋፊ የግብርናና የቱሪዝም ኢንቨስትመንቶች በነዚሁ የገጠር አካባቢዎች በብዛት ስላሉ በ ነኝህ አካባቢዎች ሽቦ አልባ የስልክ መስመሮችና፣ የሞባይል አገልግሎት በአስተማማኝ ሁኔ ንዲዳረስ የሚያስችሉ ሥራዎች በቅንጅት ይከናወናሉ ።

ሆኖም ይህ ፕሮጀክት ቀደም ሲል ተጀምረው ወይም ቅደው በሂደት ላይ የሚገኙትን መንግስ ዊ የቴሌኮሙኒኬሽን ፕሮጀክቶችንና ፕሮግራሞችን ለመተካት የ ሰበና የ ቀደ ሳይሆን በክልሉ ውስጥ ለማንኛውም የልማት ተግባር ስበው የተወጠኑና የተከናወኑም የሚገኙትን ወይም በሂደት ላይ የሚገኙትን ተመሳሳይ ፕሮጀክቶች በቅንጅት በማራመድ ለግል ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም የሚጠቅሙ ጎኖችን የማጎልበትና የማመቻቸት ተግባራት ይከናወናሉ ።

የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎትን የማስፋፋት ሥራ በግንባ ወቅትም ሆነ ግንባ ው ተጠናቆ አገልግሎቱ በሚሰጥበት ጊዜ ለብዙ ሠራተኞች የሥራና ለብዙ ባለሀብቶች ደግሞ የኢንቨስትመንት ዕድልን የሚከፍት በመሆኑ የግል ኢንቨስትመንትን በማጠናከር ከዘርፉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል ።

## 4.7 የኤሌክትሪክ ይል አገልግሎት ፕሮጀክት፣

በክልሉ የግል ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ለማጠናከር በዋጋ ተወዳዳሪ የሆነ የኤሌክትሪ ይል አቅርቦት መኖር በጣም ተፈላጊ ነው። በአሁኑ ወቅት በግንባ ላይ የሚገኙና በቅርቡ ግንባ ዎቻቸውን የሚጀምሩ የ ይድሮ-ኤሌክትሪክ ማመንጫ፣ ማከፋፈያና ማሰራጫ በተለይም በክልላችን የተጀመረው

3ው የግልገል ጊቤና የጎጀብ ይድሮ-ኤሌክትሪክ ፕሮጀክቶች ግንባ ሲጠናቀቅ በኤሌክትሪክ ይል አቅርቦት በኩል የሚ ዩ የኢንቨስትመንት ችግሮች ይቃለላሉ::

ከፍተኛ የኢንቨስትመንት ፖቴንሻል ወዳለባቸው የክልሉ አካባቢዎች ከፍተኛ አቅም ያላቸው የኤሌኬትሪክ ይል ተሸካሚ መስመሮችን የመዘርጋትና አገልግሎቱን የመስጠት ሥራዎች በኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ይል ኮርፖሬሽንና በክልሉ መንግስት በቅንጅት ይከናወናሉ:: ንዲሁም የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ይል ኮርፖሬሽን ከሚያከናውናቸው የ ይል ማመንጫትና ከፍተኛ መስመሮች የመዘርጋት ሥራ ባሻገር በክልሉ ትናንሽ ከተሞችና ገጠሮች የዲዚል ጀነሬተሮች፣ከፀሐይና ከነፋስ የኤሌክትሪክ ይል የሚያመነጩ ቴክኖሎጂዎችን፣ትናንሽ የሐይድሮ-ኤሌክትሪክ ማመንጫ ተቋማትን በመጠቀም አገልግሎቱን ለማስፋፋት ጥረት ይደረጋል ::

በተጨማሪም የግል ባለሀብቶች የማስተላለፊያና የስርጭት መስመሮችን በመዘርጋት፣ ለዚሁ ሥራ የሚያስፈልጉትን ዕቃዎችን በማምረት ላይ ያለውን ሰፊ የኢንቨስትመንት ዕድል ንዲጠቀሙ የማበረ ት ሥራዎች ይከናወናሉ:: ነዚህ ሥራዎች በሚካሄዱበት ወቅትና ግንባ ው ተጠናቆ አገልግሎቱ በሚሰጥበት ጊዜ ሰፊ የሥራ ዕድል ንደሚፈጥርም ይ መናል ::

## *4.8. የው አገልግሎት ፕሮጀክት፣*

የንፁህ መጠጥ ው አቅርቦት በከተማም ሆነ በገጠር ጤንነቱ የተጠበቀ ዜጋ ንዲኖር ለማድረግ ወሳኝ ከመሆኑም ባሻገር ለግል ኢንቨስትመንት ልማትም አስፈላጊ ከሆኑ ጉዳዮች አንዱ ነው :: ክልላችን በተፈጥሮ ው የ ደለ ቢሆንም ለመጠጥ፣ ለኢንዱስትሪና ለንግድ የሚያስፈልገውን የው አቅርቦት ንኳንስ በገጠር በከተማም ቢሆን በሚፈለገው መጠንና ጥራት ለማዳረስ አልተቻለም ::

በዚህ ረገድ የሚ የው አንዱ ችግር የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ለማዳረስ የሚያስፈልግ የኢንቨስትመንት ፋይናንስ ሲሆን ሌላው ችግር የው አገልግሎት ተቋሞች የሥራ አመራር ችግር ነው:: በክልሉ በሚገኙ ከተሞች የው አገልግሎት ሥራ አመራር በከፍተኛ ደረጃ መሻሻል ይኖርበ ል:: ይህ በሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራሞች መተግበር ሊቀረፍ የሚችል ቢሆንም የግል ኢንቨስትመንትን የሚያቀጭጩ ችግሮች ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ንዲቃለሉና ትኩረትም ንዲሰጣቸው ጉዳዩ ከሚመለከ ቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል::

የፋይናንስ ችግሮችን ለማቃለል የአገልግሎት መሻሻልና የሕብረተሰቡን ግንዛቤ የማሳደግ ሥራዎች ተጠናክረው ይከናወናሉ:: ሕብረተሰቡ ጥራት ያለውና ቀልጣፋ አገልግሎት ንዲያገኝ የማድረግ፣ ተገቢውን ክፍያም ንዲከፍሉ የማድረግና ጠንካራ የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት የመዘርጋት ሥራዎች በተመሳሳይ ሁኔ ተጠናክረው ይሠራሉ:: ሆኖም በዚህ መልክ የሚሰባሰበው ገቢ የው አገልግሎት

ተቋማትን የፋይናንስ አቅም የሚያሻሽል ቢሆንም ተፈላጊውን የመጀመሪያ ኢንቨስትመንት በሚፈለገው መጠንና ፍጥነት ለማሰባሰብ የሚያስችል አይሆንም ፡፡

በመሆኑም መንግስት መነሻ የኢንቨስትመንት ካፒ ል በመመደብ ለከተማ ማዘጋጃ ቤቶች በመጠነኛ ወለድ ብድር የሚሰጥበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡በዚህ መሰረት ገንዘቡ በብድር መልክ የተሰጠና ብድሩ የተሰበሰበ በክልሉ የሚገኙ በርካታ ከተሞችን የማዳረስና አካባቢውን ለግል ኢንቨስትመንት ምቹ የማድረግ ሥራዎች ተጠናክረው ይሠራሉ ፡፡

## 5. የጥራት ስታንዳርድ ማሻሻያና የውጭ ገበያ ንዑስ ፕሮግራም

በተለያዩ የኢኮኖሚ ሴክተሮች የተሰማራው የክልላችን የግል ኢንቨስትመንት በሥራ ዕድል መፍጠር፣ በድህነት ቅነሣና በአጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገት ለውጥ ለማምጣት በሚደረገው የትግል ሂደት ውስጥ የሚኖረው ድርሻ ከፍተኛ እንደሆነ ይታመናል፡፡

ይህ ሚና በተፈለገው ደረጃ እውን ሊሆን የሚችለው ዘርፉ በምርት ጥራቱና በምርታማነቱ የሚፈገለውን የብቃት ደረጃ ይዞ ሲገኝ ነው፡፡ ብቃት የሚገለጸዉ በአብዛኛው በማምረቻ መሣሪያዎች አመራረጥ፣ በግብዓት አመራረጥና አጠቃቀም፣ በሰው ኃይል አጠቃቀምና ሥራ አመራር ብቃት ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ በተለያዩ ጊዜያት ከተደረጉ ጥናቶች ማረጋገጥ እንደተቻለው የክልላችን የግል ኢንቨስትመንት በማምረቻ መሣሪያዎች የጥራት ጉድለት፣ በአመራረት ጥራትና ምርታማነት፣ በሥራ አመራር ብቃት ማነስና ከመረጃ ጉድለት ጋር ተያይዞ በሚከሰት ችግር፣ በፋይናንስ አጠቃቀምና ማኔጅመንት ብቃት ማነስ ምክንያት የጥራት ስታንዳርድ የማያሟሉ ምርቶችና አገልግሎቶች የሚቀርቡ በመሆኑ የውጭ ገበያ ሰብሮ መግባት ያልተቻለበት ሁኔታ ይታያል፡፡ የውጪ ገበያን ሰብሮ ለመግባት እንደ ችግር ከሚታዩ ጉዳዮች መካከል የውጪ ገበያ ተሞክሮ ውስን መሆን፣ የመረጃ እጥረትና የውጪ ገበያ መረጃና ድጋፍ ሰጪ አካል በአግባቡ ተደራጅቶ ያለመኖር በዋና ዋናዎቹ ተራ የሚመደቡ ናቸው፡፡

ስለሆነም እነዚህን መነሻ ምክንያቶች በማድረግ ችግሮቹን ለመቅረፍ የሚያስችል ንዑስ-ፕሮግራም የተቀረጸ ሲሆን ይህንን ንዑስ-ፕሮግራም ስኬታማ ለማድረግ እንዲቻል ከዚህ በታች የተመለከቱት ፕሮጀክቶች ተቀርፀዋል፡፡

### 5.1. ኢንቨስተሮችንና ባለሙያዎችን በጥራት ሥራ አመራር የማብቃት ፕሮጀክት

በግብርና፣ በአግሮ ኢንዱስትሪ፣ በኢንዱስሪና በአገልግሎት አሰጣጥ ወዘተ የተሰማሩት ኢንቨስተሮችና የየሴክተሩ ባለሙያዎች ብቃታቸውን ለማሳደግ አግባብ ያለው ሙያ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የማሰልጠንና የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራዎች ይሠራሉ፡፡

## 5.2. የጥራት ስታንዳርድ አዘገጃጀትና ክትትል ፕሮጀክት

በክልሉ በተሰማሩ ባለሀብቶች የሚመረቱ ምቶችና የሚሰጡ አገልግሎቶች በአገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ መሆን እንዲችሉ የጥራት መስፈርቶች የሚዘጋጁበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡ በተለያዩ ዘርፎች የተሰማሩና የሚሰማሩ የግል ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የሚያመርቱአቸዉ ምርቶችና የሚሰÔóቸዉ አገልግሎቶች ዓለም አቀፍ ደረጃ ያሚሉ እንዲሆኑ ለማድረግ የደረጃ መዳቢ ባለሥልጣን ተገቢዉን ድጋፍና ክትትል በማድረግ እንዲያግዛቸዉ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ፡፡

## 5.3 የውጭ ገበያና የገበያ መረጃ የማፈላለግና ድጋፍ አሰጣጥ ፕሮጀክት

የዚህ ፕሮጀክት ዓላማ በክልሉ በውጭ ገበያ የተሰማሩና ሊሠማሩ የሚፈልጉ የግል ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የውጭ ገበያና የገበያ መረጃን የሚያገኙበትና ተጠቃሚ የሚሆኑበትን አሠራር መፍጠርና በዚሁ ዘርፍ ተገቢውን ድጋፍ መስጠት ነው፡፡

ፕሮጀክቱ ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት በአሁኑ ጊዜ ያለው የውጭ ገበያ ሁኔታ በከፍተኛ ውድድር ላይ የተመሠረተ ሲሆን በውድድሩ ውስጥ በመግባት የገበያውን ማዕበል ተቋቁሞ አሸንፎ የወጣው ብቻ ሕልውናውን አስከብሮ መኖር የሚችልበት ዓላማዊ ሁኔታ ያለ በመሆኑ በክልሉ በዚህ ዘርፍ የተሰማሩ/የሚሰማሩ ባለሀብቶች የሚያስፈልጋቸው የመረጃና ሌላ ድጋፍ ተደርጎላቸው በውጭ ገበያ ተወዳዳሪ መሆን የሚችሉበት ሁኔታ ሊፈጠር ግድ የሚል በመሆኑ ነው፡፡

በኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ሰነድ ላይ በግልጽ እንደተመለከተው መንግሥት በዘርፉ ለተሰማሩ ባለሀብቶች የሚሰጠው ድጋፍ በዓለም አቀፍ የገበያ ውድድር ውስጥ ገብተው ተወዳዳሪ በመሆን አሸናፊ የሚሆኑትን በማገዝ የውድድር መንፈስን ማጎልበት ነው እንጂ ሳይወዳደሩ በአቋራጭ ለመክበር የሚሯሯጡትን ጥገኛ ባለሀብቶችን አይደለም፡፡ ይኸው በኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ሰነዱ ላይ እንደሚከተለው ተቀምጧል፡፡

*#መንግሥት በጠንካራ የዓለም ገበያ ውድድር አሸንፎ የመውጣት አቅምን ከመገንባት ውጪ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የኢንዱስትሪ ልማት ማረጋገጥ እንደማይቻል ተገንዝቦ በኢኮኖሚያችን ውስጥ ጠንካራ የገበያ ውድድር እንዲሰፍን ማድረግ፣ መንግሥት ለልማታዊ ባለሀብቶች የሚሰጠው ሁሉን አቀፍ እገዛ የገበያ ውድድርን የሚያጠናክር እንጂ የሚያዳክም አለመሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ;*

በመሆኑም በክልሉ ውስጥ በውጭ ገበያ ዘርፍ የተሰማሩ/የሚሰማሩ ባለሀብቶች በዓለም አቀፍ ገበያ ውስጥ በመግባት ምርቶቻቸው/አገልግሎታቸውን በማቅረብ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ገበያን የማፈላለግ

መረጃን በቀላሉ የሚያገኙበትን፤ ገበያ የሚፈልገው ጥራትና ብዛት ያለውን ምርት በተፈለገው ጊዜ አምርተው ለማቅረብ የሚያስችላቸውን የገበያ መረጃ የሚያገኙበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡
በተለይም በውጭ ገበያ መረጃን በተገቢው ጊዜ ማግኘት እጅግ ጠቃሚ በመሆኑ ይህንን ባለሀብቶች በቀላሉ የሚያገኙበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡ ይህንኑ የሚሰጥ ተቋም ተጠናክሮ ይደራጃል፡፡ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶችም በመረጃ የተደገፈ ሥራ እየሠሩ ተወዳዳሪ መሆን እንዲችሉ የዓለም አቀፍ ገበያ መረጃ ካላቸው አካላት ጋር በቅርበት እንዲሰሩ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ፡፡

## 6. የኢንተርፕሪነርሺፕ፣ስትራቴጂክ ፕላኒንግና ፋይናንስ ልማት ንዑስ ፕሮግራም

ኢንተርፕሪነር ማለት አዲስ የንግድ ሃሳብ የሚያመነጭ፣ (Innovetor) የተለያዩ ግብዓቶችን (መሬት፣ ጉልበት፣ካፒታል) አደራጅቶ ለልማት የሚያውል፣ በቢዝነስ ሥራ ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉና በሥራ ላይ ሊፈጠሩ የሚችሉ አደጋዎች /Risk and Uncertainity/ ሊከሰቱ እንደሚችሉ በመገመት ይኸው ቢከሰት ለመሸከም በመወሰን ድርጅት የሚያቋቁም፣ በህብረተሰቡ ውስጥ ያለውንና ወደፊት ሊከሰት የሚችለውን የምርትና የአገልግሎት ፍላጎት አቅርቦት ክፍተት ለመሙላት የሚሠራ፣ሥራንና ሀብትን የሚፈጥርና በአጠቃላይ ለአገር ኢኮኖሚ ዕድገት ቁልፍ ሚና ያለው ሰው ማለት ነው፡፡ ኢንተርፕረነርሽፕ ማለት ደግሞ ከላይ በኢንተርፕረነሩ የሚከናወኑ ተግባራትን የማከናወን ሂደት ነው፡፡

የቢዝነስ ስራ ድፍረትና (courage) ልበ ሙሉነትን፣ እንዲሁም ጥረትን ወደ ሀሣብ (idea) የመቀየር፣ በቢዝነስ ውድድር ውሰጥ የመግባት ብሎም ወደ አንድ ወደማያውቁት መጻኢ ጊዜ ውስጥ ዘሎ የመግባት ድፍረትን የሚጠይቅ ነው::

የነጻ ገበያ መርህን ለሚከተል ሀገር አስተማማኝና ዘላቂነት ያለው እድገትና ልማት ለማምጣት ከሚወሰዱት የኢኮኖሚ ማሻሻያ እርምጃዎች ውሰጥ አንዱ የኢንተርፕረነር ልማት ፕሮግራም ነው:: ስለሆነም መንግስት ኢንተርፐርነሩ ራሱን ጠቅሞ አገሩንም የሚጠቅም ስራ እንዲሰራ የማብቃት፣ ከአነስተኛ ኢንቨስትመንት ተነስቶ ወደ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንቨስትመንት እንዲበቃ ድጋፍ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ሚናና ኃላፊነት አለበት:: መንግስት ይህንን ኃላፊነቱን ለመወጣት ተስማሚ የሆኑ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎችን ከማውጣት ጀምሮ ልዩ ልዩ ድጋፎችን እያደረገ ይገኛል፡፡

በክልላችን ባሳለፍናቸው የኢንቨስትመንት ዓመታት ከታየው ልምድ አብዛኛዎቹ ኢንቨስተሮቻችን የኢንተርፕረነርሺፕ ክህሎት ያላቸው ሳይሆኑ ወደ ንግዱ አለም የሚገቡት በፍላጎትና በድፍረት ብቻ ከመሆኑም ባሻገር መሰረታዊ የሆነ የቢዝነስ እውቀት ያላቸው አይደሉም:: ከፍተኛ የሆነ ንብረት ለባንክ በማስያዝ ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ መበደርን እንጂ በአንድ አመት ውስጥ እንኳ ምንያህል የባንክ ዕዳ እንደሚጠበቅባቸው በዚያው ዓመት ገቢያቸው ምንያህል እንደሆንና ለባንክ ምን ያህል መክፈል

እንዳለባቸው አስልተው የሚያውቁ አይደሉም፡፡ ባለሙያ የማማከር ልምዱም ፈጽሞ የሌለ፣ ቢኖርም ደግሞ እጅግ አናሳ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ በግሉ ኢንቨስትመንት ሴክተር የተሠማሩ ባለሀብቶች ያላቸው ካፒታል ውስን ከመሆኑ ባሻገር በፕሮጀክት መረጣ፣ ስለፕሮጀክቶቻቸው ሥራ አመራር በቂ ዕውቀት የሌላቸው፣ የሚቀጥሯቸው ሠራተኞች የሠለጠኑ ባለሙያዎች አለመሆናቸው፣ የኢንተርፕራነርሽፕ አቅማቸው አነስተኛ የሆነና ኢኮኖሚያዊ መረጃዎቻቸውን በአግባቡ የማይመዘግቡና የማይዙ በመሆናቸው ከየት ተነስተው ወዴት እንደሚደርሱ የሚያሳይ ግልፅ ራዕይ ይዘው የማይመሩ ናቸው፡፡ ስለዚህ በቢዝነስ ሥራ አመራር፣ በሰው ኃይል አስተዳደር፣ በሂሳብ መዝገብ አያያዝ፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ አመራረጥና አጠቃቀም፣ በክልሉ ንፅፅራዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ምርቶች በጥራት በማምረትና ምርት ማሻሻል፣ በገበያ ማፈላለግ በአገር አቀፍም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ መሆን የሚያስችል ብቃት እንዲኖራቸው ለማስቻል የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ሥራ አመራር ሥልጠናና የኢንቨስትመንት ልማት የምክር አገልግሎት የሚያገኙበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

የኢንተርፕረነርሺፕ ልማት ፕሮግራም ዋነኛ ዓላማ ከፍ ብሎ የቀረበውን የኢንተርፕረነሮቻችንን ባህሪያትና በኢንተርፕረነርሺፑ ልማትና እድገት ላይ ተጽዕኖ ያላቸውን ጉዳዮች ጠንቅቆ በመለየትና በማወቅ በክልሉ የኢንተረፕረነርሺፕ ዕውቀትና ክህሎት ብሎም ተነሳሽነትን በማጎልበት ባለሀብቶች በሀገራችን የኢኮኖሚ ዕድገትና ልማት ውስጥ የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ ነው፡፡

የኢንተርፕረነርሺፕ ልማት ንዑስ ፕሮግራም የሚከተሉት ፕሮጀክቶች ይኖሩታል፡፡ እነዚህም የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ልማት የሥራ አመራር ስልጠና፣ የምክር አገልግሎትና የፋይናንስ አቅርቦት ፕሮጀክቶች ናቸው፡፡

## 6.1 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ሥራ አመራር ሥልጠና ፕሮጀክት፣

በግሉ ኢንቨስትመንት ሴክተር የተሰማሩ ባለሀብቶች በብዛት የተሰማሩባቸው የግብርና፣የአግሮ-ፕሮሰሲንግ፣ የኢንዱስትሪና የአገልግሎት ሰጪ ዘርፎች ሲሆኑ አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያመለክቱትና በፕሮጀክቶች ክትትል ወቅት መረዳት እንደተቻለው አብዛኞቹ ፕሮጀክቶች ብቃት ያለው የሥራ አመራር እንደሌላቸውና በልማዳዊ የአሰራር/አመራር ዘዴ ቢዝነሳቸውን እየመሩ እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ስለዚህ የኢንቨስትመንት መስኮች የተለያዩ እንደመሆናቸው መጠን የሥልጠና ፍላጎት ጥናትን መሰረት በማድረግ የተለያዩ ሥልጠናዎች እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ ለባለሀብቶች የሚሰጡትም ሥልጠናዎች@ በስትራቴጂክ ፕላኒንግ፣ በሂሳብ መዝገብ አያያዝ፣ በሕጎችና ደንቦች ዙሪያ፣ በአገልግሎት አሰጣጥ፣ በምርት ጥራትና በምርት ማሻሻል፣ በተመጣጣኝ ቴክኖሎጂ አመራረጥ፣ምርትን በማስተዋወቅና በገበያ ማፈላለግ፣ አሁን ካለው የግሎባላይዜሽን ዘመን አንጻር ጥራቱን በጠበቀና በአለም አቀፍ ደረጃ

ተወዳዳሪነት ያለው የኤክስፖርት ምርት በማምረት ረገድና በመሳሰሉት ላይ ትኩረት ያደረጉ ሆነው እንደየሴክተሩ ሁኔታ እየታየ የሠልጣኞችን የትምህርት ዝግጅት ባገናዘበ መልኩ እንዴት መቼና የት እንደሚሰጡ እየተጠና ተግባራዊ የሚደረጉበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

በክልላችን ውስጥ የስራ አመራር ሥልጠና ከመስጠት አንጻር ልምዱ ያላቸው የክልሉ የስራ አመራር ተቋም፣ የግብርና ሙያ ማሠልጠኛ ፣ የእርሻ ምርምር ተቋም፣ የቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛና የግል ተቋማት፣ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች ተሳታፊ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ በሥልጠናው መስክ የሚሰማሩት ተቋማት በግሉ ኢንቨስትመንት ዘርፍ ያለውን የሥልጠና ፍላጎትና አቅርቦት ክፍተት በመለየት መሙላት እንዲችሉ የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የስልጠና ፕሮግራሞች ነድፈው እንዲንቀሳቀሱ ቅንጅት ተፈጥሮ ይሠራል፡፡

ሀገሪቱ ከምትከተለው ግብርና መር የልማት ስትራቴጂ አንጻር መንግስት ለግብርናው ዘርፍ በሰጠው ትኩረት መሰረት የአርሶ አደሩን/የአርብቶ አደሩን የቴክኖሎጂ ደረጃ ከፍ ለማድረግ የሚያስችሉ የግብርና ምርምር ሠራተኞች፣ ቴክኖሎጂን በማሸጋገር አርሶ አደሩን/አርብቶ አደሩን በማሠልጠን የሚሰሩ የኤክስቴንሽን ሠራተኞች፣ የእንስሳት ጤና ሃኪሞችና የህብረት ሥራ ሙያተኞችን በማሰልጠን ካለው ከፍተኛ ርብርብ ጎን ለጎን የግብርና ሥልጠናው በግብርና ዘርፍ የተሰማሩ የግል ባለሀብቶችንም መደገፍና ማጠናከር ስላለበት በዘርፉ ከተሰማሩ ባለሀብቶች ጋር በመመካከር የሚፈልጉትን የስልጠና ዓይነቶች ለይተው ማወቅና የሥልጠና ፕሮግራሞች በማዘጋጀት የአጭርም ሆነ የመደበኛ ሥልጠና አገልግሎቶች የሚሰጡበት ሁኔታ እንዲመቻች ይደረጋል፡፡ የሥራ አመራር ሥልጠናና የምክር አገልግሎት ከመስጠት አንፃር ከላይ የተጠቀሱት ተቋማት የስልጠና ፍልጎትን መሰረት በማድረግ በቅንጅት እንዲያቀርቡ የሚደረገው ሥልጠና እንዳለ ሆኖ በክልሉ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ደረጃ የሥልጠናና የምክር አግልግሎት የሚሰጥ መዋቅር በመፍጠር የባለሀብቶች ፕሮጀክቶች ባሉባቸው አካባቢዎች በመንቀሳቀስ የሥራ ላይና የአጭር ጊዜ ሥልጠናና የምክር አገልግሎቶች የሚሰጥበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

## 6.2. የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ልማት የምክር አገልግሎት ፕሮጀክት፣

በክልላችን በግሉ ኢንቨስትመንት ዘርፍ የምክር አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች ባለመኖራቸው ምክንያት የምክር አገልግሎት አስፈላጊነትም ሆነ ተፈላጊነት አይታወቅም ወይም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል ማለት ይቻላል፡፡ የምክር አገልግሎት በተሟላ ሁኔታ መስጠት ያለበት ባለሀብቶች ገና የኢንቨስትመንት ፈቃድ በሚጠይቁበት ጊዜ ሆኖ ከዚያ በኋላም ፕሮጀክቶቻቸውን መተግበር ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ በተከታታይ መሆን አለበት፡፡ በእያንዳንዱ የፕሮጀክት ትግበራ ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ከባለሀብቱ ጋር በቅርብ

በመከታተልና የምክር አገልግሎት በመስጠት ችግሮቹ እንዲቀረፉ በማድረግ ውጤታማ የልማት ሥራ እንዲኖር ማድረግ ይጠበቃል፡፡

የግል ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ትግበራ ከሚጀመርበት ጊዜ አንስቶ ተከታታይነት ባለው ሁኔታ የሚሰጡት የምክር አገልግሎቶች ፕሮጀክቶቹ ያሉባቸውን  ችግሮች በመዳሰስ ክፍተቶቹን በመሙላትና ድክመቶቹን በማሻሻል ላይ ያነጣጠሩ ይሆናሉ፡፡ እንደየፕሮጀክቶቹ ሁኔታ ስለሥራ አመራር፣ ስለሂሳብ አያያዝና አመዘጋገብ፣ ስለሰውኃይል አስተዳደር፣ ስለገበያ ጥናት፣ ምርት ማስተዋወቅና ሽያጭ፣ ስለምርት ጥራትና ማሻሻል፣ ስለተስማሚ ቴክኖሎጂ አመራረጥና ዘመናዊ አሰራር፣ ስለመረጃ አስፈላጊነትና አጠቃቀም፣ ስለፋይናንስ ምንጭና አጠቃቀም፣ ስለዋጋ አተማመን፣ በባለሀብቱና በአርሶአደሩ መካከል ሊኖር ስለሚገባው ትስስር ማለትም በኮንትራታዊ ትስስር (Outgrowers Scheme) ባለሀብቱ የሚያመርታቸውን ወይም የሚፈልጋቸውን የግብርና ምርቶች ባለሀብቱ በሚፈልገው መጠን ጥራቱን ጠብቆ (እንደ ሻይቅጠል፣ ቡና፣ ባዮ-ዲዚል ተክል፣ አትክልትና ፍራፍሬ  ወዘተ) በማምረት ለባለሀብቱ የሚሸጥበት ኮንትራታዊ ስምምነት የሚፈጥርበት እንዲሁም  በግብርናው ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች በአገሪቱ ከሚገኙ የግብርና ምርምር ማዕከላት ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖራቸው በማድረግ የምርምር ማዕከላቱን አዳዲስ ግኝቶችና አሰራሮች ተጠቃሚ የሚሆኑበት፣ ምርጥ ዘርን በማባዛትና በፈጣን ሥርጭት ላይ በመሰማራት ራሳቸውንና አርሶአደሩን ጭምር እንዲጠቀሙ የሚያስችል የምክር አግልግሎት እንዲያገኙ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ፡፡ ከላይ በተመለከተዉ ሁኔታ ባለሀብቱ በአካባቢዉ ከሚገኙት አርሶ አደሮች/አርብቶ አደሮች ጋር በአዉትግሮወርስ ስኪም ተሳስሮ ስለሚሠራበት ሁኔታ አሠራሩን ግልጽ የሚያደርግ ሞዳሊቲ ይዘጋጃል፡፡

## 6.3. የፋይናንስ አቅርቦት ፕሮጀክት፣

በክልሉ በግል ኢንቨስትመንት መስክ የተሰማሩ አብዛኞቹ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶቻቸው ፋይናንስ በባንክ ብድር ላይ  ንደሚመሠረት የፕሮጀክት ዶክመንቶቻቸው ያመለክ ሉ፡፡  በክልላችን ብቃት ያላቸው ኢንቨስተሮች እንዲኖሩ ከተፈለገ የባለሀብቶቻችን ዋነኛ ችግሮች መካከል በግምባር ቀደምነት የሚታየዉን የፋይናንስ ችግር መፍታት ትኩረት ሊሰጥ የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አዲስም ሆኑ ነባር ባለሀብቶች ኢንቨስትመንቶቻቸውን ለማስፋፋት ወይንም ለመጀመር የሚያስችል የባንክ ብድር የማግኘት ከፍተኛ ችግር  ንዳለባቸው ይታወቃል ፡፡ በመሆኑም የግሉን ኢንቨስትመንት የፋይናንስ ችግር የመፍታቱ ሥራ በቅድሚያ ለችግሩ መንስኤ የሆኑትን ጉዳዮች ማወቅና ማቃለል ይጠይቃል ፡፡

ይህ የፋይናንስ እጥረት ከሚቀረፍባቸው መንገዶች አንዱ ቁጠባን በማጠናከርና ከዚህም የሚሰበሰበውን ገንዘብ ለልማ  ዊ ባለሀብቶች ለረዥምና ለመካከለኛ ጊዜ ብድር የማቅረብ ተግባር ቁልፍ ጉዳይ ቢሆንም

በባንኮች ዘንድ ይህ ሥራ አይ ይም ። ባንኮች የተለያዩ ስልቶችንና ማበረ ቻቾችን በመጠቀም ሕብረተሰቡን ማነቃቃትና የቁጠባን ባህል በማጠናከር ፋይናንስ ማሰባበሰብ ሲገባቸው በአብዛኛው በራሱ ተነሳሽነት መጥቶ ገንዘብ የሚያስቀምጠውን ደንበኛ ከማስተናገድ ያለፈ ሥራ ሲሠሩ አይ ይም ።

በዚህ ውስን መንገድ የተሰበሰበውም ገንዘብ ቢሆን ከፍተኛ የካፒ ል ጥረት ባለበት ሀገር ለተበዳሪ ሊሰጥ ባለመቻሉ በባንኮች ተከማችቶ የሚቀመጠው ገንዘብ መጠን ከፍተኛ ነው። የንግድ ባንኮች የሚያሰባስቡት አብዛኛው ገንዘብ በጊዚያዊነት በእጃቸው የገባ በመሆኑ ባንኮቹ ለረዥምና ለመካከለኛ ጊዜ የኢንቨስትመንት ብድር ለመስጠት ሲቸገሩ ይ ያል። ይህንኑ ገንዘብ በረዥም ጊዜ ብድር መልክ ካበደሩ አስቀማጩ ገንዘቡን ሲጠይቅ ለመክፈል ይቸገራሉ። በመሆኑም የተገኘውን ውስን ብድር የአጭር ጊዜና በአብዛኛውም በንግድ ሥራ ላይ ያተኮረ ንዲሆን ያደርጋሉ ። ይህም ማለት ልማትን ከማስፋፋት አንፃር ከፍተኛ ሚና በማይጫወት መስክ ላይ የ ጠረ ብድር በመሆኑ ኢንቨስትመንትን የሚያበረ አይደለም። የክፍያውም ሆነ የብድር አመላለስ ሥርዓቱ ጅግ ኋላ ቀር ነው ።

ስለሆነም በአንድ በኩል በባንኮች አካባቢ በሚ የው የተበዳሪዎች መረጃ ጥረት፣ በተለይም ስለንግዱ ሕብረተሰብ በአጠቃላይ፣ ስለተበዳሪዎች ደግሞ የተሟላ፣ ወቅ ዊና ትክክለኛ መረጃ የማግኘት ችግር፣ ንዲሁም በባንኮች የማስፈፀም አቅም ማነስ የተነሳ ተመላሽነ ቸው አጠራጣሪ የሆኑ ብድሮች መበራከት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ተበዳሪ ያልተገኘለት ገንዘብ በባንኮች ዘንድ ተበራክቶ መገኘት ካልተወገደ በስተቀር የብድር አገልግሎቱ በሚፈለገው መጠን ሊዳብር አይችልም ።

በንግድ ባንኮች ዘንድ የሚ የውን ይህን ችግር ለማቃለል የኢትዮጵያ ልማት ባንክን አቅም በማሳደግ ጠንክር ያለ የገንዘብ አቅም ንዲኖረውና ከንግድ ባንኮች ጋር በሰፊውና በተቀናጀ ሁኔ የሚሠራበት ሁኔ ይመቻቻል ። በዚህ ረገድ ጉዳዩ ከሚመለከ ቸው አካላትና ከባለሀብቶች ጋር በመቀናጀት በጋራ የመረባረብ ሥራዎች ይከናወናሉ ። ንዲሁም ከባንኮችና ከሌሎች የፋይናንስ ተቋማት ጋር በመቀናጀት በክልሉ ለሚካሄድ የግል ኢንቨስትመንት የሚውል ፋይናንስ አቅርቦት የማመቻቸት ሥራዎች በዚህ ንዑስ ፕሮግራምና በሥሩ በ ቀፉ ፕሮጀክቶች አማካይነት ይከናወናሉ ።

የባለሀብቶችን የፋይናንስ ችግር የመፍታቱ ሥራ ከባለሀብቶቹ ከራሳቸው መጀመር ያለበት ነው። በባለሀብቶች ዘንድ የሚ የውን የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ችግር፣ የንግድ ሥራ አመራር ዕውቀት ማነስ፣ ዝቅተኛ የምርት መጠን፣ የምርት ጥራትና ምርታማነት ማነስ ወዘተ ጋር የተዛመዱ ፋይናንስን ለማሰባሰብ የመደራጀት ችግሮችን ለማቃለል የሚያስችሉ ሥራዎች ይሠራሉ ። ባለሀብቶች የፋይናንስ ብድርን ተጠቅመው በሂደት የራሳቸውን የካፒታል አቅም በማዳበር በገበያ ተወዳዳሪ ሆነው የሚሠሩበትን አቅጣጫ ንዲከተሉ ጥረት ይደረጋል ።

ለግል ባለሀብቶች የብድር አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት የሚገጥማቸዉን ብድር ያለመመለስ ችግር ለመቀነስና ለሚሰጡት ብድር የብድር ዋስትና ሽፋን እንዲያገኙ ለግል ኢንቨስትመንት ድጋፍ ሰጪ ባንኮችና ሌሎች የሚመለከ ቸውን አካላት በማስተባበር መንግስት የብድር ዋስትና ፕሮጀክት በክልሉ ንዲቋቋም ያደርጋል፡፡

## 7. የማስፈጸም አቅም ግንባታ ንዑስ ፕሮግራም፣

እንደማንኛውም የልማት ሥራ የግሉ ኢንቨስትመንት ልማት ያለ በቂ የአቅም ግንባታ ሥራ ውጤ ማና ተግባራዊ ሊሆን አይችልም፡፡ በዘርፉ የሚነደፍ የልማት ዕቅድ ያለበቂ የሰው ኃይል፣ አደረጃጀት ና አሰራር በተሟላ መልኩ ተግባራዊ መሆን የሚችል አይሆንም፡፡

የማስፈጸም አቅም ግንባታ ሲታሰብ አንዱ መነሳት ያለበት ጉዳይ በዘርፉ የሚፈለግ ብቃትና ጥራት ያለው የሰው ኃይል ከክልል እስከ ወረዳ ድረስ ባለው መዋቅር የማሟላት ተግባር ነው፡፡ያለሰው ኃይል ማንኛዉንም የልማት ሥራ ማከናወን የማይቻል በመሆኑ የሰው ኃይል የማሟላቱ ሥራ ቀዳሚ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ይሆናል፡፡

ሌላው በዚህ ንዑስ ፕሮግራም መነሳት ያለበት ጉዳይ የኢንቨስትመንት ሴክተር ልማት ፕሮግራምን ውጤታማ ለማድረግ የሰው ኃይል አቅም በሥልጠና የማጎልበት ሥራ ነው፡፡ ከዚህም አንጻር የግሉን ኢንቨስትመንት በማስፋፋትና በማበረታታት ከክልል እስከ ወረዳ ለተሰማሩና ለሚሰማሩ ባለሙያዎች ና ድጋፍ ሰጪ አካላት የተለያዩ የረዥም፣የመካከለኛና የአጫጭር ጊዜ ሥልጠናዎችን እንዲሁም የሥራ አመራርና የቴክኒክ ሙያ ሥልጠናዎችን በመስጠት አቅማቸውን ማጐልበት ወሳኝ ነው፡፡

ሌላው ከአቅም ግንባታ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ጉዳይ የግሉ ኢንቨስትመንት የሚጠቀምባቸውን የማምረቻ መሣሪያዎችንና ቴክኖሎጂዎችን ማሻሻል ነው፡፡ በዘርፉ የተሻሻሉ የማምረቻ መሣሪያዎችና ቴክኖሎጂዎች ሳይኖሩ በሚፈለገው ደረጃ ምርታማና በገበያ ተወዳዳሪ መሆን የሚቻል አይሆንም፡፡ በመሆኑም በዘርፉ የተሰማሩ ግለሰቦች ለሥራቸው አስፈላጊ የሆኑ የተሻሻሉ የማምረቻ መሣሪያዎችንና ቴክኖሎጅዎችን ንዲሁም የአሰራር ማንዋሎችን የሚያገኙበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር ትኩረት የሚሰጠው ሥራ ነው፡፡

ከአደረጃጀት አኳያ ምቹ ሁኔታ መፍጠርና የሰው ኃይልንም ማሟላት አስፈላጊ ቢሆንም ሥራውን ለመተግበር የሚያግዝ የማቴሪያል አቅም ግንባታ ሥራም መታለፍ የማይገባው ጉዳይ ስለሆነ ትኩረት ይሰጠዋል፡፡

ከአቅም ግንባታ አኳያ ሌላው ትኩረት ማግኘት ያለበት መንግሥት የግሉን ኢንቨስትመንት ሴክተር የሚያደራጅበት፣ የገበያ፣ የፋይናንስ፣ የሥልጠናና የምክር አገልግሎት፣ ወዘተ ድጋፎች የሚሰጥበት

ግልጽ የሆነ ፖሊሲና አሰራር ሊኖረው ይገባል። በመሆኑም የአቅም ግንባ ሥራን በተገቢው ማከናወን የግሉን ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም ለማሳካትና ለማፋጠን አንዱ የትኩረት አቅጣጫ ነው።

ስለዚህ የማስፈጸም አቅም ግንባታ ንዑስ- ፕሮግራምን ይበልጥ ውጤታማና ስኬታማ ለማድረግ እንዲቻል በንዑስ ፕሮግራሙ ሥር በዋነኛነት የአቅም ግንባታና የተቋማዊ አደረጃጀት ፕሮጀክቶች እንዲተገበሩ ይደረጋል።

## 7.1 የሥልጠናና ማቴሪያል አቅም ማጎልበቻ ፕሮጀክት፣

ከክልላችን ተጨባጭ ሁኔታ ስንነሳ ከኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ጀምሮ እስከ ዞን ኢንቨስትመንት ዴስክ ድረስ አሁን ያለው የሰው ኃይል በሥልጠናም ሆነ በማቴሪያል አቅሙ ያልጎለበተና ያልተሟላ ሲሆን በየደረጃው ያለው አመራርና አስፈጻሚ አካል እንዲሁም የሚመለከታቸው ወገኖችና ህብረተሰቡ የግል ኢንቨስትመንት ሴክተሩ በአገሪቱ አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ ልማት ላይ ስላለው ሚና በቂ ግንዛቤ የሌላቸው በመሆኑ የልማት ፕሮግራሙን ስኬታማ ማድረግ አስቸጋሪ ይሆናል። ከማስፈጸም አቅም ግንባታ አንዱ የአስፈጻሚ መ/ቤቶችን የማቴሪያል ፍላጎት ማሟላት ነው። ስለሆነም ከክልል አስከ ወረዳ ድረስ የሚገኘው የኢንቨስትመንት አስፈጻሚ መ/ቤቶችን የማቴሪያል ፍላጎት በመለየት የሚሟሉበት ሁኔታ ይመቻቻል። በሴክተሩ ውስጥ ያለው የሰው ኃይል፣ በየደረጃው ያለው አመራርና አስፈጻሚ አካል በየፈርጁ በቂ ሥልጠና የሚያገኝበት፣ የሚመለከታቸው ወገኖች፣ ህብረተሰቡ፣ የሲቪክና የብዙሃን ማህበራትም ስለልማት ፕሮግራሙ በቂ ግንዛቤ የሚያገኙባቸው የሥልጠና፣ የግንዛቤ ማዳበሪያና የውይይት መድረኮች ተዘጋጅተው በየደረጃው እንዲካሄዱ ይደረጋል።

## 7.2 ተቋማዊ አደረጃጃት ማሻሻያ ፕሮጀክት፣

በክልሉ ከፍተኛ የኢንቨስትመንት ፍሰት ባሉባቸው አካባቢዎች አሁን ያለው ተቋማዊ አደረጃጀት የልማት ፕሮግራሙን ማስጀመር ያስችል እንደሆነ እንጂ ስኬታማ ለማድረግ ፈፅሞ አያስችልም። ስለሆነም ቀልጣፋ የአንድ ማዕከል አገልግሎት አሰጣጥን ተግባራዊ ለማድረግና በግሉ ኢንቨስትመንት ሴክተር ዘላቂ ልማትን ለማስመዝገብ እንዲቻል በተለይ በታችኛው እርከን ያለውን ተቋማዊ አደረጃጃት መፈተሽና ማጠናከር ተገቢ ይሆናል።

የማስፈጸም አቅም ዋነኛ መሣሪያም ውጤትም ሊሆን የሚችለው የሠለጠነና፣ ብቃት ያለው የሰው ኃይል ከአስፈላጊው አሠራርና አደረጃጃት ጋር ሲጣመሩ በመሆኑ የልማት ፕሮግራሙን ስኬታማ ለማድረግ እንዳስፈላጊነቱ እየተጠና ከክልል ጀምሮ እስከ ዞን፣ ልዩ-ወረዳ፣ የከተማ አስተዳደሮችና ወረዳ ድረስ የሚዘልቅ ጠንካራ አደረጃጃትና መዋቅር እንዲኖር ይደረጋል።

# ክፍል ስምንት

# የግሉ ኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ፕሮግራም የአፈጻጸም ስልት' የክትትልና ግብረመልስ ሥርዓት

## 1. የግሉ ኢንቨስትመንት የልማት ፕሮግራም ማስፈጸሚያ ሥልቶች፣

### ሀ/ የግሉ ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮግራም ማስፈጸሚያ ተቋማዊ አደረጃጀት

በዚህ ፕሮግራም ውስጥ በተለያዩ ክፍሎች በዝርዝር እንደተመለከተው የግሉን ኢንቨስትመንት ዘርፍ ችግሮች በመለየት ችግሮቹ የሚቀረፉባቸው የተለያዩ ንዑሳን-ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ተቀርጸዋል፡፡ በፕሮግራሙ ውስጥ የተካተቱ ንኡሳን-ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን ለማሳካት የሚያስችል አደረጃጀት በተለያየ ደረጃ መፍጠር እንዲሁም ቀደም ብሎ ያለውንም አደረጃጀት ማጠናከር ግድ ይላል፡፡ ምክንያቱም ጠንካራና ብቃት ያለው የሰው ኃይል የያዘ መዋቅር ካልተፈጠረ በስተቀር በአጠቃላይ ፕሮግራሙን በሚፈለገው ሁኔታ ተግባራዊ የማድረጉ ጉዳይ ጥያቄ ውስጥ ይገባል፡፡ ስለሆነም በፕሮግራሙ ውስጥ የተካተቱ ሥራዎች በሚጠይቁት መሰረት አደረጃጀቱ ከክልል ጀምሮ እንደ አስፈላጊነቱ እስከ ወረዳ ድረስ ይደራጃል፡፡

በክልል ደረጃ የሚኖረው መዋቅር ትኩረት ሰጥቶ መስራት የሚገባው ጉዳይ በዋናነት በጥናትና ምርምር ሥራዎች ላይ በማተኮር ለባለሀብቱ ክትትልና ድጋፍ መስጠትን መሰረት በማድረግ ይሆናል፡፡ የሚደራጁ መምሪያዎችና የስራ ክፍሎችም ይህንኑ መሠረት ያደረጉ ይሆናሉ፡፡ በዚህ መሰረት የክልሉ መዋቅር የትኩረት አቅጣጫዎች የሚሆኑት፣

i. የክልሉን እምቅ ሀብት በአግባቡ የመለየት፣ ለግሉ ኢንቨስትመንት የሚሆን የገጠርና የከተማ መሬቶችንና የኢንዱስትሪ መንደሮችን በአግባቡ እንዲዘጋጁ የማድረግና የማስተዳደር ሥራን ማከናወን፣
ii. ከላይ በተመለከተው መሰረት የክልሉን ንፅፅራዊ ጠቀሜታን መሰረት አድርጎ የተለየውን የኢንቨስትመንት እምቅ ሀብት በተገቢው መንገድ የማስተዋወቅ ሥራን ማከናወን፣
iii. በክልሉ በተለያዩ ዘርፎች የተሰማሩ/የሚሰማሩ ኢንቨስተሮች የፕሮጀክቶችን አፈጻጸም በቅርብ በመከታተል ተገቢ ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ የማመቻቸትና ችግሮች ሲያጋጥሟቸው ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የሚፈታበትን ሁኔታ መከታተል፣
iv. የተጠናከረ የመረጃ አገልግሎት የሚሰጥበትን ሁኔታ መነሻ ያደረገ የመረጃ መረብ ዘርግቶ መሥራት፣
v. በጥናትና ምርምር በመመርኮዝ በክልሉ ለተሰማሩ የግል ባለሀብቶች የስትራቴጂክ ፕላኒንግና የኢንተርፕረነርሽፕ ልማት ሥልጠና የሚሰጥና የሚያስተባብር፣ የምክር አገልግሎትና

አደረጃጀት ሥራ መስራት፣

vi. ባለሀብቶች የውጭ ገበያ መረጃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የመረጃ መረብ በመዘርጋት የማገዝ ሥራ ማከናወን፣

vii. ከተለያዩ የመሰረተ ልማት ፣የፋይናንስና ለግል ኢንቨስትመንት ልማት ድጋፍ ከሚሰጡ ሌሎች ተቋማት ጋር በቅንጅት የሚሠሩ ሥራዎችን የማስተባበርና አቀናጅቶ መምራትና የመሳሰሉትን በዋናነት የሚያከናውን አደረጃጀት ይፈጠራል፡፡

በዞን ደረጃ የሚኖረው መዋቅር በዋናነት በአንድ ማዕከል አገልግሎት አቅርቦት መርህ መሰረት ለባለሀብቶች የዞኑን እምቅ ፖቴንሻል ከማስተዋወቅ ጀምሮ የፈቃድ አፈጻጸምና ምዝገባ ሥራዎችን፣ የመሰረተ ልማትና ሌሎች አገልግሎቶችን ባለሀብቶች ከአንድ ማዕከል የሚያገኙበትን ሁኔታ መሠረት ያደረገ መዋቅር ይሆናል፡፡

በዚህም መሰረት፣

i. የፈቃድ አፈጻጸምና ምዝገባ ሥራ የማከናወን፣

ii. የዞኑን ፖቴንሻል የማስተዋወቅ፣

iii. በዞኑ የኢንቨስትመንት መሬት የሚከለልበትንና የሚዘጋጅበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

iv. በዞኑ ውስጥ የሚገኙ ለኢንቨስትመንት የተከለሉ ቦታዎች የመሰረተ ልማት አገልግሎት ሌሎች ግብአቶችን የሚያገኙበትን ሁኔታ ላይ ድጋፍ መስጠት ፣

v. ከፍትህ ጋር የተዛመዱ ሥራዎችን በቅርበት የሚያገኙባቸውን ክፍሎች በዋናነት የያዘ አደረጃጀት ይፈጠራል፡፡ አደረጃጀቱ እንደአስፈላጊነቱ በልዩ ወረዳና በወረዳም ደረጃ ሊፈጠር ይችላል፡፡

vi. የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች እንቅስቃሴና፣የሚያጋጥሙ ችግሮች እንዲሁም ለኢንቨስትመንት መስፋፋት የሚያግዙ ልዩ ልዩ ጉዳዮችን ለማሟላት የሚረዳ የክትትል ተግባር በተጠናከረ መልኩ ይከናወናል፡፡

በአጠቃላይ የልማት ፕሮግራሙን ተግባራዊ ለማድረግ የሚፈጠረው አደረጃጀትና መዋቅር የሚፈልገው የሰው ኃይል እንዲሁም ሥራው ትልቅ ግምት የሚሰጠውና ከፍተኛ የሆነ መስጠትን (commmitmenet) የሚጠይቅ በመሆኑ የመዋቅሩ ጥናት ይህንኑ መነሻ አድርጎ የሥራውን ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ተወዳዳሪ የሆነ የሰው ኃይልን ሊይዝ በሚችል መልኩ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ ይህም በአጠቃላይ የተቋሙን ደረጃ እንደሚያሻሽል ይጠበቃል፡፡

**ለ/ በግሉ ኢንቨስትመንት ሴክተር የተጠኑ ጥናቶችን መጠቀምና አዳዲስ ጥናቶችን ማካሄድ፣**

የግሉን አንቨስትመንት ሴክተር የልማት ፕሮግራም ለማስፈጸም በክልሉም ሆነ በአገር አቀፍ ደረጃ በተለያዩ አካላት የተጠኑ ንጽጽራዊ ጠቀሜታ ያላቸውና ተወዳዳሪነትን የሚያረጋግጡ ጥናቶችን

በማሰባሰብና አዳዲስ ጥናቶችን እንዳስፈላጊነቱ ማካሄድ ትኩረት ሰጥቶ በማከናወን በጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡

### ሐ/ በንዑስ ፕሮግራሞቹ ውስጥ የተመለከቱ ፕሮጀክቶችን አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ፣

የልማት ፕሮግራሙን ለማስፈጸም የተለያዩ ፕሮጀክቶችን አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ንዑሳን ፕሮግራሞቹን ለማስፈጸም የሚዘጋጁት ፕሮጀክቶች የየልማት መስኩን ዝርዝር ችግሮች፣ የአፈጻጸም ሥልቶች፣የሚያስፈልጉ ግብአቶችን ወ ዘ ተ ባካተተ መልኩ ተዘጋጅተው ተግባራዊ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

### መ/ ለፕሮግራሙ ስኬት የሚመለከታቸውን አካላት ማቀናጀትና ማስተባበር፣

የግሉን ኢንቨስትመንት ሴክተር የልማት ፕሮግራም ለማስፈጸም ኃላፊነት ያለባቸው የፌዴራል ተቋማትና ከክልል እስከ ወረዳ ድረስ በየደረጃው ያሉት የአመራር አካላት፣የፋይናንስና የመሰረተ-ልማት መ/ቤቶች፣ የከተሞች አስተዳደሮችና ማዘጋጃ ቤቶች፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ህብረተሰቡንና ባለሀብቶችን አቀናጅቶ ማንቀሳቀስ ያስፈልጋል፡፡ ይህም ሲሆን በክልላችን ያለውን ማንኛውንም ሀብት በሚፈለገው መጠን በመጠቀም የልማት ፕሮግራሙን እውን ማድረግና የሚፈለገውን ፈጣንና አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ማምጣት ስለሚቻል ሁሉም ኃይሎች ከዚህ አንጻር እንዲረባረቡ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በከተማም ሆነ በገጠር የኢንቨስትመንት መሬት አቅርቦት ረገድ ያለውን ችግር በመፍታት ዝግጅቱንና አሠጣጡን ቀልጣፋ ለማድረግ የወጣው መመሪያ ፀድቆ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ ከመሬት ጉዳይ ጋር ተያይዘው የሚዘጋጁ መመሪያዎች ላይም በየደረጃው ያሉት አመራር አካላት፣ የሚመለከታቸው ወገኖችና ህብረተሰቡ በቂ ግንዛቤ አግኝተው ለልማት ፕሮግራሙ ስኬት የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም ፕሮግራሙን ለማስፈጸም የሚረዱ አዋጆች፣ ደንቦች፣መመሪያዎችና ማኑዋሎች እንደአስፈላጊነቱ እንዲዘጋጁ ይደረጋል፡፡

ለልማት ፕሮግራሙ ንዑሳን ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ ከፍተኛ በጀት ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም ብር 1,101,851,736 (አንድ ቢሊዮን አንድ መቶ አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ሀምሳ አንድ ሺ ሰባት መቶ ሰላሳ ስድስት) የሚያስፈልግ ሲሆን አብዛኛውን በጀት የፌዴራልና የክልሉ መንግስት የሚሸፍኑት ሲሆን ቀሪው ደግሞ ከተለያዩ የልማት አጋሮች ሞቢላይዝ የሚደረግ ይሆናል፡፡

### ሠ/ የግሉን ኢንቨስትመንት ሴክተር የገበያ ተወዳዳሪነት ለማረጋገጥ፣

የግል ባለሀብቱ በግብርናውም ሆነ በኢንዱስትሪው ክፍላተ-ኢኮኖሚ በክልል ደረጃ ንፅፅራዊ ጠቀሜታ ባላቸው በሀገርአቀፍም ሆነ በዓለምአቀፍ ደረጃ የተወዳዳሪነት ብቃት ያላቸው ምርቶችንና አገልግሎቶችን በጥራት፣ በብዛት፣በተመጣጣኝ ዋጋና በሚፈለገው ጊዜ ማቅረብ እንዲችሉ ማድረግና ምርቶቻቸውንና

አገልግሎቶቻቸውን የሚያስተዋውቁባቸውና የሚሸጡባቸው የንግድ ትርኢቶችና ባዛሮች እንዲዘጋጁ ይደረጋል፡፡

### ረ/ በየደረጃው የተሞክሮ ልምድ ልውውጥ ማድረግ፣

ባለሀብቶች በክልሉ የተለያዩ ዞኖች በግል ኢንቨስትመንት ልማት ሴክተር ተሰማርተው የተሻለ ልምድ ካካበቱ፣ በተለያዩ ክልሎች ካሉና መልካም ተሞክሮዎችን ካስመዘገቡ ባለሀብቶችና፣ ከመንግስት የልማት ድርጅቶች ልምድ የሚለዋወጡበትና የተሻሉ አሰራሮችን የሚቀስሙበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡ የውጭ ሀገር ተሞክሮዎች ልምድም በሥልጠና መልክ እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡

### ሰ/ ማበረታቻና ዕውቅና መስጠት፣

ለግል ኢንቨስትመንት ልማት ውጤታማነት የላቀ አስተዋጽኦ ላደረጉ ግለሰቦች፣መንግስታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶችና ተቋማት፣ባለሀብቶች፣ የጎላ እገዛ ላደረጉ ባለሙያዎች በየወቅቱ ለፈጸሙት ተግባር ግምገማ በማድረግ ጥሩ ውጤት ላስመዘገቡት የማበረታቻ ሽልማትና ዕውቅና ይሠጣል፡፡

## 2. የግሉ ኢንቨስትመንት ሴክተር ልማት ፕሮግራም የአፈጻጸም ደረጃዎች፣

በክልላችን ባለፉት 15 ዓመታት በርካታ የግል ባለሀብቶች በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች የተሰማሩ ቢሆንም ዘርፉ በሥራ ዕድል ፈጠራ፣ የተለያዩ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን በማሸጋገር ረገድ፣ በግብርናና በኢንዱስትሪው ክፍላተ-ኢኮኖሚዎች ትስስር በመፍጠር ረገድ፣ በአርሶ አደሩ/ አርብቶ አደሩና በግብርና በተሰማራው ባለሃብት መካከል ትስስር በመፍጠር ረገድ፣ በአጠቃላይ በክልሉ ብሎም በሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ላይ የሚጫወተውን ሚና በተመለከተ በየደረጃው የሚገኙ አመራርና አስፈፃሚ አካላት፣ ህብረተሰቡ፣ የሲቪክና የብዙሃን ማህበራት፣መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በቂ ግንዛቤ እንደሌላቸው የእስካሁኑ ተሞክሮአችን ያመለክታል፡፡

ስለዚህ በመጀመሪያ ደረጃ ዋናው የልማት ሥራ በሚከናወንበት በታችኛው የአስተዳደር እርከን የሚገኙ የአመራር አካላትና ህብረተሰቡ በቂ ግንዛቤ አግኝተው ለልማት ፕሮግራሙ ስኬት የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ለማስቻል በቂ የውይይትና የሥልጠና ፕሮግራሞች በሚያመች መልኩ ተነድፈው ተግባራዊ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የፕሮግራሙ አፈጻጸም ሂደት በንዑሳን ፕሮግራሞች ውስጥ የተመለከቱ ፕሮጀክቶችን በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡ የሚቀረጹት ፕሮጀክቶች፣ የኢንተርፕሪነርሽፕ ልማት፣ የተለያዩ የሥልጠናና የምክር አገልግሎቶች፣ የመሰረተ ልማት፣ የምርት ጥራትና ምርታማነት ማሻሻያ፣ የፋይናንስ፣ የመረጃ ፣የአንድ ማዕከል አገልግሎት አሰጣጥና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ንዑሳን

ፕሮግራሞቹንና ፕሮጀክቶቹን ለማስፈጸም የሚረዱ መመሪያዎችና የአሰራር ማኑዋሎች ይዘጋጃሉ፡፡ ፕሮጀክቶቹንም ለማስፈጸም የሚረዱ ወይም የሚያግዙ የተለያዩ ሕጎችና ደንቦች እንዲዘጋጁ ይደረጋል፡፡

በሦስተኛ ደረጃ የልማት ፕሮግራሙን አፈጻጸም ስኬታማ ለማድረግ በንዑስ ሴክተሩ ለተሰማሩ ባለሙያዎች፣ ባለድርሻ አካላትና ተባባሪዎች በሥልጠናና በልምድ ልውውጥ አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ የሚከናወነው ተግባር ነው፡፡

የልማት ፕሮግራሙን በየደረጃው ማስፈጸም እንዲቻል በክልል፣ በዞን፣ በልዩ ወረዳና በወረዳ ደረጃ ህብረተሰቡን፣ የሚመለከታቸውን የመንግስት አመራር አካላት፣ባለሀብቶችን ፣የግብርናና የቴክኒክ ማሠልጠኛ ተቋማትን፣መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ያቀፈ ቅንጅት እንደ አስፈላጊነቱ ይቋቋማል፡፡ ይህንንም የልማት ፕሮግራም በአንድ ጊዜ አሟልቶ ተግባራዊ ማድረግ ስለማይቻል በየደረጃው ቅድሚያ የሚሰጣቸው ሥራዎች ተግባራዊ እየተደረጉ፣ የሚታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች እየተገመገሙ አስፈላጊው ማስተካካያ እየተደረገበት በሂደት ወደተሟላ ተግባር የሚገባበት ይሆናል፡፡

## 3. የግሉ ኢንቨስትመንት ሴክተር ልማት ፕሮግራም ማስፈጸሚያ ትስስር፣

የግሉን ኢንቨስትመንት ሴክተር የልማት ፕሮግራም ለማሳካት በርካታ ችግሮች ይኖራሉ፡፡ እነዚህም የገጠርና የከተማ ኢንቨስትመንት መሬት አቅርቦትና አሰጣጥ፣ የመሰረተ ልማት አቅርቦት፣ የሥልጠናና የምክር አገልግሎቶች፣ የፋይናንስ፣ የገበያ፣ የተመጣጣኝ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ የምርት ማሻሻልና የምርት ጥራትና የመሳሰሉት ችግሮች ሲሆኑ እነዚህ ችግሮች በአንድ ወይም በተወሰኑ አካላት ጥረት ብቻ ሊፈቱና ዉጤት ላይ መድረስ ስለማይቻል ችግሮቹን ከመፍታት አንጻር ከሚመለከታቸው አካላትና ኃይሎች ጋር ትስስር መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ ይህንንም ትስስር ጠቅለል ባለ መልኩ በሁለት መልኩ ማየት ይቻላል፡፡ በአንድ በኩል በግሉ ኢንቨስትመንት ልማት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚሳተፉ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (ከክልል እስከ ወረዳ ድረስ ያለው አመራርና አስፈጻሚ አካል፣የመሰረተ ልማት መ/ቤቶች፣ የግብርናና የቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛ ተቋማት፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ኮሌጆች፣ የፋይናንስ ተቋማት፣የልማት ፕሮግራሙን የሚደግፉ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ወዘተ) እና በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶች ናቸው፡፡ በሌላ ወገን ደግሞ የግል ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በሚገኙባቸው አካባቢዎች የሚኖረው ህብረተሰብ፣ የሲቪክና የብዙሃን ማህበራት ናቸው፡፡ ስለዚህ ከእነዚህ ሁለት ወገኖች ጋር በመቀናጀትና በመተሳሰር ለፕሮግራሙ ስኬት የየራሳቸውን አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ተገቢው ጥረት ይደረጋል፡፡

## 4. የልማት ፕሮግራሙ ክትትል፣ ግምገማና ግብረ-መልስ፣

የክልሉን የግል ኢንቨስትመንት ሴክተር ልማት ፕሮግራም በሚፈለገው አቅጣጫ ለመምራትና የሚፈለገው ግብ ላይ ለመድረስ ግልጽ የሆነ የክትትልና የግምገማ ሥልቶችና ነጥቦች /አመልካቾች/ እንዲኖሩ ይደረጋል፡፡ ለዚህም እንዲያመች ፕሮግራሙን በመጀመሪያ ደረጃ በዓመታዊ ዕቅዶች፣ በሥራ መዘርዝር፣በንዑስ ፕሮግራሞች፣ በፕሮጀክቶችና በውጤት ተኮር ዕቅድ መዘርዘር አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በመቀጠልም ፕሮግራሙ ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ከመግባቱ በፊት በአጠቃላይ በግሉ ዘርፍ ተሰማርተው የሚገኙ ባለሀብቶች ያሉበትን ደረጃ የሚያሳይ መረጃ ይደራጃል፡፡

ወቅታዊ ሪፖርቶች፣ የመስክ ግምገማዎች፣ ፎረሞች፣ ሲምፖዚየም፣ ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ ግምገማዎች፣ ከክልል እስከ ፕሮጀክት ሳይት ድረስ የሚደረጉ የተለያዩ ጥናቶች የፕሮግራሙ ዋነኛ የክትትልና ግምገማ ሥልት ይሆናል፡፡ የፕሮግራሙን ዕቅድ አፈጻጸም፣ ሴክተሩ የፈጠረውን የሥራ ዕድል፣ የተገኘው የአገር ውስጥና የውጭ ገበያ፣ ለህብረተሰቡ ኑሮ መሻሻል ያበረከተው አስተዋፅኦ፣ የተፈጠረው የኢንተርፕሪነርሽፕ አቅም፣ የተገኘው የቴክኖሎጂ ሽግግርና አዳዲስና ዘመናዊ አሰራር፣ በግብርናና በኢንዱስትሪው መካከል የተፈጠረው ትስስር፣ በግብርናው መስክ በተሰማራው ባለሀብትና በአርሶ አደሩ/አርብቶ አደሩ መካከል የተፈጠረው ትስስር ወዘተ እንደመለኪያ እየታየ የፕሮግራሙ አፈፃጸምና ውጤታማነት በየወቅቱ ይገመገማል፡፡

## ማጠቃለያ

የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ሰፊ የሰው ይልና የተፈጥሮ ሃብት ንዳለው የሚ ወቅ ነው፡፡

የክልሉ መንግሥት በክልሉ ውስጥ ያለውን የሰው ኃይልና የተፈጥሮ ሃብት ለመጠቀም ና የሕዝቡን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ለመፍ ት መጠነ ሠፊ የልማት ንቅስቃሴ በየዘርፉ በማካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ በዚህም የልማት ንቅስቃሴ ባለፉት ዓመ ት ቀላል የማይባሉና ለቀጣይ የልማት ንቅስቃሴ መሰረት ሊሆኑ የሚችሉ ውጤቶች በግብርና፣ በምግብ ዋስትና፣ በዘላቂ ልማትና ድህነት ቅነሳ፣ በትምህርትና በጤና፣ በንጹህ ውሃ አቅርቦት፣ በገጠር መሠረተ ልማት፣ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት፣ በቤት ልማት፣ በግል ባለሀብት ማስፋፋት ወዘተ... ተገኝተዋል፡፡

የክልሉ መንግሥት የክልሉን ልማት ለማፋጠን ያለውን ምቅ ሃብት የሚያሳይ ጥናት ያካሄደ ሲሆን በዚህም የሀብት ሁኔ ፣ የልማት አቅምና ድሎች በዝርዝር ተለይተዋል፡፡ ባለፉት 15 ዓመታት በርካታ ባለሀብቶች በክልሉ የተለያዩ የኢንቨስትመንት መስኮች ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ሲሆን እስካሁን ፕሮጀክቶቻቸውን በመተግበር ረገድ ያጋጠሟቸውን ችግሮች መሠረት በማድረግና የክልሉን ተጨባጭ ሁኔ ከግምት ውስጥ በማስገባት የግሉን ኢንቨስትመንት ሴክተር ልማት በማፋጠን በዘርፉ ለተሰማሩ አካላት የተቀናጀና ሁሉ አቀፍ ድጋፍ መስጠት አልተቻለም፡፡ ይህንን ችግር በተቀናጀ መልኩ ለመቅረፍና

ተግባራዊ እንቅስቃሴውን አጠናክሮ ለማስቀጠል እንዲቻል የግል ኢንቨስትመንት ሴክተር ልማት ፕሮግራም ተዘጋጅቷል፡፡

